Addis Ababa University
አዲስ፡አበባ፡ዩኒቨርሲቲ


የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረምረቃ መርሐግብር


# በተማሪዎች የአማርኛ ትምህርት የማንበብና የመፃፍ ክሂሎች ላይ የመምህራን ቃላዊና ፅሁፋዊ ምጋቤምላሽ አቀራረብ ትንተና

## (በምስራቅ ጉራጌ ዞን ኬላ ወረዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)

ለአማርኛን ማስተማር (TeAm) ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት


በ ደረጀ ስለሞን



2016 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# በተማሪዎች የአማርኛ ትምህርት የማንበብና የመፃፍ ክሂሎች ላይ የመምህራን ቃላዊና ፅሁፋዊ ምጋቤምላሽ አቀራረብ ትንተና

## (በምስራቅ ጉራጌ ዞን ኬላ ወረዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎችጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረምረቃ መርሐግብር

አማርኛን ማስተማር (TeAm) ማስተር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ ደረጀ ሰለሞን

የጥናቱ አማካሪ

ዳዊት ፍሬህይወት (ዶ/ር)

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረምረቃ መርሐግብር

# በተማሪዎች የአማርኛ ትምህርት የማንበብና የመፃፍ ክሂሎች ላይ የመምህራን ቃላዊና ፅሁፋዊ ምጋቤምላሽ አቀራረብ ትንተና

## (በምስራቅ ጉራጌ ዞን ኬላ ወረዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)

በ ደረጀ ሰለሞን

2016 ዓ.ም.

**የፈተና ቦርድ አባላት**

**የአማካሪ ስም፡-**

ዶክተር ዳዊት ፍሬህይወት ፊርማ______________ ቀን______________

**የውጭ ፈታኝ ስም፡-**

ዶክተር መሰሉ መንግስቱ ፊርማ______________ ቀን______________

**የውስጥ ፈታኝ ስም፡-**

ዶክተር ጌታቸው እንዳላማው ፊርማ______________ ቀን______________

# የአጥኚው ማረጋገጫ (Declaration)

ይህ ጥናት "በተማሪዎች የአማርኛ ትምህርት የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች ላይ የመምህራን ቃላዊና ጽሁፋዊ ምጋቤምላሽ አቀራረብ ትንተና (በምስራቅ ጉራጌ ዞን ኬላ ወረዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት") በሚል አብይ ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድኅረ- ምረቃ መርሐግብር ለአማርኛን ማስተማር (TeAm) ማስተር ዲግሪ ማሟያ የቀረበው ጥናት፣ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑን እና በጥናቱ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን መረጃዎችም ሆነ ዋቢዎች በትክክል መግለጼን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም፡- ደረጀ ሰለሞን ጀምበር

ፊርማ፡- ______________________

ቀን፡- ________________________

ቦታ፡- አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

# ምስጋና

በማስቀደም ለተፈቀደው ሰዓት አድራሽ፣ አቅምን ሰጪና ጠባቂ ለሆንኸው አምላኬ ምስጋናዬ ይድረስህ፡፡

በመቀጠልም ዶክተር ዳዊት ፍሬ ሕይወትን እድሜ ከሰላም ጋር ይስጥልኝ፡፡ ከተወሰኑ ደጋግ ሰዎች ጎን አግኝቻቸዋለሁና! ልጅ አባትን መርቆ አይሆንም፤ ልጆች በአባታቸው ይባረካሉ እንጂ፡፡ የመልካምነት ሙላትን እያደሉ አጀግነውኛል፡፡ ህፀፄን እያቃኑ፣ ጎደሎዬን እያሟሉ ያለመሰላቸት ድካማቸውን እየቻሉ ለትውልድ፣ ለሃገር፣ ለማህበረሰብና ለቤተሰብ እንድደርስ የድርሻቸው አልቀረም፡፡ አመሰግናለሁ!

የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የማረቆ ልዩ ወረዳ፣ ጌታ ወረዳ፣ የምስራቅ ጉራጌ ዞን እና ኬላ ወረዳ የኬላና ጎጌቲ አማርኛ ቋንቋ መምህራን (የሙያ አጋሮቸ) ብዙ ነገሮችን ያገኘሁባችሁ በመሆኑ ሃገሬን እንዳገለግል የበኩላችሁ አለበትና የእውነት ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡

ለአአዩ እንቁ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል መምህራን፣ አቶ ተሾመ እምሩ፣ አቶ ደርቤ ጫኔ፣ አቶ አለምይሁን እርቄና ወይዘሮ ትዕግስት ጌታሁን ላደረጋችሁልኝ ድጋፍና ማበረታቻ ፈጣሪ ይስጥልኝ፡፡ ከነቤተሰቦቻችሁ ሰላም ተመኝቻለሁ፡፡

በመጨረሻም ከዚህ ጥናት ዝግጅት ጋር በተያያዘ እንደስህተት የሚቆጠሩ ማስተካከያዎች ካስተዋላችሁ ይቅርታም ምድቡ ከምስጋና ጎን ነውና ‹‹እኔ አጥፍቸ ከሆነ እናንተ በመንፈስ የምትኖሩ አርሙት›› እላለሁ፡፡

# አጠቃሎ (Abstract)

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በተማሪዎች የአማርኛ ትምህርት የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች ላይ የመምህራንን ቃላዊና ጽሁፋዊ ምጋቤምላሽ አቀራረብ መተንተን ነው፡፡ ተጠኝዎቹም በምስራቅ ጉራጌ ዞን ኬላ ወረዳ 2ኛ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ አምስት መምህራን ሲሆኑ በጠቅላይ እና 70 ተማሪዎች በእጣ ናሙና ተወስደዋል፡፡ 55ቱ ተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቁን በአግባቡ ሞልተው መልሰዋል፣ በመሆኑም በትንተና ክፍሉ የተካተቱት እነዙህ ብቻ ናቸው፡፡ የጥናቱን ዓላማ ለማሳካትም በሰነድ ፍተሻ፣ በምልከታ፣ በቃለመጠይቅና በጽሁፍ መጠይቅ መረጃዎች ተሰብስበው፣ በአይነታዊ እና በመጠናዊ መተንተኛ ዘዴዎች በአፅንኦት ተተንትነዋል፡፡ የጥናቱ ግኝትም የቋንቋ መምህራን የማንበብና መጻፍ ክሂሎችን ሲያስተምሩ ሁሉንም የምጋቤምላሽ ዓይነቶች እየቀያየሩ ወይም አንዱን ከአንዱ ጋር እያጣመሩ በሚገባ መጠቀም አለመቻላቸውን፣ ብዙውን ጊዜ የግልና የብጤ (ጓደኛ) ምጋቤምላሾችን በመጠቀም ምጋቤምላሽ እንደማይሰጡ እና በምጋቤምላሽ አሰጣጥ ወቅት ማስረጃዎችን እንጂ ደጋፊ ምልክቶችን እንደማይጠቀሙ እና የመምህራን ምጋቤምላሽ አቀራረብ የተለያየ መሆኑን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ከጥናቱ መሰረታዊ ግኝቶች በመነሳት አስተያየቶችን ማቅረብ የተቻለ ሲሆን የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ለአራቱም የምጋቤምላሽ ዓይነቶች ትኩረት ሰጥተው ለተማሪዎች የሚገባቸውን ምጋቤምላሽ እኩል ሊባል በሚችል ደረጃ ቢሰጡ፣ መምህራን ለገምጋሚ ምጋቤምላሽ ዓይነት ትኩረት በመስጠት ክፍል ውስጥ ምጋቤምላሻቸውን ማቅረብ ቢችሉ፣ ምጋቤምላሽ በሚሰጡበት ወቅት የመሰላቸትና የድካም ስሜት በአንዳንድ መምህራን የተስተዋለ ስለሆነ በይበልጥ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን በሚያስተምሩበት ወቅት ድካማቸውን ሊያስወግድ የሚችሉ ዘዴዎችን ቢያመቻቹ የሚሉት ቀርበዋል፡፡

# የይዘት ማውጫ

**ይዘት** **ገፅ**

የአጥኚው ማረጋገጫ (Declaration) i
ምስጋና ii
አጠቃሎ (Abstract) iii
ምዕራፍ አንድ 1
መግቢያ 1
1.1 የጥናቱ ዳራ 1
1.2 ሰበበ ጥናት 3
1.3 የጥናቱ ዓላማ 4
1.4 የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች 4
1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ 5
1.6 የጥናቱ ወሰን 5
1.7 የጥናቱ ውስንነት 6
1.8 የቁልፍ ቃላት ትርጉም ወይም ፍች 6
ምዕራፍ ሁለት 7
ክለሳ ድርሳናት 7
2.1 የማንበብ ክሂል ምንነት 7
2.1.1 የማንበብ ክሂል ትምህርት አስፈላጊነት 8
2.1.2 የማንበብ ክሂል ትምህርት በክፍል ውስጥ አቀራረብ 9
2.2 የመጻፍ ክሂል ምንነት 10
2.3 የምጋቤምላሽ ምንነትና ተያያዥ ጽንሰ- ሀሳቦች 12
2.3.1 የምጋቤምላሽ አይነቶች 13
2.3.1.1 ገምጋሚ 13
2.3.1.2 ትዕዛዛዊ 14
2.3.1.3 አጠናካሪ 14
2.3.1.4 አስተካካይ 15
2.3.2 የምጋቤምላሽ አሰጣጥ ዘዴዎች 16
2.3.2.1 ምልክቶችን በመጠቀምና ማስረጃዎችን በማቅረብ ስህተቶችን ማመልከት 16
2.3.2.2 የሚታዩ ስህተቶችን በሙሉ በተገቢው ሁኔታ ማረም 17

2.3.2.3 ከስህተቶች ጎልተው የሚስተዋሉትን መርጦ ወይም ለይቶ እርማት መስጠት............18
2.3.3 የምጋቤምላሽ መስጫ መንገዶች............19
2.3.3.1 የቃላዊ ምጋቤምላሽ ምንነት............20
2.3.3.2 የጽሁፋዊ ምጋቤምላሽ ምንነትና ትኩረት............21
2.3.4 የምጋቤምላሽ ባህርያት............22
2.3.4.1 አዎንታዊ (Positive) ባህሪ............22
2.3.4.2 አሉታዊ (Negative) ባህሪ............24
2.3.4.3 ውጤታማ ባህሪ............25
2.3.5 ምጋቤምላሽ ሊሰጡ የሚችሉ አካላት............25
2.3.5.1 የግል (የራስ) ምጋቤምላሽ............26
2.3.5.2 የብጤ (የጓደኛ) ምጋቤምላሽ............26
2.3.5.3 የመምህር ምጋቤምላሽ............27
2.4 የቀደምት ተዛማጅ ጥናቶች............29
ምዕራፍ ሦስት............31
3. የጥናቱ ንድፍ እና የአጠናን ዘዴ............31
3.1 የጥናቱ ንድፍ............31
3.2 የአጠናን ዘዴ............31
3.1 የናሙና አመራረጥ............31
3.1.1 የጥናቱ አካላይ............31
3.1.2 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ............31
3.1.3 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ............32
3.1.5 የመምህራን ናሙና አመራረጥ............33
3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች............34
3.2.1 ሰነድ ፍተሻ (Document analysis)............34
3.2.2 የጽሁፍ መጠይቅ (Questionnaire)............35
3.2.3 ቃለመጠይቅ (Interview)............35
3.3 የመረጃ አተናተን (Methods of Data analysis)............35
ምዕራፍ አራት............36
የመረጃ ትንተና............36
4.1 ሰነዶችን በመፈተሽ የተገኙ መረጃዎች ትንተና............36
4.2 ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና............37

4.3 ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........ 52
ምዕራፍ አምስት ........ 59
ማጠቃለያና አስተያየት ........ 59
5.1 ማጠቃለያ ........ 59
5.2 አስተያየት ........ 60
ዋቢ መጻህፍት ........ 61
አባሪዎች ........ 66
አባሪ ሀ፡- የተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ ........ 67
አባሪ ለ፡- ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቀረበ ቃለ መጠይቅ ........ 72

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

የቋንቋ ትምህርት አራቱ መሰረታዊ ክሂሎች ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ ተማሪዎች የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክሂላቸው እንዲጎለብት፣ ከንግግር ያለፈውን የቋንቋን ሰዋስዋዊ ህግጋት እንዲያውቁና እና የስነ-ጽሁፍ ግንዛቤ እንዲኖራቸው የሚያስችል ዓላማ ያለው ነው፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች ለእያንዳንዱ ክሂሎች ትኩረት ሰጥተው እንዲማሩ የሚያስችል ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ የሚያዳምጡትን እንዲገነዘቡ፣ ልዩ ልዩ ጽሁፎችን በማንበብ እውቀት እንዲቀስሙ፣ ያነበቡት ላይ በመነሳት እንዲጽፉ እና ክፍል ውስጥም ሆነ በአካባቢያቸው በነፃነት ሀሳባቸውን መግለፅ እንዲችሉ የቋንቋ ትምህርቱ ትልቁን ሚና ተጨዋች ነው፡፡ ነገር ግን ቋንቋውን ከማወቅ እና ካላቸው የቋንቋ ብቃት አንፃር ስናያቸው የበቁ ናቸው ማለት አንችልም፡፡ በሚያነቡበትና በሚጽፉበት ጊዜ በርካታ ስህተቶችን ሲሰሩ ስለሚስተዋሉ ነው፡፡

የቋንቋ ትምህርቱም በማንበብና በመፃፍ ጊዜ የሚታዩትን እንቅፋቶች ተማሪዎች ደጋግመው እንዳይሰሯቸው የማድረግ አስተዋፅኦ አለው፡፡ ቀዳሚውን ስፍራ የሚይዙት ባለድርሻዎችም መምህራን ናቸው፡፡ መምህራን ዘወትር ሳይሰለቹ በሚያነቡበት ወቅት እና በሚፅፉበት ጊዜ ማስተካከያ ወይም እርማት በመስጠት ችግሮችን ለማቃለል እና ለመፍታት መጣር ይኖርባቸዋል፡፡ በርካታ ገለፃዎች የሚኖሩት ቢሆንም በተማሪዎች ንባብ እና ጽሁፍ ላይ በመምህራን የሚደረገው ማስተካከያ፣ የሚሰጠው እርማት እና ማሻሻያ ምጋቤምላሽ (feedback) በመባል የሚታወቅ ነው፡፡

የማንበብን ምንነት በተመለከተ Nuttal (1982) ሲያስረዱ፣ "ማንበብ ዓላማ ያለው የሚፈልገውን መረጃ ከጽሁፍ ላይ ማግኘት ነው፡፡" በማለት ሲበይኑት ንባብ ማለት አንድ የተጻፈን ነገር ወይም ምንባብን አንብቦ ፍሬሃሳቡን የመረዳት ሁኔታ ነው በማለት Wiliames (1984) ይገልፁታል፡፡ ይህ ማለትም ተፈላጊውን መረጃ ከጽሁፍ ማግኘት ወይም ፍሬሃሳቡን መረዳት ማለት እንደሆነ የሚጠቁም ነው፡፡ ተማሪዎች በተሳካ ሁኔታ ማንበብ እንዲችሉ እና የጽህፈት ክሂላቸው እንዲዳብር ያስችላል፡፡ ስለሆነም በንባብ ሂደት ወቅት መደነቃቀፍ እንዳይኖርና በትክክል አንብቦ ያለመረዳት ሁኔታ ተማሪዎች እንዳይገጥማቸው ያደርጋል፡፡

በተጨማሪም "ማንበብ ማለት ከአንድ አሀድ (text) ውስጥ ተፈላጊውን መረጃ በብቃት ማሰባሰብ መቻል ማለት ነው፡፡ በዚህ ዓይነት ሂደት ውስጥ አንባቢው የማይፈልገውን መረጃ በመተው

የሚፈለገውን ይዘት ብቻ ሊመርጥ ይችላል፡፡ በተጨማሪም የአሀዱን መሰረታዊ ሀሳብ ከመረዳት ባሻገር ዝርዝሩን በብቃት የሚገነዘብበትን ሁኔታ የሚያጠቃልል ነው” Grellet (1981) ብለዋል፡፡ ከሀሳቦች ማስተዋል እንደሚቻለው ማንበብ ቃላትን በቅልጥፍና እና የአደራደር ስርዓታቸውን ጠብቆ ከማንበብ በአሻገር ተፈላጊ የሆነን መረጃ አውጥቶ ለመጠቀም የሚያስችል እንደሆነ ነው፡፡ በመሆኑም የንባብ ምጋቤምላሽ አስፈላጊ እንደሆነና መምህራን በተማሪዎች ንባብ ላይ የተለያዩ ምጋቤምላሾችን ማድረግ እንዳለባቸው ይታመናል፡፡

በጽህፈት ጊዜም “ጽሁፋዊ ምጋቤምላሽ ከጽሁፍ ክሂል ተለይቶ የማይታይ የጽህፈት ክሂል እንዲጎለብት የሚያስችል፣ በተለያዩ የጽህፈት ተግባራት ወቅት ሊተገበር የሚችል፣ የጸሐፊውን ስህተት ለመቀነስ የሚያግዝ የማስተማሪያ ስነዘዴ ነው” Zamel (1985)፡፡ በተጨማሪም “ምጋቤምላሽ ተማሪዎች በጽሁፍ አማካኝነት የሚሰጣቸውን የቋንቋ ትምህርት ይዘቶችና ግቦች መምህራን ካነበቡ በኋላ በጽሑፍ የሰፈረው ሀሳብ በትክክል መጻፍ አለመፃፉን በመረጃ አስደግፈው የሚሰጡት ምጋቤምላሽ” እነደሚባል Brookharte (2008) እና Raimes (1983) ይገልፃሉ፡፡

የቀረበው ሃሳብ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ የማንበብና የመጻፍ ክሂልየጠበቀ ቁርኝት ያላቸው ናቸው፡፡ ማንበብ ካለ መጻፍም ይኖራል፡፡ ማንበብና መጻፍ የማይለያዩ የቋንቋ ክሂሎች ናቸው፡፡ ከንባብ ብዙ ነገር ስለሚገኝና የተፃፈን ነገር ስለምናነብ ነው፡፡ ከዚህ በመነሳትም እነዚህ ሁለቱ ክሂሎች ላይ መምህራን የሚሰጧቸውን ቃላዊና ጽሁፋዊ ምጋቤምላሾች አቀራረብ መተንተን ይሆናል፡፡

ምጋቤምላሽ ተማሪዎች በጻፏቸው ጽሁፎች ላይ ያሉ ስህተቶች እነዚህ ናቸው፤ በዚህ መልክ መስተካከል አለባቸው፤ ስህተቱ በዚህ ምክንያት ሊፈጠር ችሏል በማለት እና ጥሩ ሙከራዎችን በማሳየት ለቀጣይ ጥሩ የጽሁፍ ስራ የሚጋብዝ አሰራር ነው በማለት Ur (1996) ይገልጻሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም “ጽሁፋዊ ምጋቤምላሽ የጽህፈት ችሎታን ለማሳደግ የሚያግዝ የጽህፈት ትምህርት የተባበረ ክፍል ነው” በማለት Pincas (1982) ገልፀዋል፡፡

ምጋቤምላሽ በመማር ማስተማር ሂደት የማይለይ በመሆኑ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማንበብና መጻፍ ክሂሎችን ሲያስተምሩ በንባብ ጊዜና በጽህፈት ልምምድ ወቅት ማስተካከያ የሚያደርጉበት መንገድ ምጋቤምላሽ የምንለው ነው፡፡ ምጋቤምላሹ የክፍል ውስጥ ተግባር ብቻ ላይሆን ይችላል፡፡ ምክንያቱም የሚሰጠው ምጋቤምላሽ ቃላዊ እና ጽሁፋዊ ሊሆን ስለሚችል ነው፡፡ ቃላዊ ከሆነ አንደበትንና መተያየትን ይጠይቃል፡፡ ጽሑፋዊ ከሆነ ደግሞ በጽሁፍ መገለፅ እንዳለበት ያሳያል፡፡ ዋናው ግን ከሀሳቡ አደረጃጀት፣ አሰካክ፣ የሀሳብፍሰት፣ የሰዋሰው ህግ

መከተሉን፣ የቃላት አመራረጥ፣ አጠቃቀም እና መሰል ጉዳዮችን መሰረት ያደረገ ምጋቤምላሽ መሰጠት ይኖርበታል፡፡ ምጋቤምላሽ በተለይም በንባብ እና ጽህፈት ትምህርት ውስጥ ዘወትራዊ ተግባር እና ክንውን ነው፡፡ ያለ ምጋቤምላሽ ትምህርቱን ውጤታማ ማድረግ አይቻልም፡፡

ተማሪዎች ለጻፉት ጽሑፍ ጠቃሚና ገንቢ ምጋቤምላሽ መስጠት፣ የጥረታቸውን ደረጃ መለየት፣ ማድነቅና ማበረታታት፣ ጽሑፋቸውን ማረምና አስተያየት መስጠት የሚሉትን መርሆች መምህራን መከተል እንዳለባቸው Attkins (1996) ይገልፃሉ፡፡ በተጨማሪም የተማሪዎች የጽህፈት ደረጃ የተሻለ እንዲሆን ከተፈለገ ጽሑፋዊ ምጋቤምላሽ በአግባቡ መሰጠት አለበት፡፡ ተማሪዎችም ትኩረት እንዲሰጡት በቀላሉ ሊገባቸውና ሊረዱት በሚችሉት ደረጃ መቅረብ እንዳለበት Brookhart (2008) ይገልፃሉ፡፡ ጽንሰሀሳቡ የሚጠቁመውም መምህራን የሚሰጡት ቃላዊና ጽሁፋዊ ምጋቤምላሽ የሚያበረታታ ማለትም የተማሪዎችን ጥንካሬዎችና ድክመቶች ሊያመላክት የሚችል መሆኑን ነው፡፡

በተጨማሪም "ምጋቤምላሽ ውጤታማነቱ የጎላ እንዲሆን ተማሪዎች እየተማሩ ባሉበት ሂደት በተገቢው ቦታና ጊዜ ሊሰጥ መቻል እንዳለበት" Byren (1998) ያሳስባሉ፡፡ ስለሆነም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተማሪዎችን በሚያስነብቧቸው ምንባቦችና ተማሪዎች በሚጽፏቸው ልዩ ልዩ ጽሁፎች ላይ የማይቋረጥ ዘወትራዊ ምጋቤምላሽ እየተከታተሉ መስጠት ይገባል፡፡ ምክንያቱም በዚህ ጥናት የተካከቱት የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ግማሽ ክፍሉን ይይዛሉ፡፡ ስለሆነም ይህ ጥናት ትኩረቱን ያደረገው በጉራጌ ዞን ኬላ ወረዳ ሁለተኛ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን ብቻ ሲሆን የተማሪዎች አማርኛ ትምህርት የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች ላይ የመምህራን ቃላዊና ጽሁፋዊ ምጋቤምላሽ ተተንትኗል፡፡

## 1.2 ሰበበ ጥናት

የአንብቦ የመረዳት እና የመጻፍ ክሂሎች እንደ መሰረታዊ ፍላጎት ተደርገው የሚወሰዱ መሆን አለባቸው:: ምክንያቱም አንብቦ መረዳት ካልተቻለ እና የሚፈለገውን ሁሉ በእጅ ጽሁፍ መግለፅ ካልተቻለ አሁን ካለው ዘመን አንፃር ከባድ እንደሚሆን መረዳት አያዳግትም፡፡ በDechant and Smith (1987) ገለፃ፣ ተማሪዎች በመጀመሪያዎቹ ክፍሎች አንብቦ የመረዳት ክሂላቸው በደንብ ከዳበረ በኋለኞቹ አመታት (ክፍሎች) በጣም ስኬታማ ይሆናሉ በማለት ሲገልፁ እንደ Zamel (1983) አገላለፅ ደግሞ የጽህፈት ክሂል በአብዛኛው መምህሩ ተማሪዎች ምን እየተማሩ እንደሆነ የሚያረጋግጥበት ዘዴ ነው በማለት አስቀምጠዋል፡፡

ይህ የሚያሳየውም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማንበብን እና የመጻፍን ክሂል ማሻሻል እንደ ዋና ዓላማ አድርገው መስራት እንዳለባቸው ነው፡፡

- ✓ በመሆኑም ለጥናቱ የተመረጡትን ሁለቱን መሰረታዊ ክሂሎች በሚያስተምሩበት ወቅት የቋንቋ መምህራን የሚሰጧቸው ቃላዊ እና ጽሁፋዊ ምጋቤምላሾችን ለመተንተን ቀስቃሽ ፍላጎት ስላለ፣
- ✓ መምህራን ትክክለኛውን የምጋቤምላሽ አሰጣጥ መንገድ ተከትለው መስጠት አለመስጠታቸውን ለማወቅ፣
- ✓ ምጋቤምላሽ ሲሰጡ እንቅፋት የሚሆኗቸውን ችግሮች ለመለየትና በጥናቱ መፍትሔ መስጠት ስለተፈለገ በርዕሰጉዳዩ ላይ ለማጥናት መነሳሳት ተችሏል፡፡

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በምስራቅ ጉራጌ ዞን ኬላ ወረዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን ትኩረት በማድረግ በተማሪዎች የአማርኛ ትምህርት የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች ላይ የመምህራንን ቃላዊና ጽሁፋዊ ምጋቤምላሽ አቀራረብ መተንተን ሲሆን የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡

- ❖ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎች የአንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂሎች ላይ ቃላዊና ጽሁፋዊ የምጋቤምላሽ መስጫ መንገዶችን ተከትለው መስጠት አለመስጠታቸውን መፈተሽ፣
- ❖ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎች የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች ላይ ምን ዓይነት ቃላዊ እና ጽሁፋዊ ምጋቤምላሽ እንደሚሰጡ መፈተሽ፣
- ❖ መምህራን ምጋቤምላሻቸውን በምን መልኩ እንደሚያቀርቡት መፈተሽ፣
- ❖ የተማሪዎቻቸው የንባብና የመጻፍ ክሂሎች ላይ ቃላዊ እና ጽሁፋዊ ምጋቤምላሾችን ሲሰጡ ትኩረታቸው የሚያደርጉትን ማወቅ እና ትክክለኛነታቸውን ማረጋገጥ፣

## 1.4 የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች

ይህ ጥናት ዓላማውን ያሳካ፣ የሚፈለገውን ግብ የመታ እንዲሆን የሚያደርጉት መሪ ጥያቄዎች የግድ አስፈላጊ በመሆናቸው እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- ✓ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎቻቸው የንባብና የመፃፍ ክሂሎች ላይ ቃላዊና ፅሁፋዊ ምጋቤምላሾችን በትክክል ይሰጣሉ ወይስ አይሰጡም?
- ✓ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎች የማንበብና የመፃፍ ክሂሎች ላይ ምን ዓይነት ቃላዊ እና ጽሁፋዊ ምጋቤምላሽ ይሰጣሉ?

- ✓ የተማሪዎቻቸው የንባብና የመፃፍ ክሂሎች ላይ ቃላዊ እና ፅሁፋዊ ምጋቤምላሾችን ሲሰጡ ትኩረታቸው የሚያደርጉት ምንድን ነው?
- ✓ መምህራን ምጋቤምላሽ ሲሰጡ ተጽዕኖ የሚያሳድሩባቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት ለኬላና ጎጌቲ አጠቃላይ ሁለተኛ ትምህርት ቤቶች፣ ለጥናቱ አካባይ እና ይህንን ጥናት በመረጃነት ለሚጠቀሙት ሁሉ በርካታ መሰረታዊ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል፡፡

- ✓ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን ብቻ በሚያስተምሩበትና ምጋቤምላሽ በሚሰጡበት ጊዜ የምጋቤምላሽ አቀራረባቸው የታሰበበት እንዲሆን የማድረግ፣
- ✓ የምጋቤምላሽ ዓይነቶችን አዘውትረው በመጠቀም ምጋቤምላሽ እንዲሰጡ ለማስቻልና ትኩረት ማድረግ የሚኖርባቸው ላይ ትኩረት ሰጥተው ተማሪዎቻቸውን እርማት እንዲሰጡ፣
- ✓ ሁለቱን ክሂሎች በማስተማር ላይ የሚገጥሟቸውን አሉታዊ ተፅዕኖዎች በቀላሉ መቋቋም እንዲችሉ፣
- ✓ መምህራን ምጋቤምላሽ በሚሰጡበት ወቅት ተዘውትረው የሚሰተዋሉትን ደካማ ጎኖች መቅረፍ እንዲችሉ እንዲሁም ደግሞ ጥንካሬዎቻቸው ላይ እንዲበረቱ አቅጣጫ ጠቋሚ ነው፡፡
- ✓ በተጨማሪም ወደፊት በዚህ ጥናት ርዕስ ዙሪያ ተዛማጅ ወይም ተጨማሪ ጥናት ማድረግ ለሚፈልጉ የቋንቋ አጥኝዎች እንደግብዓት በመሆን ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

የጥናቱን ከቦታ እና ትምህርት ቤት አንጻር በመወሰን ማቅረብ ተችሏል፡፡ ስለሆነም ከቦታና ትምርት ቤት አንጻር ሲታይ የዚህ ጥናት ትኩረት በጉራጌ ዞን ኬላ ወረዳ ስር የሚገኙትን ሁለት ሁለተኛ ደረጃ (ጎጊቲና ኬላ) ትምህርት ቤቶች በማተኮር ሲሆን የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ብቻ ነው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያትም በአካባቢው የስራ ቆይታ በመደረጉ አካባቢውን ጠንቅቆ ማወቅ ስለተቻለና አካባቢው ላይ በርካታ ጥናቶች ተደርገው ማግኘት ስላልተቻለ ለተመረጡት ትምህርት ቤቶች የሚረዳ መሆኑ የግል እምነት በመያዝ ጥናቱ ተሰናድቷል፡፡

## 1.7 የጥናቱ ውስንነት

ከይዘት አኳያ ሲታይ ደግሞ ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው የተማሪዎች አማርኛ ትምህርት የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች ላይ መምህራን የሚሰጧቸው ቃላዊ እና ጽሁፋዊ ምጋቤምላሾችን ብቻ ተንትኖ ያቀረበ ነው፡፡ በመሆኑም ጥናቱን ለማድረግ ሰነድ ፍተሻ፣ ቃለመጠይቅና የጽሁፍ መጠይቅ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ በመረጃ ምንጮች የተገኙት መረጃዎች በአግባቡ የተተነተኑ ሲሆን ከጠቀስኳቸው ውጪ ያሉትን የቋንቋ ክሂሎች አይመለከትም፡፡

## 1.8 የቁልፍ ቃላት ትርጉም ወይም ፍች

**የማንበብ ክሂል ችሎታ** (Reading Skill Performance)፡- መምህራን ክፍል ውስጥ በሚያስተምሩበት ወቅት ወይም በሚያስነብቡበት ጊዜ የንባብ ብቃታቸው የሚታይበት፣ የሚለካበት ክሂል ነው፡፡ የማንበብ ክሂል ትምህርት አንብቦ የመረዳት ችሎታን የሚያስገኝ ነው፡፡

**የመጻፍ ክሂል ችሎታ፡-** የሻረግ (2010) በጥናታቸው እንደገለጹት "የመጻፍ ክሂል ችሎታ (Writing Skill Performance) አንድን ጽሁፍ ከይዘት/ ከሀሳብ አፍልቆት፣ ከሀሳብ አደረጃጀት፣ ከቋንቋ አጠቃቀም፣ ከቃላት ምርጫና ከስርዓተ ጽህፈት አንጻር ተገቢነቱ የሚመዘንበትና የችልታ ደረጃ የሚሰጥበት ነው፡፡"

**የምጋቤምላሽ ምንነት (Definition of feedback)፡-** የሻረግ (2010)፣ (Ur, 1996)ን በመጥቀስ በመመረቂያ ጥናታቸው እንደገለጹት "ምዘና (Assessment) እና እርማት (Correction) የተባለ ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ያሉት ሲሆን ምዘና ተማሪው ምን ያህል ጥሩ እንደሰራና እንዳልሰራ መጨረሻ ላይ ውሳኔ የምናሳርፍበት ሲሆን እርማት ደግሞ የተማሪዎችን ክህሎት (Performance) ለማሳደግ የተወሰነ መረጃ የምናስተላልፍበት መንገድ ነው፤ ስለሆነም ምጋቤምላሽ መምህራን የአማርኛ ቋንቋ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች ላይ የሚሰጧቸውን ቃላዊና ጽሁፋዊ ግብረመልሶች፣ እርማቶች፣ ማስተካከያዎች፣ አዎንታዊና አሉታዊ ትችቶች ሁሉ ምጋቤምላሽ ማለት ይቻላል፡፡"

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 የማንበብ ክሂል ምንነት

ማንበብ ውስብስብ የሆነ ሂደት ነው፡፡ ውስብስብ የሚያደርገው ደግሞ ረቂቅ በሆነ አዕምሯዊ ሂደት የሚመራ መሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም የማንበብን ምንነት በተለያዩ ዘመናት የተለያዩ ምሁራን በተለያየ መንገድና አተያይ ሲበይኑት እናስተውላለን፡፡

ማንበብ አዕምሮን ያበለፅጋል፡፡ በትምህርት ስርዓት ውስጥ ይሁነኝ ተብሎ የሚያልፍ አንድ ተማሪ (ግለሰብ) በአዕምሮው በተሟላ አግባብ ይጠቀም ዘንድ የማንበብ ክሂል እንዲኖረው መሰረታዊ ከሆነው የፊደል ልየታ አንስቶ ያሉትን የማንበብ ደረጃዎች በአግባቡ እንዲማርና እንዲለማመድ ምቹ ሁኔታ መፍጠርና ማበረታታት ያስፈልጋል በማለት ደረጀ (2013) ገልፀውታል፡፡

ከቀረበው ሃሳብ መረዳት የሚቻለው የማንበብ ክሂል በትምህርት ሲዳብር ለአዕምሮ እድገት መሰረት መሆኑን ነው፡፡

“ማንበብ ዓላማ ያለው የሚፈልገውን መረጃ ከጽሁፍ ላይ ማግኘት ነው” Nuttal (1982)፡፡ በማለት ሲበይኑት Wiliames (1984) ደግሞ ማንበብ ማለት አንድ የተጻፈን ነገር ወይም ምንባብን አንብቦ ፍሬሃሳቡን የመረዳት ሁኔታ ነው በማለት ይገልፁታል፡፡ ይህ ማለትም በአጭሩ ተፈላጊውን መረጃ ከጽሁፍ ማግኘት ወይም ፍሬሃሳቡን መረዳት መቻል መሆኑን የሚጠቁም ነው፡፡ ማንበብ አንባቢንና ጸሐፊውን የሚያገናኝ መድረክ ነው፡፡ ይህ ማለት አንባቢ በማንበብ ሂደት የሚገነዘበው ቁምነገር በደራሲው የቀረበ ሀሣብ መሆኑን ተገንዝቦ ጥቅምና ጉዳቱን በማመዘን ፀሀፊውን ሊያመሰግን ወይም ሊያወግዝ ይችላል ማለት ነው፡፡ አንባቢና ፀሀፊ የሚገናኙበትና የሚከራከሩት ሀሣብ ግን የጸሀፊው መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ማንበብ በዓይንና በአእምሮ የቅንጅት ሂደት የሚከናወን መንገዱን ይገልፃል፡፡ ዓይን መልዕክት ሲቀበል፣ አዕምሮም መልዕክቱን የመመዘንና የማሰላሰል ስራን ያከናውናል፡፡ እንደ ማዳመጥ ሁሉ ከውጪው ዓለም ወደ ውስጣችን የተለያየ ልምድ፣ እውቀትና ብልሀት የምንገበይበትና የምናሰርጽበት ክሂል ነው፡፡ ይህንን በተመለከተም Grellet (1981) እንደሚከተለው ያብራራሉ፡፡

ማንበብ ማለት ከአንድ አሀድ ውስጥ ተፈላጊውን መረጃ በብቃት ማሰባሰብ መቻል ማለት ነው፡፡በዚህ ዓይነት ሂደት ውስጥ አንባቢው የማይፈልገውን መረጃ በመተው የሚፈለገውን ይዘት ብቻ ሊመርጥ ይችላል፡፡ በተጨማሪም የአሀዱን መሰረታዊ ሀሳብ ከመረዳት ባሻገር ዝርዝሩን በብቃት የሚገነዘብበትን ሁኔታ የሚያጠቃልል ነው፡፡

ከዚህ ሀሳብ መገንዘብ የሚቻለው አንብቦ መረዳት ማለት ተፈላጊ የሆነውን መረጃ ለመምረጥ ተገቢ ትኩረት ማሳረፍ መቻል እንደሚገባነው፡፡ በምን መልኩ ማንበብ ተገቢ እንደሆነ ማወቅ ከተቻለ የሚነበበውን ነገር በቀላሉ ለመረዳት የማያዳግት መሆኑን ነው፡፡

በተጨማሪም Anderson (2000) የማንበብን ምንነትና ሂደት በተመለከተ ሲገልፁ፣ የማንበብ ሂደት በማንበብ ሂደትና በሚመጣው ውጤት ያለውን ርቀት ነው፡፡ ይህም ርቀት በአንባቢውና በጽሁፍ መስተጋብር የሚሞላ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ በተጨማሪም በማንበብ ሂደት አንባቢው የተፃፈውን ከማንበብ፣ ምልክቶችን ከመረዳት ባለፈ የተጻፈውን ሀሳብ ምንነት፣ ከሌሎች ፅሑፎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት፣ በማንበቡ የሚያገኘውን ፋይዳ፣ ከቀደመ እውቀቱ ጋር በማገናዘብና ቀጣዩንም እየገመተ ያነባል፡፡ አያይዞም የጽሑፉን አዝናኝነት፣ አሰልችነት፣ ጠቃሚነት እየለየ እንደሚሄድ ይናገራሉ፡፡

ማንበብ ከትንሹ ፊደልን ከመለየት ጀምሮ እየሰፋ ወደሚሄደው ፊደላትን የመገጣጠምና ፊደላት ተገጣጥመው የሚፈጥሩት ቅንጅት ሊያስተላልፉት የሚችሉትን ሀሳብ ወይም መልዕክት መረዳትን ጭምር የሚይዝ ሰፊና ውስብስብ አዕምሮሯዊ ክንውን ነው፡፡ በመሆኑ ምንባብ በየደረጃው እያደገ የሚሄድ ክሂል ነው፡፡

## 2.1.1 የማንበብ ክሂል ትምህርት አስፈላጊነት

ማንበብ የራሱ የሆነ ጥቅምና ዓላማ አለው፡፡ ስለዚህ ማንበብ በጽሁፍ የቀረበውን መልእክት ለመረዳት አንባቢ በግሉ የሚያከናውነው ተግባር ነው፡፡ በመሆኑም የአነባበቡ ሁኔታ እንደሚፈለገው የመረጃ አይነትና ሁኔታ ይለያያል፡፡ ማንበብ የተለያዩ አላማዎች ሲኖሩት ጥቂቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡ ከነዚህም ውስጥ፡-

- ከምንባቡ አጠቃላይ መረጃ ለማግኘት፣
- የተወሰኑ መረጃዎችን ለማግኘት፣ ደስታና እርካታን ለማግኘት ዋና መሣሪያ ነው፡፡
- በተጨማሪም በትምህርት ቤት የተለያዩ ትምህርቶችን ለማስተማር ከፍተኛ እገዛ ይደረጋል፡፡

ይህን በተመለከተ "ማንበብ በትምህርት ውጤታማ ለመሆን ይረዳል፤ ማንበብ የተማሪን ፍላጎት ያነሳሳል፤ ማንበብ የመማርን ዘለቄታዊነት ይተክላል፤ ማንበብ አስተሳሰብንና አሰራርን ያሳምራል፤ የማንበብ ክሂል በራሱ ልዩ መታወቂያ ነው" በማለት ደረጀ (2013) ገልፀዋል።

ከሃሳቡ መረዳት እንደሚቻለው ማንበብ እይታን እንደሚያስተካክል፣ ስኬታማ ለመሆን እንደሚረዳ፣ በጥንካሬ ለማወቅ (ለመማር) የሚያስችል ልዩ ብቃት እንደሆነ መረዳት ተችሏል። በተጨማሪም ደረጀ (2013) ፀሐፉን ጠቅሰው "ማንበብና መፃፍ ታላቅ ቁም ነገር፣ በህይወቴ ጎሎ እቸገር ነበር" በሚል ስንኝ ገልፀውታል።

ከቀረበው ስንኝ መረዳት የሚቻለው የማንበብ ክሂል በማንኛውም ሰው ህይወት ውስጥ የግድ መኖር ያለበት እና ህይወትን የሚሞላ መሆኑን ነው። የማንበብ ክሂል አስፈላጊነት የተገለፀበት ነው።

በተጨማሪም "ማንበብ በተለይ በአሁኑ በሰለጠነው ዘመን አስፈላጊ ከሚባሉት ሙያዎች ውስጥ የሚደመር ነው። ማንበብ እውቀት የማግኛ መንገድ ብቻ ሳይሆን መዝናኛ ምሆኗል" ተስፋዬ (1981) ይላሉ ። በተጨማሪም የንባብን አስፈላጊነት እንደሚከተለው ገልፀዋል።

- ከአንድ ጽሁፍ አጠቃላይ የሆነ ሀሳብ ለማግኘት፣
- አንድን ጽሁፍ በጥልቀት አንብቦ በተወሰነ ርዕሰጉዳይ ላይ ሰፊ ሀሳብን ለመገንዘብ፣
- ዕውቀትን ለማዳበር እና ለተዝናኖት መሆኑን ይገልፃል።

በአጠቃላይ ስለንባብ የምንረዳው በህይወታችን ውስጥ ከፍተኛ ቦታ እንዳለውና በትምህርትቤት ቆይታ ወቅት ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሳይሆን አንድ ሰው ህይወቱን ሙሉ የሚገልፅበት ክሂል መሆኑን ጭምር የሚያሳይ ነው።

## 2.1.2 የማንበብ ክሂል ትምህርት በክፍል ውስጥ አቀራረብ

የማንበብ ትምህርት በሦስት ደረጃ ላይ ከፋፍሎ ማቅረብ ተማሪው ለማንበብ ያለው ፍላጎት እንደሚጨምርና ለተለያዩ ልምምዶች ራሱን እንዲያደራጅ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። በድሉ (1996) የንባብ ተግባራትን በሦስት ክፍል ከፍለው አስቀምጠዋቸዋል። እነሱም፡- ቅድመ ንባብ ተግባራት (pre- reading)፣ የንባብ ጊዜ ተግባራት (while reading) እና የድህረ ንባብ ተግባራት(post reading) ናቸው። እነዚህን ደረጃዎች ተከትለው መምህራን የንባብ ክፍል ውስጥ ትምህርቱን ያቀርቡታል።

## 2.2 የመጻፍ ክሂል ምንነት

የመጻፍ ክሂል ከአራቱ አበይት የቋንቋ ክሂሎች አንዱ ሲሆን በቀላሉ የማይጨበጥ በጣም ውስብስብና ረቂቅ የሆነ ክሂል ነው። የጽህፈት ክሂል ከሌሎች ክሂሎች በተለየ ውስብስብና አስቸጋሪ ሊሆን የቻለው አንዱ ምክንያት በትምህርት ልምድ ብቻ የሚገኝ በመሆኑ ነው።ጠቅለል ባለ አገላለፅ የጽህፈት ክሂል በአዕምሮ ሃሳብን የማደራጀት ችሎታንና ይህንንም አስቀድሞ የተደራጀውን ሃሳብ በወረቀት ላይ የማስፈር ጥምር ችሎታ የሚይዝ ነው ማለት ይቻላል።

የመጻፍ ክሂል በትምህርት የሚገኝ ክሂል ነው። ይህ ክሂል በተለያየ ጊዜና ቦታ በማንበብና በማዳመጥ የተሰበሰበውን መረጃ በቃላት አማካኝነት ሃሳብ የሚገለጽበት የማፍለቅ ክሂል ነው። ደሳለኝ (1994) ሲያስረዱ የመጻፍ ክሂል ይዘት በአጭሩ ከየእጅ ጽህፈት ሆህያትን አጣጣል (Hand writing) ጀምሮ እስከ ሃሳብን በተገቢ መንገድ ወረቀት ላይ ማስፈር ያለውን ሂደት የሚያጠቃልል ሰፊ የቋንቋ ክሂል ነው በማለት ይገልፁታል። ሃሳብን በወረቀት ማስፈር ሲባል የውስጥ ስሜት ያፈለቃቸው የተለያዩ ቁምነገሮች ወይም መልእክቶች አንባቢ ወይም ተቀባይ ሊገነዘበው በሚችለው አገባብ ምርጥ ቃላትን በመጠቀም ስርዓት ያላቸው የአረፍተነገሮች ቅንብር፣ አንቀፆችንና ከዚያ በላይ ይዘቶችን መመስረት ማለት ነው።

የመጻፍ ክሂል በማዳመጥና  በማንበብ የካበተ ዕውቀት መልሶ ለሌላ ወገን ለማስተላለፍ የሚያስችል አንዱ ክሂል ነው። አንድ ሃሳብ ወይም አስፈላጊ መልዕክት ወይም የምርምር ውጤት ሊሆኑ ይችላሉ መዝግቦ ለሌላ ሰው ለማስነበብ ወይም ለመጪው ዘመን ታሪክ ለማሰቀመጥ ከፍተኛ ሚና አለው። የጽህፈት አገልገሎት የሚመዘነው ተማሪዎች መልስን በትክከል ወረቀት ላይ ማስቀመጥ ሲችሉ፣ የስራ ማስታወቂያ (ማመልከቻ)፣ ለወዳጅ ዘመድ ደብዳቤ ወዘተርፈ መጻፍ ሊችሉ  የሚችሉት በትክክል መፃፍ ሲችሉ ነው።

መጻፍ የንግግር ወኪል ነው። በቦታና በጊዜ በተለያዩ ሰዎች መካከል በምልክቶች አማካይነት ግንኙነት ለመፈጠርና ራስን ለመግለፅ እንዲሁም መረጃ መለዋወጥ በቋንቋ መጠቀም ማለት ነው። ጽሕፈት ሀሳብን ቋሚና ዕይታዊ በሆነ ትዕምርት ቀርፆ ለማቆየት የሚያስችል፣ በቦታና በጊዜ የማይወሰን ህያው ሆኖ የሚቆይ ምልክት ነው። ስለሆነም መጻፍ ማለት ሃሳብን ወደ ምልክት የመለወጥ ሂደት ነው ሊባል ይችላል። ጽሕፈትን አስመልክተው የተለያዩ ሙሁራንየተለያየ ብያኔ ይሰጣሉ።

መጻፍ የንግግር ድምፆችን የሚወክሉ ትዕምርቶችን ተጠቅሞ መልእክትን በወረቀት ላይ ማስፈር ነው ሊባል ይችላል። ንግግር ድምፅ ከማመንጨት በላይ እንደሆነ ሁሉ፣ ጽህፈትም ትእምርቶችን በመጠቀም ቃላትን፣ ዓረፍተ-ነገሮችን፣ አንቀፆችን፣ ድርሰቶችን በቋንቋው ስርዓት መሰረትነት አቀናብሮ የሚያቀርብ ነው በማለት Byrne (1991) ገልፀዋል።

ከአገላለፃቸው መረዳት የሚቻለው ጽህፈት ሀሳብን በትክክል ለማሰተላለፍ ከድምፅ ጀምሮ ያሉትን በቋንቋው ስርዓት መሰረት ቅደም ተከተላቸው ጠብቀውና ተቀነባብረው የሚቀርቡበት መሆኑ ነው።

መጻፍ መጠነ ሰፊ የሆነ የሃሳብ አሰሳ የሚካሄድበት ከመሰረታዊ ክሂሎች አንዱ ነው።ይህ ሃሳብ በማጠናከር በድሉ (1996) ደግሞ ጽህፈት ልቅ የሆነ የመረጃ መሰብሰብ የሚታይበት ሂደት መሆኑ ይገልፁታል። ይህ የሚያመለክተው ስሜታችን በወረቀት ከማስፈራችን በፊት ከተለያዩ አቅጣጫዎች ሀሳብ ማከማቸትና መለየት የሚጠይቅ ክሂል ነው።

መጻፍ ከንግግር የሚለየው ቋንቋ በወከላቸው ትዕምርቶች በመታገዝ ያለማቋረጥ ተከታታይ ልምዶችን የሚጠይቅ ክሂል በመሆኑ ነው።ይህ ክሂል በማስመልከትዳንኤል (1998) ሲያብራሩ አበዛኛው ስንናገር ወደ አዕምሯችን የመጣ ሃሳብ በቀጥታ ነው። ስንፅፍ ግን የታቀደና የተቀናጀ እንዲሆን የግድ እንጥራለን። ምክንያቱም ጽህፈት እንደ ንግግር የቀለለ አይደለም። ጊዜ፣ ልምድና መማር ይጠይቃል የሚል ሃሳብ ይሰጣሉ።

ሃሳቡ የሚያስረዳው ንግግር ከአዕምሮ በቀጥታ እያፈለቁ ማስተላለፍ ሲሆን መጻፍ ስናስብ ግን የመጻፍ ሂደቶችን የሚያልፍና ትምህርትን የሚጠይቅ መሆኑን ነው፡፡

በተመሳሳይ Glue, G.R. እና Jacobson, B. (2001) መጻፍ አዲስ ሃሳብ እንዳለ በቀጥታ የምናሰፍርበት ሳይሆን የምናውቀውና የምንፈልገው ጉዳይ በወረቀት ከማስፈር በፊት ማሰላሰል የሚጠይቅ ውስብስብ ተግባር የሚከናወንበት የሂደቶች ውጤት መሆኑን ይገልፃሉ። በአጠቃላይ ከፍ ብለው ከተገለፁት ሃሳቦች የምንገነዘበው ጽህፈት ከንግግር በላይ ማደራጀት፣ ማብላላትና ማቀድ የሚያስፈልገው መሆኑን ነው።

በአጠቃላይ ምሁራን ካሉት ሃሳብ በመነሳት የጽሕፈት ክሂል እንደ ማዳመጥና መናገር በልምድ የማይገኝ በትምህርት የሚገኝ ክሂል መሆኑ ለመከናወኑ ከሌሎች በበለጠ ውስብስብና አስቸጋሪ ነው። በመሆኑም የጽህፈት ክሂል የድምፆቹ ወኪል የሆኑ ሆሂያት በመጠቀም ሃሳብና ፍላጎትን፣ አመለካከትና ዝንባሌን ወይም መልዕክትን በተገቢ የአጻጻፍ

ሂደት ወረቀት ላይ በማስፈር ለሌላ ሰው ወይም ለመጪው ትውልድ ማስተላለፍ የሚችል የክሂሎች አውራ ነው።

## 2.3 የምጋቤምላሽ ምንነትና ተያያዥ ጽንሰ- ሀሳቦች[1]

የማንበብና የጽህፈት ክሂሎችን በማስተማር ወቅት ምጋቤምላሽ የመስጠት ዋና ዓላማ ክሂልን ለማዳበር ነው፡፡ ተማሪዎች የሚያነቡትን ምንባብና የሚያከናውኑትን የጽህፈት ተግባር በማበረታታትና በማነቃቃት ምጋቤምላሽ መስጠት አንዱ መሳሪያ ነው፡፡ ምክንያቱም ያላወቁትን እንዲያውቁ፣ የሳቱትን እንዲያስተካክሉ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ እንደ Hyland (2006) አገላለፅምጋቤምላሽ መስጠት በትምህርት ላይ በስፋት የሚታይ ጉዳይ ነው፡፡ መማርን በማበረታትና በማጠናከር እንደዋና መሳሪያ የሚያገለግል ነው በማለት ይገልፃሉ፡፡

እንደ Kepner (1991) አገላለፅ በአጠቃላይ ምጋቤምላሽ በማንኛውም የመማር ማስተማር ሂደት ትክክል ወይም ስህተት መሆንን የምናሳይበት መሳሪያ ነው፡፡ ምጋቤምላሽ የሚለው ቃል ግብረመልስ፣ አስተያየት፣ ማስተካከያ ወይም እርማት መስጠት ከሚሉት ቃላቶች ጋር ይመሳሰላል፡፡ እነዚህን ቃላቶች አንዱን በአንዱ በመተካት መጠቀም እንደሚቻል ይገልፃሉ፡፡ ነገር ግን ቃላቶቹን በተማሪዎች ጽሁፍ ላይ ስንጠቀም የተወሰነ ልዩነት ሊኖራቸው ስለሚችል ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ ያስረዳሉ፡፡

እንደ Timbur, John (1985) አገላለጽ ምጋቤምላሽ ተከታታይ የሆነ ክንውንን የሚነካ የተማሪዎችን ስሜት ወደ ተወሰኑ ጉዳዮች በመማረክ እነዚህኑ ጉዳዮች በተከታታይ ክንውን ውስጥ ለውጥ እንዲያካሂዱ የሚያደርግ የክንውን መረጃ (ዜና) ነው፡፡ እንደ Crystal, David (1994) አስተሳሰብ ምጋቤምላሽ ለኦርጅናሉ ውጤት አመንጭ መረጃ (ዜና) መልእክት የሚተላለፍበት ሂደት ነው፡፡ መረጃው ወይም ዜናው ራሱ ምጋቤምላሽ ነው፡፡ ቃሉ ከሳይበርኔትክስ የመጣ ሲሆን ለማሽኖች፣ ለእንስሳትና ለሰው መገናኛ ውሏል፡፡

መልዕክት ላኪው ለመልእክት ተቀባዩ የተላለፈለትን መልእክት ስለመቀበሉ የሚቆጣጠርበትና አስፈላጊ ለውጦችን የሚያደርግበት ስርአት ነው፡፡ Keh,C,L (1990) እንደገለፁት ምጋቤምላሽ ለጽህፈት ሂደታዊ አቀራረብ መሰረታዊ አላባ ነው፡፡ ተማሪው (ጸሀፊው) ጽሁፉን እንዲከልስ

[1]በቀጥታ ቃሉን በተመለከተ ምጋቤምላሽ ከሌላ ቋንቋ የተወሰደ የሚመስል የአማርኛ ቃል ነው፡፡ መጋቤ ከሚለው የተወሰደ አይደለም፡፡ የእንግሊዘኛ ቃሉ (Feedback) የሚለው ነው፡፡ መሪጌታ ቤዛ (ቃሉን በተመለከተ ለተጠየቁት የሰጡት መልስ)

መምህሩ የሚሰጠው የመረጃ ግብአት አለው፡፡ በሌላ አነጋገር ጸሀፊው አንባቢን የሚስብ ጽሁፍ እንዲያቀርብ የሚያገኘው አስተያየት ጥያቄዎችና ሀሳቦችን ይመለከታል፡፡

## 2.3.1 የምጋቤምላሽ አይነቶች

ምጋቤምላሽ በተለያየ መንገድ ሊሰጥ ይችላል፡፡ Anker (2000) መምህራን ምጋቤምላሽ ዓይነቶችን በክፍል ውስጥ ሊጠቀሙ የሚችሉት አንዱን አይነት ለብቻው ወይም አንዱን ከአንዱ ጋር በማደበላለቅ ሲሆን እያንዳንዱ የምጋቤምላሽ አይነት የራሱ የሆነ አስተዋፅኦ ወይም ጠቀሜታ ስላለው መምህራኑ ይህን ተረድተው በአጠቃቀም ጊዜ አስፈላጊውን ትኩረትና ጥንቃቄ መስጠት ይገባቸዋል በማለት ገልፀዋል፡፡ እንደ Angelo, Cross (1993) እና Daiker (1989) በዋናነት የሚጠቀሱት የምጋቤምላሽ አይነቶች የሚከተሉት እንደሆኑ ይገልጻሉ፡፡

### 2.3.1.1 ገምጋሚ ምጋቤምላሽ

ይህ የምጋቤምላሽ አይነት በውጤት የሚገለጽ ነው፡፡ መምህራን ተማሪዎች ለሚጽፉት ጽሁፍ ተገቢ ይሆናል ያሉትን ውጤት የሚሰጡበት ሲሆን ተማሪዎቹም በመምህራቸው የተሰጣቸውን ውጤት በማየት የጽሁፋቸውን ደረጃ ጥሩ ወይም ዝቅተኛ መሆኑን ይገነዘቡና በቀጣይ ስራቸው የጎደለውን ውጤታቸውን ለማስተካከል ፍላጎት እንዲያድርባቸው የሚያበረታታ ነው Daiker, (1989) በማለት ገልፀዋል፡፡

ከቀረበው ሃሳብ መረዳት የተቻለው መምህራን የተማሪዎችን ጽሁፎች ከገመገሙ በኋላ ውጤት የሚሰጡበት መንገድ መኖሩንና ተማሪዎች በተሰጣቸው ውጤትም ምን ዓይነት ጽሁፍ እንደጻፉ የሚገነዘቡበት መንገድ እንደሚኖር ያስረዳል፡፡

እጅጋየሁ አብርሃ (2002) ን ጠቅሰው ገምጋሚ ምጋቤምላሽ ተማሪዎች በጻፉት ፅሁፍ ላይ ያለምንም ማስተካከያ ውጤት ብቻ የሚሰጥበት ምጋቤምላሽ አይነት እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ይህ የምጋቤምላሽ አይነት በውጤት ላይ የሚያተኩር በመሆኑ ከፍተኛ ውጤት ያመጡትን የሚያበረታታ ሲሆን ዝቅተኛ ውጤት ያመጡትን ተማሪዎች ደግሞ ተስፋ ሊያስቆርጥ ይችላል፡፡

ከዚህ ሃሳብ መረዳት የተቻለውም መምህራን ተማሪዎቻቸው የጻፏቸውን ጽሁፎች በሚገባ ከተመለከቱና ከገመገሙ በኋላ ውጤት በመስጠት እንደሚለይዋቸው ያስረዳል፡፡ በመሆኑም በተማሪዎች መካከል ልዩነት ሊኖር እንደሚችል ያሳያል፡፡ ይህ ሊሆን የሚችለው ደግሞ ሁሉም ተማሪ እኩል በሆነ ደረጃ ሊጽፍ እንደማይችል የሚያስገነዝብ ነው፡፡

### 2.3.1.2 ትዕዛዛዊ ምጋቤምላሽ

ትዕዛዛዊ ምጋቤምላሽ በተማሪዎች ልምምድ ስራ ላይ ያሉትን ወይም ወደፊት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ስህተቶችን እንዲያስተካክሏቸው በመምህራን ከሚሰጡት አስተያየቶች ይልቅ ተማሪዎች ራሳቸው ስህተታቸውን እንዲያርሙ የሚረዳ ዘዴ ነው፡፡ ዘዴው ተማሪዎች ምን አይነት ስህተት እንደፈጸሙና እንዴት መታረም እንዳለበት እንዲያውቁ የሚረዳቸው ቢሆንም ተማሪዎች ብዙ ድካም ስለማይፈልጉ ተቀባይነቱ አነስተኛ ነው Daiker (1989) ብለዋል፡፡
ከቀረበው ሃሳብ መረዳት የተቻለው ትዕዛዛዊ ምጋቤምላሽ የሚባለው ተማሪዎች ያዘጋጁትን ጽሁፍ ከመምህራቸው በሚሰጣቸው ትዕዛዝ መሰረት ራሳቸው ስህተታቸውን እንዲፈልጉና እንዲያርሙ የሚያደረግ ነው፡፡ ይህ መሆኑም ተማሪዎች ጽሁፎችን እንዴት ማረምና ማስተካከል እንደሚቻል እንዲያውቁ የሚያደርግ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

የትዕዛዛዊ ምጋቤምላሽ ዓይነት ተማሪዎች ስህተታቸውን በራሳቸው እንዲያስተካክሉ መምህሩ በትዕዛዝ መልክ ምጋቤምላሽ የሚሰጥበት ሂደት ነው፡፡ ይህም በመሆኑ ተማሪዎች ምን ላይ ስህተት እንደሰሩ እና እርማቱምን እንዲገነዘቡ ያደርጋቸዋል እታለማሁ (2006) ብለዋል፡፡

ከሃሳቡ መረዳት የተቻለው ተማሪዎች ምን ዓይነት ስህተት እንደሰሩ የማሰቢያ ጊዜ በመውሰድ በራሳቸው እርማት እንዲወስዱ ከተደረገ በኋላ ከመምንራቸው የሚሰጣቸውን እርማት ለመገንዘብ ቀላል መንገድ መሆኑን የሚያስገነዝብ የምጋቤምላሽ ዓይነት ነው፡፡
እንደ Anker (2000) ትዕዛዛዊ ምጋቤምላሽ አሰጣጥ ስሌት ያለው፣ ተቀባይነት እና ተመራጭነት ያለው እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች ብዙ ጥረት ማድረግ ስለማይጠበቅባቸው የመጻፍ ችልታቸውን ለማሻሻል ይረዳል፡፡
ሃሳቡ የሚያስገነዝበው ተመራጭ የምጋቤምላሽ ዓይነት መሆኑን ነው፡፡ በተጨማሪም ብዙ ጥረት ማድረግና መድከም የማያስፈልገው የምጋቤምላሽ ዓይነት ስለሆነ የመጻፍ ችሎታን ለማሳደግ የሚረዳ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡

### 2.3.1.3 አጠናካሪ ምጋቤምላሽ

እንደ Moxley (1989) አገላለፅ አጠናካሪ ምጋቤምላሽ በተማሪዎች ጽህፈት ላይ የሚሰጠው በጥያቄዎች መልክ ነው፡፡ ጥያቄው ሲቀርብ ጠቅለል ብሎ ሲሆን የሚያተኩረው በተወሰነ ነገር ላይ ብቻ ነው፡፡ አጠናካሪ ምጋቤምላሽ ሲቀርብ የጽሁፉ ዋና ሀሳብ የቱ ነው? ጽሁፉ በምን ላይ

ያተኩራል? የተሰጠው ማጠቃለያ ተገቢ ነው? ወዘተርፈ በሚሉ ጥያቄዎች ላይ ያተኩራል፡፡ በተጨማሪም ይህ ዘዴ ከጽሁፍ ቅርጽ ይልቅ ለይዘት የሚሰጠው ትኩረት ከፍተኛ ነው፡፡

እታለማሁ (2006) ፣ Kroma (1988) ን በመጥቀስ በተማሪዎች ፅሁፍ ላይ አስተያየትም ሆነ ጥያቄ ከመቅረቡ በፊት መምህሩን በመጀመሪያ የትምህርቱ ዓላማ ምን ላይ ያተኩራል? ተማሪዎች እንዲለማመዱ የተሰጣቸው ፅሁፍ በምን ላይ ያተኩራል? ሂደታዊ አፃፃፍ ከሆነ የተፃፈው ረቂቅ ስንተኛ ነው? ፅሁፋዊ ምጋቤምላሾችን ተማሪዎች በቀላሉ ይረዷቸዋል? ለሚሉት ነጥቦች ትኩረት የሚሰጥ የምጋቤምላሽ ዓይነት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

የቀረቡት ሃሳቦች የሚያስገነዝቡት አጠናካሪ ምጋቤምላሽ በጥያቄ መልክ እንደሚሰጥና ተፅፎ በቀረበው ጽሁፍ ማዕከላዊ ሃሳብ (ፍሬነገር) ላይ እንደሚያተኩር የሚፈትሽ ሲሆን የሚሰጠውን አጠናካሪ ምጋቤምላሽ ተማሪዎች ሊረዱት በሚችል መልኩ እንደሚያደርብ የሚያሳይ ነው፡፡

በተጨማሪም Moxeley (1998) አጠናካሪ ምጋቤምላሽ አመቻች እንደሚባልና ትኩረት የሚያደርገው በቋንቋው ይዘት ላይ እንደሆነ ለቋንቋው ቅርፅና ሰዋሰው ትኩረት እንደማይሰጥ ይገልፃሉ፡፡

ሃሳቡ አጠናካሪ ምጋቤምላሽ አመቻች ምጋቤምላሽ እየተባለ አገልግሎት ላይ እንደሚውልና የጽሁፎች ጭብጥ ላይ እንጂ ሰዋሰዋዊ ህጎችን ትኩረት ያደረገ ምጋቤምላሽ እንደማይሰጥ የሚያስረዳ ነው፡፡

### 2.3.1.4 አስተካካይ ምጋቤምላሽ

አስተካካይ ምጋቤምላሽ ተማሪዎች ለሚጽፏቸው የሰዋሰው ስህተቶች መምህሩ በመጠቆም ተቀባይነት ያለውና ትክክለኛውን አስተካክሎ በመጻፍ የሚሰጥ እርማት ነው Anglo እና Cross (1993) ብለዋል:: ይህ ዘዴ ሲተገበር ስህተት የሆነውን በማክበብ ወይም የተለየ ምልክት በማድረግ ሲሆን ስህተት የሆነው ቃል ሀረግን ዐረፍተነገርን በማጥፋት የቃላትና የሀረጋት አገባብ በማስተካከል የተዘበራረቀ የአረፍተነገሮች ቅደምተከተል አስተካክሎ በመጻፍና ያልተሟላ ቃል ወይም ሀረግ በጽሁፍ ውስጥ ከታየ አስፈላጊውን እየጨመሩ አስተካክሎ ምጋቤምላሽ መስጠትን ይጠይቃል (Daiker 1989) በማለት ገልፀዋል::

ከቀረቡት ሃሳብ መገንዘብ የተቻለው አስተካካይ ምጋቤምላሽ የሚባለው በይበልጥ በመጻፍ ክሂል ጊዜ ተማሪዎች የሚጽፏቸውን ጽሁፎች መምህራን በትክክልና በትኩረት በማየት አጠቃላይ ሰዋሰዋዊ ስህተቶቻቸውን የሚያስተካክሉበት የምጋቤምላሽ ዓይነት መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች የቋንቋ ህጎችን አውቀው እንዲጽፉ ያደርጋል፡፡ ምክንያቱም በጽሁፍ ሃሳብን

መግለጽና መልዕክት ማስተላለፍ ብቻ ሳይሆን የጽህፈት ህግን ተከትሎ መጻፍ መታሰብ ያለበት መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡

አስተካካይ ምጋቤምላሽ በመተካት፣ በመሰረዝ፣ በመጨመርና በቅደምተከተል በማደራጀት ሰዋሰዋዊ ስህተቶችን በመጠቆምና ቀጥተኛ ምላሽ በመስጠት ስህተቶችን የማስተካከል ተግባር ነው፡፡ ስለዚህ ይህ የግብረመልስ አይነት በቋንቋ ቅርፅ ላይ የሚያተኩር ነው Zamel (1995) ይላሉ፡፡

ከዚህ ሃሳብ መረዳት የሚቻለው አስተካካይ ምጋቤምላሽ ተማሪዎች ይገልጽልኛል በሚል የተጠቀሙትን ቃል አግባብነት ባላቸው ተተኪ ቃላት በመለወጥ፣ ሃሳባቸውን በማስፋትና በማጥበብ፣ ሃሳቦችን በቅደምተከተላቸው በማስቀመጥ እና የጽሁፉን ቅርጽና ስርዓተነጥብ በማስተካከል የሰዋሰው ህፀፆችን የሚያርሙበት መንገድ አስተካካይ ምጋቤምላሽ እንደሆነ መረዳት ተችሏል፡፡

## 2.3.2 የምጋቤምላሽ አሰጣጥ ዘዴዎች

ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ ሆነው በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ እንዲጽፉ ማድረግ እና ተገቢ የሆነ ምጋቤምላሽ መስጠት የማንበብ እና የመጻፍ ችሎታቸውን ያዳብርላቸዋል፡፡ እነዚህ የምጋቤምላሽ አሰጣጥ ዘዴዎች እንደሚከተለው ያሰፍሯቸዋል፡፡

### 2.3.2.1 ምልክቶችን በመጠቀምና ማስረጃዎችን በማቅረብ ስህተቶችን ማመልከት

ስለዚህ ዘዴ Hedge (1988) እና Raimes (1983) እንደ የተሻለ አማራጭ የሚወሰድና የመምህሩን የስራ ጫናን ያቃልላል ተብሎ የሚታሰብ ሲሆን መምህራን ስህተቶችን በማመልከት የሚጠቀሙባቸው የምጋቤምላሽ ዘዴዎች የተለያዩ ናቸው፡፡ ምልክቶችን በመጠቀም ስህተቶችን ማመልከት በሚለው የጽሁፍ ወይም የድርሰት ምጋቤምላሽ ዘዴ መምህራን ሲጠቀሙ ተማሪዎቻቸው ለሁሉም ምልክቶች እንግዳ እንዳልሆኑና ሲያጋጥሟቸው አገልግሎት እንዳላቸው በቅድሚያ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ምልክቶችን በመጠቀም ስህተቶችን ማመልከት ምጋቤምላሽን ስንጠቀም ቀጥሎ ከተዘረዘሩት መምረጥና መገልገል እንደምንችል ያስረዳል፡፡ ስህተት የሆነውን አሀድ በማስመር በጽሁፍ ጠርዝ ላይ ምልክቱን ማስቀመጥም ተገቢነት አለው፡፡

እንደ Byrne (1988) ገለጻ ደግሞ ተማሪዎች በድርሰቶቻቸው ላይ ስለሰፈሩት የተለያዩ ምልክቶች የተማሪዎችን ጽሁፎች በማረም በኩል ችግሮችን ሙሉ በሙሉ በአንድ ጊዜ

የሚቀርፍ ሳይሆን በተደጋጋሚ በመጻፍ ከስህተታቸው ለማውጣት ጥረት እንዲያደርጉ የሚረዳ እንደሆነ የሚያመላክት ምጋቤምላሽ መሆኑን የሚገልጽነው በማለት ገልጸውታል፡፡

ከላይ ከቀረቡት ሃሳቦች መረዳት የሚቻለው ከትምህርቱ ጋር ሊገናኙ የሚችሉ ምልክቶችንና ማስረጃዎችን በመገልገል ተማሪዎች በሚያነቡበትና በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈፅሟቸውን ስህተቶች ማመልከት እንደሚቻል ነው፡፡ ምንም እንኳን ድርሰትን መነሻ አድርገው ገለፃቸውን ያቀረቡት ቢሆንም ምልክቶች ከንባብ እና ከፅሁፍ ልምምድ በኋላ የቃልና የጽሁፍ ምጋቤምላሽ መሽጫ መሆን እንደሚችሉ ያስረዳሉ፡፡

## 2.3.2.2 የሚታዩ ስህተቶችን በሙሉ በተገቢው ሁኔታ ማረም

ይህን የጽሁፍ የማረም ዘዴ አጠቃላይ እርማት መሆኑንና ምላሹ ጥንታዊ የአስተራረም ዘዴ በመባልም እንደሚታወቅ ይገልጻሉ፡፡ ይህ የምጋቤምላሽ ዘዴ ተማሪዎች በሚጽፉት ጽሁፍ ላይ የሚታዩትን ማንኛውንም ስህተቶች አንድ በአንድ እየነቀሰ በማሳየት ምጋቤምላሽ የሚሰነዘርበት ነው በሚል Lalande (1982) ገልፀውታል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ Byrne (1988) በጽሁፍ ውስጥ ለሚታይ ለማንኛውም ስህተት ምጋቤምላሽ የሚሰጥ ከሆነ ተማሪዎች ብዙ ስህተቶችን በመስራታቸው እንዲያፍሩ፣ እንዲሸማቀቁና ከጓደኞቻቸው ያነሱ እንደሆኑ አድርገው ራሳቸውን ስለሚቆጥሩ በመምህሮቻቸው ላይ አሉታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ ይህ ደግሞ የመጻፍ ተነሳሽነታቸውንና ዝንባሌያቸውን ስለሚያሳጣቸው ትምህርቱንም ሆነ መምህራንን እንዲጠሉ ያደርጋቸዋል፡፡

በተጨማሪም Madson (1983) እንደሚገልፁት በጽሁፍ ውስጥ ለሚታዩ ለማንኛውም ስህተት ምጋቤምላሽ መስጠት አስፈላጊ አይደለም ምክንያቱም ከመጠን ያለፈ እርማት የሚደረግላቸው ከሆነ በርካታ ተማሪዎች ከመጻፍ ሊታቀቡ ይችላሉ፡፡ Gipps (2004) እና Edge (1988) እንደሚገልጹት ደግሞ ተማሪዎች በጽሁፋቸው ለሚታዩ ስህተቶች ከሚሰጠው ምጋቤምላሽ የበለጠ እንዲማሩ ስህተቶቻቸውን እንዲቀንሱና እንዲቀርፉ ከተፈለገ ምጋቤምላሹን ቀስበቀስ መስጠት እንጂ በአንድ ጊዜ ለሚፈጽሙት ለእያንዳንዱ ስህተት የሚሰጥ ምጋቤምላሽ በተማሪዎች ሆነ በመምህራን ላይ ጫናን የሚፈጥር ግራ መጋባትን የሚያስከትልና ተነሳሽነትን የሚቀንስ ነው፡፡

ከቀረቡት ሃሳቦች መረዳት የሚቻለው ምጋቤምላሽ ቀስበቀስ የተማሪዎችን ስህተቶች እንደሚቀርፍ፣ ተማሪዎች በሚጽፏቸው ጽሁፎች ውስጥ የሚታዩትን ስህተቶች አብዝቶ መግለፅ የመጻፍ ፍላጎታቸውን እንደሚቀንስና ከጓደኞቻቸው የበታች የሆኑ እንዲመስላቸው አድራጊ ስለሚሆን የተወሰኑ ስህተቶችን በመስጠት ማበረታታት እንደሚገባ ያሳያሉ፡፡

### 2.3.2.3 ከስህተቶች ጎልተው የሚስተዋሉትን መርጦ ወይም ለይቶ እርማት መስጠት

እንደ Byrne (1988) እና Lalande (1982) ይህ ስህተት የማረም ዘዴ የሚከወነው የተወሰኑ ችግሮችን ብቻ መርጦ በማረም ሲሆን ጥቂት ስህተቶች የትኩረት አምድ ሆነው ይመረጣሉ:: ስህተቶቹ የሚታረሙት አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በተደጋጋሚ የሚፈጽሟቸውና የቋንቋ መማርን በሚያደናቅፉ አጠቃላይና ዋና ዋና የጋራ ችግሮች (Global errors) ላይ ብቻ ነው፡፡ በተጨማሪም መግባባትን ሊከለክሉ የሚችሉ ለሁሉም ወይም ለአብዛኛው ተማሪ የጋራ የሆኑ ዋና ዋና ስህተቶችን ማረም የጽሁፍ ስራን ውጤታማ ያደርገዋል፡፡ ስህተቶችን መርጦ ማረም የሚከወነው ስህተቶችን ሁሉ የማረም ዘዴ በቋንቋ መምህሩ ላይ የሚፈጥረውን ረጅም ጊዜ መሻማትና በቋንቋ ተማሪዎች ላይ የሚከሰተውን የተስፋ መቁረጥ ስሜት ለመቅረፍ ታስቦ ነው፡፡ እንደ Anker (2000) ገለጻ መምህራን በተማሪዎች ጽሁፍ ውስጥ የሚታዩ ሁሉንም ስህተቶች የሚያስተካክሉበት ምክንያት መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡፡

- ተማሪዎች እንዲምታቱና ግራ እንዲጋቡ ስለሚያደርግ የሚፈጽሙትን ስህተት ለማስወገድ ተነሳሽነቱና ዝንባሌው ስለማይኖራቸው፤
- ምጋቤምላሹ ከመብዛቱ የተነሳ ተማሪዎች መምህራንንም ሆነ ትምህርቱን መጥላት እንዲጀምሩ ስለሚያደርጋቸው፤
- ተማሪዎች ደካማ እንዲሆኑና ለመጻፍ ብቁ እንዳልሆኑ አድርገው እንዲያስቡ ስለሚያደርግ፤
- ለሁሉም ስህተቶች ምጋቤምላሽ ለመስጠት ብዙ ጊዜን ስለሚጠይቅ፤
- ተማሪዎች በጽሁፍቸው ለፈጸሙት ስህተት የተሰጠውን ምጋቤምላሽ ሊረሱት ስለሚችሉ የሚሉት ናቸው፡፡

የቋንቋ መምህራን በእርማት ሂደት ምጋቤምላሹ የሚያተኩርባቸውን ነጥቦች በማስገንዘብ የታለፉ ስህተቶች እንደሚገኙና የተሳሳተ የቋንቋ አጠቃቀም እንዳይጎለብት በማሳወቅ የተማሪዎችን የግንዛቤ አቅጣጫ ማስፋት ይገባቸዋል Lalande (1982) በሚል ገልፀዋል፡፡ እነዚህ የምጋቤምላሽ አሰጣጥ ዘዴዎች በተማሪዎች የጽሁፍ ወረቀት ላይ በሁለት አይነት መንገድ ሰፍረው ሊገኙ ይችላሉ Keh (1990) ይላሉ:: እነሱም በተማሪዎች ጽሁፍ ግራና ቀኝ ባሉት ክፍት ቦታዎች የሚሰጠው ሕዳጋዊ ምጋቤምላሽ (Marginal Feedback) ናቸው፡፡

በተማሪዎች ጽሁፍ ግራና ቀኝ ባሉት ክፍት ቦታዎች የሚሰጠው ሕዳጋዊ ምጋቤምላሽ በጽሁፍ ውስጥ ባሉት በእያንዳንዱ መስመር ላይ የሚሰጥ ከመሆኑም ባሻገር ግልጽና አጭር ነው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች ስህተታቸውን በፍጥነትና በቀላሉ ለመረዳት ያስችላቸዋል፡፡ ነገር ግን የጽሁፉን ጥቃቅን ስህተት እንጂ አጠቃላይ የሆነውን እርማት አያሳይም፡፡ የማጠቃለያ ምጋቤምላሽ አሰጣጥ መንገድ ግን በጽሁፉ መጨረሻ የሚሰጥ ሲሆን ተማሪዎች የፈጸሙትን አጠቃላይ ስህተት በመጠቆም ጽሁፉን ለማዳበር የሚያግዙ አስተያየቶችን በጽሁፉ መጨረሻ ያመለክታል፡፡ ሆኖም ይህ ምጋቤምላሽ አሰጣጥ መንገድ ለተማሪዎች ግራ የሚያጋባ ነው፡፡ ምክንያቱም በፈጸሙት በእያንዳንዱ ስህተት ዙሪያ ጥቆማ አያካሂድም፡፡ ስለዚህ ብቻውን መሰጠቱ ውጤት አልባ ሊያደርገው ስለሚችል ሕዳጋዊ ምጋቤምላሽና ማጠቃለያ ምጋቤምላሽን በተመጣጠነ ሁኔታ እየተጣመሩ ቢሰጡ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

### 2.3.3 የምጋቤምላሽ መስጫ መንገዶች

መንገዶቹን በሚመለከት Colle እና Chan (1994) የምጋቤምላሽ ባህርያት በማለት ያቀርባቸዋል፡፡ እነዚህም፡- ቃላዊና ጽሁፋዊ ምጋቤምላሽ፣ ይዘታዊና ቅርጻዊ ምጋቤምላሽ፣ አዎንታዊና አሉታዊ ምጋቤምላሽ ወዘተ በማለት ይከፍሏቸዋል፡፡ በCohen.A.D, Cavalcantl (1990) እና Leki (1990) አገላለጽ የተማሪዎችን የመማር ችሎታ ለማዳበር የሚሰጠው ምጋቤምላሽ ወደፊት ጠንክረው እንዲሰሩ ተስፋ የሚሰጥና ትችት እንዳይቀርብበት የሚያደርጉ የምጋቤምላሽ አሰጣጥ ሁኔታዎች ከላይ የጠቀስናቸው መሆናቸውን ይገልፃሉ፡፡

እንደ Arends (1997) ደግሞ ምጋቤምላሽ የሚሰጥባቸው መንገዶች በማለት ያቀርባቸዋል፡፡ ምጋቤምላሽ ቃላዊ፣ ጽሁፋዊና የቪዴዮ (ቲቪ) በማለት በዓይነት ከፍለዋቸው ይስተዋላል፡፡ ይሁን እንጂ krol (1991) በበኩላቸው ደግሞ በመምህራን የሚሰጥ ምጋቤምላሽ በቃል የሚከወን (Orall Feedback) እና በጽሁፍ የሚከናወን (Written Feedback) በማለት በሁለት ብቻ ይከፍሏቸዋል፡፡ ምንነታቸው የሚቀርብ ቢሆንም የዚህ ጥናት ትኩረት ግን በቃላዊና በጽሁፋዊ ምጋቤምላሾች ላይ ይሆናል፡፡

ከላይ ከቀረቡት ሃሳቦች መረዳት እንደሚቻለው ምሁራን የምጋቤምላሽ መንገዶችን በተለያየ መልኩ እንደሚከፍሏቸው እና የምጋቤምላሽ ባህሪያት በማለት እንደሚያቀርቧቸውም ያሳያል፡፡ ዋናው ግን ምጋቤምላሽ ከማቅረቢያ መንገዶች መካከል መምህራን የቃልና የጽሁፍ ምጋቤምላሽ እንዴት እንደሚያቀርቡ የፈተሸ በመሆኑ ጥናቱን ትክክለኛ እና ታማኝ እንዲሆን የምጋቤምላሽ መንገዶችን ከምንነታቸው ጋር ማቅረብ ተችሏል፡፡

### 2.3.3.1 የቃላዊ ምጋቤምላሽ ምንነት

ቃላዊ ምጋቤምላሽ በይዘት፣ አደረጃጀትና በቋንቋ አጠቃቀም ወዘተ… በመሳሰሉት ስህተቶች ላይ ትኩረት የሚያደርግ ነው፡፡ ከእያንዳንዱ ተማሪ ጋር ፊት ለፊት በመገናኘት ለተወሰነ የጊዜ ቆይታ ተግባራዊ የሚያደርግ የማስተማሪያ ዘዴ ነው፡፡

እንደ Hyland (2003) አገላለፅ ቃላዊ ምጋቤምላሽ በስህተት ወይም በድክመት ላይ ትኩረት በማድረግ የይዘቱን አደረጃጀትና የቋንቋ አጠቃቀም ፊት ለፊት በመገናኘት ከአምስት እስከ አስራ ሁለት ደቂቃዎች ያህል በእያንዳንዱ ተማሪ ፅሁፍ ላይ ምጋቤምላሽ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ቃላዊ ምጋቤምላሽ ተግባራዊ ሲሆን በመጠየቅ፣ በትዕዛዝ፣ በማድነቅና አስተያየት በመስጠት ይቀርባል፡፡ እነዚህም የቃላዊ ምጋቤምላሽ አሰጣጥ ዘዴዎች የዓረፍተ ነገሩን ትክክለኛ የሰዋሰው ቅደምተከተል በጥሩ ሁኔታ ተደራጅቶ መቅረቡን ስህተት የሰሩበትን ቦታ በማሳየት፣ እንደገና አስተካክለው እንዲሰሩ በማሳየት፣ የሳቱትን ወዲያውኑ በማሳየት ስህተታቸውን በግልፅ በመጠየቅ እና ስህተቱን በመድገም ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

በተጨማሪም Hyland (2006) የተሰኙ William (1984) የተባሉትን ምሁር ጠቅሰው ቃላዊ ምጋቤምላሽ በቃለ ምልልስ ይቀርባል፡፡ መምህራን ለተማሪዎች ቀጥተኛ የሆነ አስተያየት በመስጠት እርስ በርስ በመግባባት የሚሰጡትን ቃላዊ ምጋቤምላሽ ማስታዎሻ ይወስዳሉ፡፡

#### 2.3.3.1.1 የቃላዊ ምጋቤምላሽ አሰጣጥ

ቃላዊ ምጋቤምላሽ በክፍል ውስጥ ሲከናወን በማንኛውም አይነት ቃለ ምልልስ ይቀርባል፡፡ የንግግር ክፍላችንን በክፍል ውስጥ በብዛት በማቀናጀት መጠቀም ግልፅ የሆኑ ተግባራቶችን ለማከናወን ያስችላል፡፡ በዚህ መልክ መከወኑ ደግሞ የተማሪዎችን የማንበብና የመጻፍ ችሎታን ለማዳበር ይረዳል፡፡

እንደ Sanja Hadzic (2016) እንደገለጹት ቃላዊ ምጋቤምላሽ በሁለት አይነት መልኩ ሊሰጥ ይችላል፡፡ እነሱም፡- አዎንታዊ ምጋቤምላሽ ወይም አድናቆት (positive praise) ማስቀመጥ እና አሉታዊ ምጋቤምላሽ (Corrective Feedback) ናቸው፡፡ አዎንታዊ (አድናቆታዊ) ምጋቤምላሽ አዎ፣ ጥሩ ነው፣ እሽ የሚሉና የመሳሰሉትን በማለት የሚሰጥ ምጋቤምላሽ አይነት እንደሆነ Ellis (2008) ይገልፃሉ፡፡ Veliz (2013) እንደሚያስረዱት አሉታዊ ምጋቤምላሽ በቃል (በግልጽ) ወይም ውስጣዊ በሆነ መልኩ ሊቀርብ የሚችል የምጋቤምላሽ አይነት ነው፡፡ መምህሩ ውስጣዊ ምጋቤምላሽ በሚሰጥበት ጊዜ ተማሪው የፃፈውን ስህተት ደጋግሞ እንዲል (እንዲናገር) በማድረግ ስህተቱን በራሱ ተረድቶ እርማት መስጠት ነው፡፡ ሌላው ደግሞ መምህሩ በግልጽ (በቀጥታ) የሰሩትን ዓረፍተ ነገር ትክክል አይሆንም ስህተት ነው በማለት ነው፡፡

### 2.3.3.2 የጽሁፋዊ ምጋቤምላሽ ምንነትና ትኩረት

ይህ የምጋቤምላሽ መስጫ መንገድ እርማቱን የሚሰጠው በጽሁፍ ብቻ ነው፡፡ ተማሪዎች ሳነበቡት ምንባብ ሰሌዳ ላይ የሰሯቸውን ስህተቶች በመፃፍ እንዳይደግሟቸው ያደርጋል፡፡ የጻፏቸውንም ከሆነ መምህራን ተማሪዎች የጻፉበት ወረቀት ላይ ከተለያዩ አቅጣጫዎች በማየት የጽሁፍ እርማቶችን ይሰጣሉ፡፡

እንደ Fathman እና Whalley (1990) ገለፃ አንድ አንድ መምህራን ለስርዓተ ነጥብ፣ ለፊደል አጣጣል፣ ለሰዋሰው አገላለፅና ለመሳሰሉት ትኩረት ሲሰጡ አንዳንዶቹ ደግሞ ከዚህ በተለየ ሁኔታ ለይዘት አደረጃጀት ቅድሚያ ይሰጣሉ፡፡ ስለዚህ የመምህራን ቃላዊና ጽሁፋዊ ምጋቤምላሽ አሰጣጥ ትኩረት የተለያየ ሆኗል፡፡ በመሆኑም የመምህራን ቃላዊና ጽሑፋዊ ምጋቤምላሽ ትኩረት ቅርጽን፣ ይዘትን ወይም ቅርጽንና ይዘትን በጥምረት መሆን አለበት የሚለው ቁርጥ ያለ መደምደሚያ ያልተሰጠው ነው፡፡

ከሃሳቡ መረዳት የተቻለው መምህራን ቃላዊና ጽሁፋዊ መጋቤምላሽ ሲሰጡ ትኩረት አድርገው የሚጀምሩበት መንገድ የሚለያይ መሆኑን ነው፡፡

እንዲሁም Keh (1990) እና Hedge (1988) በቅርጽ ዙሪያ የሚያነጣጥር ምጋቤምላሽ፣ በሆህያት ግድፈት በስርዓተነጥብና በቃላት ተገቢነት በዓረፍተነገር አመሰራረት በአንቀፆችና በሰዋሰው ህግጋት ትክክለኛ መሆን ላይ ትኩረት ያደረጋል:: በተጨማሪም Zamel (1985) ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ተግባቦታዊ ተግባር ለማለፍ ሰዋሰዋዊ ስርዓቱን በትክክል ማዋቀርና ማፍለቅ በመቻልና ባለመቻላቸው ላይ አጽንኦት በመስጠት እርማት የሚደረግበት ስልት ቅርጽን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ በተጨማሪም የቋንቋ መምህራን ምጋቤምላሻቸው ከይዘት ይልቅ በቅርጽ ላይ ትኩረት ማድረጉ ለመጻፍ ክሂል መሻሻል የተሻለና ትክክለኛ አካሄድ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

በተመሳሳይ Shih (1986) እንደሚያስረዱት ለይዘታዊ ምጋቤምላሽ ቅድሚያ መስጠት አስፈላጊ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ ለተማሪዎች የጽሁፍ ልምምድ በመምህራን የሚሰጣቸው ምጋቤምላሽ የተዋጣለት የሚሆነው የጽሁፉን ይዘት መሰረት ካደረገ ነው፡፡ ይዘታዊ ምጋቤምላሽ ማለት ደግሞ የተማሪዎችን ጽሁፍ ከሀሣብ አንድነት አደረጃጀትና ጥልቀት ከመሳሰሉት አንፃር ታይቶ አስተያየት የሚሰጥበት ሂደት ነው፡፡ በተጨማሪ በይዘት ላይ ትኩረት ተደርጐ የሚሰጥ ምጋቤምላሽ በአብዛኛው በትርጉም ወይም በፍቺ ዙሪያ መሆን ይኖርበታል፡፡ ምክንያቱም መልዕክቱ የቀረበበት ቋንቋ ወይም ሰዋሰው ቅንብሩ ጥሩ ነው ባይሰኝም ይዘቱ በተገቢ ሁኔታ

ከተደራጀ ከሌላ ሰው ጋር መግባባት እንደሚያስችል ያስረዳል፡፡ እንዲሁም Shih (1986) ይዘትን ትኩረት የሚያደርግ ምጋቤምላሽ አስፈላጊና ላቅ ያለ ቦታ እንደሚሰጠው ያሳያል፡፡
ከላይ የቀረቡት ሃሳቦች እንደሚያስገነዝቡት ቅርጽን፣ ይዘትን፣ ሰዋሰው መዋቅርንና ህግጋትን መሰረት ውስጥ በማስገባት ሁሉም እንደፍላጎቱ ቀዳሚ ለሚለው ትኩረት በመስጠት ምጋቤምላሽ መስጠት እንደሚቻል የሚያሳይ ነው፡፡
በተጨማሪ Fathman እና Whalley (1990) እንደገለፁት መምህራን ለይዘት በተናጠል ምጋቤምላሽ ከሰጡባቸው ጽሑፎች የበለጠ ይዘትንና ቅርፅን አስመልክተው ጥምር ምላሽ የሰጡባቸው ፅሁፎች በይዘታቸው ላይ የተሻለ መሻሻል አሳይተዋል፡፡ ስለሆነም Grami (2005) ተማሪዎች ጽሑፎቻቸውን የበለጠ የሚያሻሽሉት ቅርፅንና ይዘትን በማጣመር ምጋቤምላሽ ከተሰጠ መሆኑን መምህራን ሊረዱት ይገባል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ይዘትንና ቅርጽን ያጣመረ ምጋቤምላሽ የተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡
Taylor (1981) ጠቅለል አድርገው እንዳስቀመጡት ምጋቤምላሽ በቅርጽ፣ በይዘት እንዲሁም ሁለቱን በጥምረት ሊሰጥ ይችላል፡፡ ሆኖም በብዙ ምሁራን ዘንድ መስማማትን ያገኘው ቅርፅንና ይዘትን ያጣመረ ምጋቤምላሽ ተመራጭነት ይኖረዋል የሚል ነው፡፡ ስለዚህ በቅርጽና በይዘት መካከል የተሳሰረ ዝምድና በማንኛውም ጥሩ ጽሁፍ ውስጥ የሚታይ ጉልህ ግንኙነት አንዳላቸው ተገንዝቦ እንደአስፈላጊነቱ መጠቀም ተገቢ ነው፡፡
ከላይ ከቀረቡት ተከታታይ ሃሳቦች መረዳት የሚቻለው መምህራን በቃልና በጽሁፍ ምጋቤምላሽ ሲሰጡ የጽሁፍን ቅርፅና ይዘት በማጣመር ማቅረብ እንዳለባቸው ነው፡፡ ምክንያቱም የሚዘጋጁት ጽሁፎች ሁሉ ቅርጻቸውን የጠበቁ እና መገለፅ የሚፈለገውን ሃሳብ በትክክል እንዲያስተላልፉ ሆነው መዘጋጀት እንዲችሉ የሚያደርግ መሆኑን ነው፡፡

## 2.3.4 የምጋቤምላሽ ባህርያት

### 2.3.4.1 አዎንታዊ (Positive) ባህሪ

እንደ Colle እና Chan (1994) አዎንታዊ የምጋቤምላሽ ባህሪ የተማሪዎችን ክንዋኔ ተገቢነት ያለው ስለመሆኑ ወይም ተማሪዎች ትክክለኛ መልስ ለማቅረብ መሞከራቸውን መምህሩ ትክክል ነው ወይም በጣም ጥሩ መልስ ነው በማለት ጥቆማ የሚያደርግበት ሲሆን ለተማሪዎች በሰሩት ስራ ላይ ጠንካራ ጎናቸውን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት መረጃ ለመስጠት የሚያገለግል ነው፡፡

በተጨማሪ Gipps et al (2004) ገለጻ ደግሞ ለተማሪው የሚቀርበው ምጋቤምላሽ ውጤታማ እንዲሆን የተማሪውን የመጻፍ ክሂል ለማሻሻል እንዲረዳና ተስፋ አስቆራጭ እንዳይሆን መምህራን የሚሰጡት ምጋቤምላሽ አዎንታዊ መሆን ይኖርበታል፡፡ ስለሆነም አዎንታዊ ምጋቤምላሽ ተማሪዎች የትምህርቱን አላማ ለማሳካት በትክክለኛው መንገድ እንዲጓዙ የሚያደርግ ስለሆነ የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማፋጠን ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል፡፡ እንደ Raimes (1983) ገለጻ ተማሪዎች በሚጽፏቸው ድርሰቶች ውስጥ መልካም ነገር ከተገኘ መጥቀስና ማድነቅ ለመምህሩ ስህተቶችን ለማረም መንገዱን ያቃልልለታል፡፡ መምህሩ አድናቆትን ለመስጠት በመጀመሪያ የተማሪውን ጽሁፍ በሚገባ ማንበብ ይጠበቅበታል፡፡ ከሀሳብ አደረጃጀት ጀምሮ እስከ ስርአተነጥብ አመራረጥና አጠቃቀም ድረስ በመውረድ እየተከተለው መሆኑን ከተገለጸለት በቀጣይ ስራ ጠንካራ ጎኑን እንዲከተል ያበረታታዋል፡፡

ከቀረቡት ሃሳቦች መረዳት የተቻለው ተማሪዎች መነቃቃት እንዲታይባቸው ሊያበረታቱ የሚችሉ ወይም መምህራን ለተማሪዎች መልካም እይታ እንዳላቸው የሚገልፁ አበረታች ሃሳቦችን በመናገር (በማቅረብ) ደስታን እንዲፈጥርላቸው አድርጎ ትምህርቱን መስጠት እንደሚገባ ያሳያል፡፡

በተጨማሪም አዎንታዊ ምጋቤምላሽ በመምህሩ ላይ የስራ ጫናን አይፈጥርም፡፡ ስለዚህ መምህራን ከስራ ብዛት የተነሳ እንዲሁም በተማሪዎች ለመወደድ ሲሉ የሚሰጧቸው ምጋቤምላሾች አዎንታዊ ወይም ጠንካራ ጎናቸውን ብቻ የሚያንጸባርቅ ከሆነ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ሊያጎለብት አይችልም፡፡ በመሆኑም ይህን ሁኔታ መምህራን በመገንዘብ የተማሪዎችን ደካማ ጎኖች የሚያሳዩ ምጋቤምላሾችን መስጠት አስፈላጊ መሆኑን ማጤን ይገባቸዋል Byrne (1988) ብለዋል፡፡

ሃሳቡ የሚያስገነዝበው መምህራን ለተማሪዎቻቸው ጽሁፍ ምጋቤምላሽ በሚሰጡበት ጊዜ ጥሩ፣ በጣም ጥሩ፣ ደህና እና የመሳሰሉትን አዎንታዊነት ያላቸውን ቃላት መጠቀማቸው ብቻ በቂ አይደለም፡፡ መምህራን ሁል ጊዜ አበረታች ነጥቦችን ብቻ የሚናገሩ ከሆነ የተለመደና ድክመታቸው እንደማይነገራቸው ስለሚገባቸው ትምህርቱን መቀበል ላይ ችግር እንዲጣይ ያደርጋል፡፡ ስለዚህ አንደነዚህ አይነት መልሶችን አዘውትሮ ከመናገር ይልቅ ስህተቶቻቸውን ሊያስተካክሉላቸው ወይም ሊጠቁማቸው ከሚችሉ ምጋቤምላሾች ጋር በማጣመር ቢሰጡ ውጤታማ መሆን ይችላሉ፡፡

በአጠቃላይ አዎንታዊ ምጋቤምላሽ የተማሪዎችን የአመለካከት ለውጥ ከማምጣቱም ባሻገር የመማር ተነሳሽነትን ከፍ የሚያደርግ በመሆኑ መምህራን ይህን አይነት ምጋቤምላሽ ቢጠቀሙበት በተማሪዎቻቸው ላይ የሚታየውን የመጻፍ ክሂል ችግር ሊቀረፍ ይችላል፡፡

## 2.3.4.2 አሉታዊ (Negative) ባህሪ

አሉታዊ የምጋቤምላሽ ባህሪን አስመልክቶ Leki (1997) እና Colleand Chan (1994) በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች ለሚሰሯቸው ለተለያዩ ስህተቶች ትኩረት እንዲሰጡ ለማድረግ ወይም ይህን አይነት ስህተት መስራት እንደሌለባቸው ለማሳሰብ ወይም በጥቃቅን ጉድለት ለሰሩት የጽሁፍ ስህተት እንደማስጠንቀቂያ ፊት ለፊት የሚሰጥ ነው:: አሉታዊ ምጋቤምላሽ የጽሁፍ ስራው ትክክል አለመሆኑን በሚጠቁም መልኩ ቀለል ባለሁኔታ መገለጽ አለበት፡፡ አለበለዚያ ተማሪዎች ለጻፉት ነገር የሚሰጣቸውን አሉታዊ ምጋቤምላሽ ትችታዊ አድርገው ስለሚቆጥሩ አስተያየቶቹ ምን እንደሚሉ፣ በወጉ ምን እንደሚል ስለሚያነቡት ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን ሳያገኙ ይቀራሉ፡፡

በተጨማሪም Colle እና Chan (1994) አሉታዊ ምጋቤምላሽ በተማሪዎች ላይ ሊደርስ የሚችለውን አሉታዊ ለውጥ ለመቀነስ የሚደረገው ጥረት የመምህራንን ብቃት የሚጠይቅ ነው፡፡ በመሆኑም መምህራን የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ እንዳይጎዳ ስሜታቸውን በማገናዘብ አግባብነት ያለው አሉታዊ ምጋቤምላሽ ሊሰጧቸው ይገባል፡፡ ይህ ከሆነ ተማሪዎቹ ደካማ ጎናቸውን ተገቢ በሆነ መንገድ በመረዳት ማስተካከል ይችላሉ::

Anderson እና Faust (1975) በጥናታቸው እንዳረጋገጡት ደግሞ በአሉታዊ (Negative) ምጋቤምላሽ ተማሪዎች በተሻለ ሁኔታ የጽህፈት ክሂል ችሎታቸውን ያዳብራሉ፡፡ ሆኖም በተማሪዎች በኩል የአሉታዊ (Negative) ምጋቤምላሽ ተቀባይነቱ በጣም አነስተኛ ስለሆነ መምህራን አስፈላጊ የሆነ አዎንታዊ (Positive) ምጋቤምላሽ በመሰንዘር የተማሪዎችን የጽህፈት ክሂል ችሎታቸውን እንዲያጎለብቱ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ከሃሳቦቹ መረዳት የሚቻለው አሉታዊ ምጋቤምላሽ የሚባለው ተማሪዎች የሚጽፏቸው ጽሁፎች ትክክል አለመሆናቸውን ወይም የጽሁፍ ድክመታቸውን ብቻ ማሳየት የሚቻልበት የምጋቤምላሽ መንገድ ነው፡፡ ምንም እንኳን በተማሪዎች በኩል ብዙም ተቀባይነት ያለው ባይሆንም ለመምህራን ግን ብቃታቸውን የሚያሳዩበት እንደሆነ ከምሁራኑ ሃሳቦች መቅሰም ተችሏል፡፡

### 2.3.4.3 ውጤታማ ባህሪ

ለተማሪዎች ጽሁፍ የሚሰጣቸው ምጋቤምላሽ ውጤታማ ነው ለማለት የራሱ መለያ ባህሪ እንዳለው ምሁራን ይገልጻሉ። እንደ Colle እና Chan (1994) አገላለፅ ደግሞ የውጤታማ ምጋቤምላሽ ባህሪዎችን በሚከተለው መልኩ አስፍረዋቸዋል።

መምህሩ የምጋቤምላሾችን አይነትና ብዛት ከተማሪዎች ዳራዊ ዕውቀት፣ ፍላጎትና እድሜ ጋር በማጣጣም በመርሀ ትምህርቱ አጠቃላይ ይዘት ላይ ሳይሆን ውስን በሆነ ነገር ላይ ያነጣጠረ ግልጽነት ከጎደለው ይልቅ ግልጽነት ባለው ሁኔታ ምጋቤምላሽ መቅረብ ብቻ በተማሪዎች ጽሁፍ በሚታዩ ስህተቶች ወይም ጠንካራ ጎኖች ላይ በሚሰጡ ምጋቤምላሾች የቋንቋ መምህራን ድርሻ የላቀ ቢሆንም ሁልጊዜም ምጋቤምላሹ በእነሱ ብቻ መሰጠቱ ውጤታማ ሊያደርገው አይችልም።

ስለዚህ በተማሪዎች መካከል የእርስ በርስ (ቢጤ) እርማት እንዲያደርጉ እድሉን በማመቻቸት የመማር ማስተማሩን አቅጣጫን ማቀላቀል ሲቻል ምጋቤምላሹ በተማሪዎች ልምምድ ላይ ትኩረት ለማድረግ የመጻፍ ክሂል ችሎታቸውን በማሻሻል በኩል ተገቢ የሆኑትን በማበረታታት ወይም የታዩትን ስህተቶች ጥቆማ የሚያደርግ እንጂ ስህተት ለምን ተገኘ ተብሎ አላስፈላጊ እርምጃ ውስጥ የማይገባ ሲሆን፣ ምጋቤምላሹ በመርሐግብሩ መሰረት የታቀዱትን ልምምዶች በክንውን ላይ እያሉ የሚሰጥ ሲሆን በተማሪዎች የጽሁፍ ልምምድ ላይ የሚሰጠው ምጋቤምላሽ የሚገለጽበት ሁኔታ ጽኑነትና ተቀባይነት ያለው የአስተራረም ስልት ያለው ሆኖ ሲገኝ፣ ማለትም ምጋቤምላሽ መሰጠት ያለበት ስህተቶችን ሳይዘል ጥቆማ ሰጥቶ የሚሄድ ወይም የተማሪዎችን ጽሁፎች ማበረታታት ወይም የተገኙትን ስህተቶች ምጋቤምላሽ የተሰጡት ነጥቦች በሌላው ተማሪ ጽሁፍ ላይ ሳይለወጥ በወጥነት ከተሰጠ የሚሉት ናቸው።

ከሃሳቡ መረዳት የተቻለው ውጤታማ ምጋቤምላሽ የሚባለው መምህራን ምጋቤምላሽ ሲሰጡ ግልፅነት ባለው ሁኔታ መስጠት እንዳለባቸውና ሁልጊዜም መምህራን ብቻ ሳይሆን ተማሪዎች እርስ በርስ እንዲተራረሙ በማድረግ ምጋቤምላሽ መስጠት የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ እንደሚያግዝ የሚያስረዳ ነው።

## 2.3.5 ምጋቤምላሽ ሊሰጡ የሚችሉ አካላት

ይህን ይዘት በተመለከተ Kroll (1990) እንደሚገልፁት ተማሪዎች በሚያነቡት ምንባብ እና ጽሁፍ ላይ ምጋቤምላሽ ሰጭዎች ሶስት እንደሆኑ ይገልጻሉ። እነሱም፡- የራስ (የግሌ) ምጋቤምላሽ፣ የብጤ ምጋቤምላሽ እና የመምህር ምጋቤምላሽ ናቸው።

### 2.3.5.1 የግል (የራስ) ምጋቤምላሽ

ይህ የምጋቤምላሽ ዓይነት የራስ፣ የግል ወይም የግሌ እየተባለ ይጠራል፡፡ የግሌ ምጋቤምላሽ የራስን ስህተት በራስ ማስተካከል መቻል ነው፡፡ የግሌ ምጋቤምላሽ ዓላማው ተማሪዎች በጽሁፎቻቸው ላይ ተደጋጋሚ ሂሳዊ ወይም የአርትኦት ንባብ በማካሄድ የሀሳቦቻቸውን ትክክለኛነት፣ (ተያያዥነት፣ ግጥምጥምነትና ውህደት) እና ተጠየቃዊነት በመመርመርና ክለሳ (review) በማድረግ የማንበብና የመጻፍ ክህሎታቸውን እንዱያጎለብቱ ማስቻል ነው፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንድ ተመራማሪዎች የግሌ ምጋቤምላሽ የማንበብም ሆነ የመጻፍ ክሂልን እንደማያሻሽል ያስገነዝባሉ፡፡

ለአብነት Beach (1979) ተማሪዎችን በሶስት ምድቦች ከፍለው ባካሄዱት ጥናት የደረሱበትን ውጤት ወይም ግኝታቸውን ሲያብራሩ የግሌ ምጋቤምላሽ በተሰጣቸውና ምንም አይነት ምጋቤምላሽ ባልተሰጣቸው ተማሪዎች መካከል የችሎታ ልዩነት ያስተዋለ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ እንደ Olson (1990) የብጤና የግሌ ምጋቤምላሽን ውጤታማነት በንጽጽር ፈትሸዋል፡፡ የደረሱበት ውጤትም እንደሚያሳየው የግሌ ምጋቤምላሽ ያከናወኑ ተማሪዎች የብጤ ምጋቤምላሽ ከተቀበሉ ተማሪዎች በተሻለ ሁኔታ የማንበብና የመጻፍ ክሂላቸው መሻሻል ማሳየቱን አስረድተዋል፡፡ በተጨማሪም Edge (1990) እና Mangelsdorf (1992) ተማሪዎች የራሳቸውን ስህተት ሲያርሙ በራስ የመተማመን ችሎታቸውን ከፍ እንደሚያደርጉ ይገልጻሉ፡፡

### 2.3.5.2 የብጤ (የጓደኛ) ምጋቤምላሽ

እንደ Byren (1988) እና Edge (1990) የብጤ ምጋቤምላሽ ተማሪዎች ተራ በተራ በሚያነቡበት ወቅት ወይም በንባብ ጊዜ የሚያስተናግዱትን ስህተት በመልቀም የሚነጋገሩበት እናያዘጋጁትን ጽሁፍ (ያከናወኑትን ሙከራ) እርስ በርስ በመለዋወጥ አንዱ የሌላውን የሚያይበትና አስተያየት የሚሰጥበት ነው፡፡ Keh (1990) ምጋቤምላሹም በተለያየ ስሌት በጥንድ ወይም በቡድን ሊተገበር እንደሚችል ይገልጻሉ፡፡ የብጤ ምጋቤምላሽ ውጤታማነቱን ለማወቅ ከግሌ ምጋቤምላሽ ጋር ንጽጽራዊ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ ለአብነት Abadikhah (2014) ከብጤ ምጋቤምላሽና ከራስ ምጋቤምላሽ የተማሪዎችን የጽሁፍ ፍሰት (Linguistic Accuracy) ለማሻሻል የትኛው ውጤታማ እንደሆነ ለማወቅ ባደረጉት ጥናት የተገኘው ውጤት ቡድኖች በጽሁፍ ፍሰታቸው ላይ ጉልህ መሻሻል እንዳመጡ ገልፀዋል፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይ Diab (2010) በበኩላቸው ከብጤና ከግሌ ምጋቤምላሽ የተማሪዎችን ስህተት ከመቀነስ አንጻር የትኛው የተሻለ እንደሆነ ለማወቅ ባደረጉት ሙከራዊ ጥናት የተማሪዎችን ስህተት ከመቀነስ አንጻር ከግሌ ምጋቤምላሽ ይልቅ የብጤ ምጋቤምላሽ የተሻለ እንደሆነ

ተመራማሪው ጠቁመዋል፡፡ እንደ Lucking (2008) የብጤ ምጋቤምላሽ የተማሪዎችን አካዳሚያዊ የማንበብና የመጻፍክሂል ለማሻሻል በተለይ በዩኒቨርሲቲ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውል ውጤታማ ዘዴ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ Min (2005), እንደገለፁት የብጤ ምጋቤምላሽ ውጤታማነት በአብዛኞቹ ምሁራን ዘንድ እንደሚተች (ነቀፋ እንደሚቀርብበት) ይገልጻሉ፡፡

## 2.3.5.3 የመምህር ምጋቤምላሽ

እንደ Leki (1990) ይህ ምጋቤምላሽ በግልና በብጤ ቢሰጥም አብዛኛውን ጊዜ ግን በመምህራን ተግባራዊ እንደሚደረግ ይገልጻሉ፡፡ በመሆኑም Ferris (1995) ከተማሪዎች ንባብ እና የጽሁፍ ምጋቤምላሽ አኳያ የመምህራንን ሚና በሶስት መልኩ ያዩታል፡፡

እነሱም እንደአሰልጣኝ (Coach)፣ እንደእውነተኛ አንባቢ (Real reader) እና እንደገምጋሚ (Evaluator) የመሆን ሚና አላቸው ይላሉ፡፡ በመሆኑም መምህራን ተማሪዎችን ሲያስነብቡ የሚሰሯቸውን ስህተቶች በመልቀም እና የተማሪዎችን ጽሁፍ እንደእውነተኛ አንባቢ ማንበብ እንደሚጠበቅባቸው ያስረዳሉ፡፡ የንባብ እና ጽሁፋዊ ምጋቤምላሽ አብዛኛውን ጊዜ በመምህራን ተግባራዊ ስለሚደረግ ውጤታማነቱ ከፍ ያለ ነው፡፡ በተመሳሳይ ከብጤ ምጋቤምላሽ ይልቅ የመምህር ምጋቤምላሽ በተማሪዎች የንባብና የጽሁፍ ክሂል ላይ የተሻለ ለውጥ እንደሚኖረው ጠቁመዋል፡፡

ሃሳቦቹ የሚያስረዱት መምህራን ምጋቤምላሽ ሲሰጡ እንደ ስልጠና ሰጪ፣ እንደ ሃያሲ፣ እና ጥልቅ አንባቢ በመሆን ለተማሪዎች ፅሁፍ ምጋቤምላሽ እንደሚሰጡ ነው፡፡ የተማሪዎችን ፅሁፍ በትክክል በማንበብ እየገመገሙ ምጋቤምላሽ መስጠት እንደሚገባ ያስረዳሉ፡፡

እንደ Yang (2015) የመምህር ምጋቤምላሽ ከብጤ ምጋቤምላሽ ጋር በቅንጅት መሰጠት እንዳለበት ጠቁመው የብጤና የመምህር ምጋቤምላሽ በቅንጅት የተሰጣቸው ተማሪዎች የመምህር ምጋቤምላሽ ብቻ ከተሰጣቸው ተማሪዎች በማንበብና በመጻፍ ችሎታቸው ላይ የተሻሉ መሆናቸውን ይገልጻሉ፡፡ Miao et al. (2006) እንደሚገልፁት አብዛኞቹ መምህራን የብጤ ምጋቤምላሽ ጠቃሚ እንዳልሆነ ያምናሉ፡፡ ምክንያታቸው ደግሞ ተማሪዎች በቂ ችሎታና ተሞክሮዎች ስለሌላቸው ለብጤዎቻቸው ጥሩ ምጋቤምላሽ መስጠት አይችሉም የሚል ነው፡፡

የቀረበው ሃሳብ የሚያስረዳው የብጤና የመምህር ምጋቡምላሽ በአንድ ተቀናጅተው መሰጠት ያለባቸው መሆኑን ነው፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ ተማሪዎች በቂ ችሎታ ስለማይኖራቸው ከትምህርቱ መጨረሻ ላይ በመምህራን የታገዘ ምጋቤምላሽ እንዲያገኙ የሚያደርግ መሆኑን ያስረዳል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የብጤ ምጋቤምላሽ ሶስት ዋና ዋና ችግሮች እንዳሉበት Parthasarathy (2014) ይገልጻሉ፡፡ እነሱም፡- ተማሪዎች ከይዘት ይልቅ ቅርጻዊ ስህተት ላይ ማዘንበላቸው፣ ብዙ ጊዜ ተማሪዎች የሚሰጡት ምጋቤምላሽ ለክለሳ የሚያበረታታ አለመሆኑ እና የብጤ ምጋቤምላሽ ተገቢ መሆኑን ለማወቅ አስቸጋሪ መሆኑ ነው፡፡

## 2.4 የቀደምት ተዛማጅ ጥናቶች

ከዚህ ጥናት ጋር በተወሰነ መልኩ ዝምድና ያላቸው ቀደምት ጥናቶች ቅኝት የሚደረግበት ንዑስ ክፍል ነው፡፡ በመሆኑም የየጥናቶችን መነሻ ሃሳብና ዓላማቸውን በመጥቀስ ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸው ተመሳስሎና እና ልዩነት በዝርዝር ቀርቧል፡፡

የሻረግ (2010) "ቅርፅ ተኮር፣ ይዘት ተኮርና ቅርፅና ይዘት ተኮር የፅሁፍ ምጋቤምላሽ የተማሪዎችን ድርሰት የመጻፍ ችሎታ የማሻሻል ሚና፣ በዘጠነኛ ክፍል ተተኳሪነት"፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ የተካሄደ ሲሆን የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ከቅርጽ ተኮር፣ ከይዘት ተኮርና ከቅርጽና ይዘት ተኮር ምጋቤምላሽ የተማሪዎችን ድርሰት የመጻፍ ችሎታ በማሻሻል ረገድ የትኛው የላቀ ሚና እንዳለው መመርመር ነው፡፡ ቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች እና የጽሁፍ መጠይቅ በመረጃ መሰብሰቢያነት የተጠቀሟቸው ሲሆኑ የትንተና መንገዱም በነጠላል ይይት ኤስ ፒ ኤስ ኤስ ቨርዥን 23ን (SPSS V. 23) በመጠቀም እንደተነተኗቸው ገልፀዋል፡፡ በአጠቃላይ የጥናቱ ውጤት ያሳየው ቅርጽና ይዘት ተኮር (ቅርጽና ይዘትን ያጣመረ) ምጋቤምላሽ የተማሪዎችን ድርሰት የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻልና ተማሪዎች ለምጋቤምላሽ መስጫ ዘዴው ያላቸውን አመለካከት ከፍ ለማድረግ ከሌሎቹ የምጋቤምላሽ መስጫ ዘዴዎች በተለየ ሁኔታ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው መሆኑን ነው፡፡

የሻረግ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለውን ስንመለከት ምጋቤምላሽ ላይ የተመሰረቱ መሆናቸው፣ ሁለቱም ሙከራን መነሻቸው ያደረጉ ጥናቶች በመሆናቸው፣ በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ትኩረት ያደረጉ መሆናቸው እና የተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ላይ መመስረታቸው ሲሆን ልዩነታቸውን ስንመለከት ደግሞ በቀደምት የተጠቀሰው የመፃፍ ችሎታን ለማሻሻል በቅርፅ፣ ይዘት እና ቅንጅት ተኮር የፅሁፍ ምጋቤምላሽ ላይ ምርምሩ ተካሂዷል፡፡ የአሁኑ ጥናት ግን የተማሪዎች አማርኛ ትምህርት የማንበብና የመፃፍ ክሂሎች ላይ የሚሰጡ ምጋቤምላሾችን አቀራረብ የሚተነትን መሆኑ ከይዘት ትኩረት አንፃር ለየት የሚያደርገው ነው፡፡ በተጨማሪም በአጠናን ስልታቸው፣ ዘመናቸው፣ የአጥኚዎች እድሜና ደረጃ፣ በጥናት መቼታቸው ይለያያሉ፡፡

እጅጋየሁ (2011) "በተማሪዎች ድርሰት ላይ የመምህራን ጽሁፋዊ ምጋቤምላሽ ያለው አስተዋፅኦ ትንተና በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት፡፡" ጅማ ዩኒቨርሲቲ፡፡ የተካሄደ ሲሆን የጥናቱ መሰረታዊ ዓላማ በሰሜን ሸዋ ዞን በመንዝ ላሎ ምድር ወረዳ የ9ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ተማሪዎች ለሚጽፏቸው ድርሰቶች መምህራን የሚሰጧቸው ፅሁፋዊ ምጋቤምላሾች የመፃፍ ችሎታቸውን በማሻሻል ረገድ ያለውን አስተዋፅኦ መተንተን ነው፡፡ በመረጃ

መሰብሰቢያነት ፈተና፣ የጽሁፍ መጠይቅና ቃለ መጠይቅ የተጠቀመች ሲሆን በአይነታዊ እና መጠናዊ አተናተን ዘዴ መረጃዎች ተተንትነው የቀረቡበትን መንገድ መመልከት ተችሏል። ከጥናቱ የተገኘው ውጤት ደግሞ መምህራን ለተማሪዎች ድርሰት መጻፍ ችሎታ መዳበር የመምህራን ጽሑፋዊ ምጋቤምላሽ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳለው በእርግጠኛነት የገለፁ ሲሆን ተማሪዎቹም ሆነ መምህሮቻቸው ፅሁፋዊ ምጋቤምላሽ የመጻፍ ችሎታቸውን ለማዳበር እንደረዳቸው ገልፀዋል።

በካሳዬ (2008) "በተማሪዎች ድርሰት ላይ መምህራን የሚሰጡት ምጋቤምላሽ መለያየት ምክንያት።" ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ። የተካሄደ ሲሆን የዚህ ጥናት ዓላማ በአማራ ክልል በምዕራብ ጎጃም ዞን በደቡብ አቸፈር ወረዳ በዱር ቤቴ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በሚፅፉት ድርሰት ላይ መምህራን የሚሰጡት ምጋቤምላሽ የመለያየት ምክንያት መመርመር ነው። በክፍል ውስጥ ምልከታና በጽሁፍ መጠይቅ መረጃው የተሰበሰበ ሲሆን በቲ- ስሌት ቀመር እና ዓይነታዊ ዘዴን በመጠቀም መረጃው ተተንትኖ የቀረበበትን ሁኔታ እንመለከታለን። የጥናቱ ግኝት ደግሞ መስፈርትን በመጠቀም አግባብነት ያለው ውጤት መስጠት መቻልና መነሻ መስፈርትን ባለመጠቀም የጅምላ ውጤት በመስጠት መካከል በሚፈጠር የኃላፊነት ስሜት መለያየት የተነሳ መምህራን ለተማሪዎች ድርሰት በሚሰጡት ውጤት ልዩነት እንዳይፈጠር ምክንያት እንደሆነ ያሳየ ሆኖ ይገኛል።

የቀደመውን ጥናት እንደ ቀደምት ግልጋሎት ላይ ሳውለው የመምህራን ምጋቤምላሽ ላይ በመመስረቱ ነው። ጥናቱ የተካሄደበት ዘመንና የተካሄደበት መቼት ለያይቷቸዋል።

# ምዕራፍ ሦስት

# 3. የጥናቱ ንድፍ እና የአጠናን ዘዴ

## 3.1 የጥናቱ ንድፍ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በምስራቅ ጉራጌ ዞን ኬላ ወረዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን ትኩረት በማድረግ በተማሪዎች የአማርኛ ትምህርት የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች ላይ የመምህራንን ቃላዊና ጽሁፋዊ ምጋቤምላሽ አቀራረብ መተንተን ሲሆን በአሃዛዊና ገላጭ የጥናት ንድፍ ተካሂዷል፡፡ ገላጭ የጥናት ንድፍን ያለው (2009) "ገላጭ ንድፍ ተመራማሪው የሚያጠናውን ባህሪ እንዳለ ትረካዊ በሆነ በአንባቢው አዕምሮ ውስጥ ስለጉዳዩ ስዕል በሚፈጥር ሁኔታ ባልተጋነነ፣ ባልተሞካሼ፣ ባልተንኳሰሰና እውነታውን በማያደበዝዝ መልኩ ለማቅረብ ያስችላል" በሚል ገልፀውት የሚገኝ ሲሆን ጥናቱም ከአሃዛዊ የጥናት ንግፍ በተጨማሪ ገላጭ የጥናት ንድፍን ተከትሏል፡፡

## 3.2 የአጠናን ዘዴ

ለጥናቱን ዓላማዎች ምላሽ ለመስጠትና መሪ ጥያቄዎችን ለመመለስ ይህ ጥናት አይነታዊና መጠናዊ ዘዴዎችን ወይም ቅይጥ ዘዴን ተጠቅሟል፡፡ ስነ- ዘዴዎችን በተመለከተ **ያለው** (2009) እንደሚሰበሰበው የመረጃ አይነትና የአተናተን ዘዴዎች አንፃር በቁጥር የሚገለፁ መረጃዎችን በመጠናዊ ምርምር ዘዴ እና በትረካዊ መልክ የሚገለጹትን ደግሞ በዓይነታዊ ምርምር ዘዴ በመጠቀም መተንተን ይቻላል ሲሉ አቅርበዋል፡፡

## 3.1 የናሙና አመራረጥ

### 3.1.1 የጥናቱ አካላይ

ይህ ጥናት በምስራቅ ጉራጌ ዞን ኬላ ወረዳ ላይ ያተኮረ ሲሆን በወረዳው ሁለት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብቻ ይገኛሉ፡፡ ወረዳው አዲስ የተቋቋመ እንደመሆኑ በሁለቱም ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎችን ተተኳሪ አድርጓል፡፡

### 3.1.2 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

ለዚህ ጥናት በምስራቅ ጉራጌ ዞን ኬላ ወረዳ ስር የሚገኙት የኬላ እና ጎጌቲ ሦስት ሁለት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተመርጠዋል፡፡ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልላዊ መንግስት ስር የሚተዳደሩ ሌሎችን ዞኖች እና በጉራጌ ዞን ስር የሚገኙ የሌሎችን ወረዳ ትምህርት ቤቶች

አላካተተም። ይህም በአመቺ ናሙና ዘዴ (Convenience sampling) የተመረጠ ነው። ዘዴው የተመረጠበት ምክንያት ደግሞ ጥናቱን ለማስሄድ አመቺ ሆኖ ስለተገኘ እና ወረዳው አዲስ በቅርቡ የተቋቋመ በመሆኑ ጥናት ያልተካሄደበት በመሆኑ ነው። በክልሉ የሚገኘው የጉራጌ ዞን እና በዚህ ዞን ስር የሚገኘው የኬላ ወረዳ አመቺ በመሆናቸው ተመራጭ ሆነዋል። አመቺ ያደረገው ምክንያትም የስራ አካባቢ በመሆኑ ነው።

### 3.1.3 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

ለጥናቱ የተመረጡት በምስራቅ ጉራጌ ዞን ኬላ ወረዳ ስር የሚገኙት ሁለት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ2015 ዓ.ም የትምህርት ዘመን ዘጠነኛ ክፍል በመማር ላይ የሚገኙ ተማሪዎች ናቸው። እነዚህ ተማሪዎች የተመረጡበት ምክንያት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመጡ (የተሻገሩ) በመሆናቸው ምንባቦችን በሚያነቡበት ወቅት እና በልዩ ልዩ ጽህፈት ጊዜ በርካታ ስህተቶችን ሲያስተናግዱ እመለከታለሁ። በመሆኑም በማንበብና መጻፍ ክሂሎች ላይ የሚሰጧቸውን እርማቶች መተንተን እንዳለባቸው ስላመንሁ ነው። ይህ የክፍል ደረጃ የተመረጠውም በወሳኝ ንሞና ስልት ነው። ሌሎችን የክፍል ደረጃዎች አላካተተም።

### 3.1.4 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

በኬላና ጎጌቲ ሦስት ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ትምህርታቸውን ለመከታተል የተመዘገቡ 1000 ተማሪዎች መካከል በተለያየ ምክንያት የሚያቋርጡና ማንበብና የመፃፍ ትምህርት ሲሰጥ በተደጋጋሚ የማይገኙ ተማሪዎችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በእያንዳንዱ ክፍሎች ከሚመደቡ 40 ተማሪዎች ወይም ጠቅላላ 25 ክፍሎች መካከል የእጣ ናሙና ዘዴን Random or probability sampling) በመጠቀም የሚመረጡ 70 ተማሪዎች የጥናቱ ተሳታፊዎች ይሆናሉ። 14 ከመቶ የሚሆነውን ማካተት ተችሏል። ይህ የተደረገውም ከሁሉም ተማሪዎች የሚገኙ መረጃዎችን ለመተንተን አስቸጋሪ በመሆኑ ነው። ምን ያህል ተጠኝዎች መረጃ ሰጪ መሆን እንዳለባቸው ታስቦ 70 ተማሪዎች ብቻ ተሳታፊ መሆን እንዳለባቸው ታምኖበታል። የተመዝጋቢ ተማሪዎችን ዳራ በተመለከተ አብዛኞቹ በጉራጌኛ (ክስታኔኛ) አፋቸውን የፈቱ ሲሆን ውስን የሚባሉ ተማሪዎች በኦሮምኛና በአማርኛ አፈፈት ናቸው። ሆኖም ግን በተደረገው የስራ ቆይታ የአፍ መፍቻ ተፅዕኖ ጎልቶ እንደማይታይባቸው መረዳት ተችሏል። እንደአንዳንድ አካባቢዎች አፍ መፍቻው ተፅዕኖ ሲያደርግባቸው አልተስተዋለም።

**ሰንጠረዥ 1፡- ተማሪዎችን የተመለከተ መረጃ**

| ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች | የፅሁፍ መጠይቆች ብዛት | በአግባቡ ተሞልተው የተመለሱ መጠይቆች | ጭራሽ ያልተመለሱና የተቀደዱ መጠይቆች | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| ኬላ | 35 | 29 | 6 | ግድየለሽነት እና ትኩረት ማጣት |
| ጎጌቲ | 35 | 26 | 9 | |

ከሰንጠረዡ መመልከት እንደሚቻለው በቁጥር 15 ተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቁን ጭራሽ ሳይመልሱ የቀሩ፣ በእርጥበት በማበላሸት እና በመቅደድ በሚገባ ሳያስረክቡ ቀርተዋል፡፡ ይህ ሊሆን የቻለውም መጠይቁን የሞሉበት ተማሪዎች ናሙና የተወሰደው በእጣ በመሆኑ ግድየለሽነትና ፍላጎት ማነስ ያለባቸው ተማሪዎች በመሳተፋቸው ነው፡፡ ይህ ማለት ግን ተማሪዎች በእጣ መለየታቸው ተገቢነት የለውም ማለት አይደለም፡፡ አወሳሰዱን ፍትሃዊ ለማድረግ እጣ የተሻለው መንገድ ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህ 15 ተማሪዎች በጥናቱ አልተተነተኑም፡፡ በትክክል ሞልተው የመለሱት 55 ተጠኝዎች በሚገባ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

### 3.1.5 የመምህራን ናሙና አመራረጥ

ይህ ጥናት በዋናነት የመምህራን ቃላዊና ጽሑፋዊ ምጋቤምላሽ በተማሪዎች የማንበብና ጽህፈት ክሂል ላይ ያለውን አቀራረብ ተንትኗል፡፡ በምስራቅ ጉራጌ ዞን ኬላና ጎጌቲ ሦስት ሁለት 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች አምስት (5) የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚያስተምሩ መምህራን ይገኛሉ፡፡ እነዚህ መምህራን ቁጥራቸው አነስተኛ ስለሆነ በጠቅላይ ናሙና ዘዴ (Comprehensive Sampling) መሰረት በጥናቱ ተተኳሪ ሆነዋል፡፡ የትምህርት ደረጃቸው ሁሉም የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸውና ከአምስት ዓመት በላይ የስራ ልምድ ያላቸው ናቸው፡፡ ከፍላጎት አንፃር ሲታይ መምህሮቹ ሊያበረክቱ በሚችሉት አስተዋፅኦ ሙሉ ፈቃደኛ መሆናቸውን ከወዲሁ ገልፀዋል፡፡

**ሰንጠረዥ 2፡- መምህራንን የተመለከተ መረጃ**

| ተ.ቁ | የትምህርት ቤቶች ስም | የመምህራን ብዛት | | የትምርት ደረጃ | | የስራ ልምድ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | ዲግሪ | ማስተርስ | |
| 1 | ኬላ | 2 | 1 | 5 | - | ሁሉም ከ6 ዓመት በላይ |
| 2 | ጎጌቲ | 1 | 1 | | | |

ሰንጠረዡ እንደሚያሳየው ሁሉም መምህራን የመጀመሪያ ዲግሪና ከስድስት ዓመት በላይ የስራ ልምድ ያላቸው መሆናቸውን ነው፡፡

## 3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

በምርምር ሂደት እንደ ምርምሩ ዓይነት እንደ ተጠኚዎቹ ሁኔታ፣ እንደተመራማሪው ችሎታ፣ ተመራማሪው ምርምሩን ለማካሄድ እንዳለው የገንዘብና የጊዜ መጠን፣ የስልጠና እና የፍልስፍና ሁኔታ ለመረጃ መሰብሰቢያነት የሚያገለግሉ በርካታ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አሉ፡፡ ዋና ዋናዎቹ የጽሁፍ መጠይቅ፣ ቃለ መጠይቅና መዛግብት፣ የተለያዩ ፈተናዎች እና ቡድን ተኮር ውይይት ናቸው በማለት ያለው (2006) ይገልፃሉ፡፡

በዚህም የጥናቱን ዓላማ እንደሚያሳኩ ታምኖባቸው የተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በዋናነት አራት የተለያዩ መንገዶች ናቸው፡፡ አንደኛው የሰነድ ፍተሻ ነው፡፡ የተማሪዎችን የግልና የቡድን ስራዎችና ደብተሮቻቸውን በትኩረት በመመልከት መረጃ ተሰብስቧል፡፡ ሁለተኛው ቃለመጠይቅ ሲሆን ይኸውም ከመምህራን ጋር በተማሪዎች የንባብና መጻፍ ክሂሎች ዙሪያ ስለሚሰጧቸው የምጋቤምላሽ አሰጣጥ በተመለከተ የሚቀርቡላቸውን ጥያቄዎች መነሻ በማድረግ ቆይታ ተደርጓል፡፡ ሶስተኛው የጽሁፍ መጠይቅ ነው፡፡ በጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች በመምህራን ምጋቤምላሽ አሰጣጥ ዙሪያ የጥናቱን ዓላማ መሰረት ያደረጉ አማራጭ የተሰጣቸው ጥያቄዎች ቀርበውላቸዋል፡፡ በእነዚህ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተገኙት መረጃዎች በወጉ ተተንትነዋል፡፡

### 3.2.1 ሰነድ ፍተሻ (Document analysis)

ይህ ጥናት ከሚጠቀምባቸው ዋና ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች መካከል ሰነዶችን መፈተሸ አንዱ ሆኗል፡፡ ያለው (2006) "መዛግብት በጽሁፍ መልክ ከቤተ መፃህፍቱ ከቤተ መዛግብቱ ወይም ከሌሎች መሰብሰቢያ ቦታዎች እንደ ሁኔታው ከግለሰቦች ሊገኙ የሚችሉ የመረጃ ምንጮች ናቸው" በማለት ገልፀዋል፡፡

ከላይ የቀረበው ሃሳብ እንደሚያስረዳው የተጻፉ ነገሮችን ፍተሻ በማድረግ መረጃዎችን መሰብሰብ እንደሚያል የሚያሳይ ነው፡፡ በዚህ መሰረት የተማሪዎችን ደብተር፣ የግልና የቡድን ስራዎችና የአጋማሽና ሌሎችን ፈተናዎችን የሚያካትት ነው፡፡ ፈተናዎች ይፈተሻሉ ሲባል መምህራን በቃላቸው የሚሰጧቸውን ምጋቤምላሾችን የሚፈትሽ ስለሆነ ነው፡፡ በመሆኑም ፈተናዎች መልስ ስጦችና ፃፎች ወይንም ማብራሪ ፈላጊዎች ከሆኑ ከተማሪዎች መልሶች ስር ምጋቤምላሹ በፅሁፍ ስለሚቀመጥ የሚፈለገውን መረጃ ቀለል ባለ መልኩ ለመሰብሰብ አጋዥ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

### 3.2.2 የጽሁፍ መጠይቅ (Questionnaire)

የጽሁፍ መጠይቁ በተመረጡ ተማሪዎች ብቻ ተሞልቷል፡፡ ጥያቄዎች በዓብይና ንዑሳ ክፍሎች ተከፋፍለው የቀረቡ ናቸው፡፡ መጠይቁ በፅሁፍ እንዲቀርብ የተደረገውም ተማሪዎች የሚነሱላቸው ጥያቄዎች ላይ ያላቸውን ግንዛቤ ለመለካት የሚያስችል በመሆኑ ነው፡፡

### 3.2.3 ቃለመጠይቅ (Interview)

ይህን በተመለከተ Gray (2004) ቃለመጠይቅ ሰዎች በውስጣቸው የነበረን ሃሳብ እንዲያወጡ የሚረዳ ዘዴ ነው፡፡ ይህም ሲባል አመለካከታቸውንና የሚያውቁትን በራሳቸው ዘዴ እንዲገልፁ ማስቻሉ ነው በማለት ገልፀውታል፡፡

ከሃሳቡ የምንረዳው አንድን መሰረታዊ አላማ መነሻ በማድረግ ጥያቄዎችን በማዘጋጀትና በማስገምገም ከተጠኝዎች ጋር ፊት ለፊት በመገናኘት መረጃዎችን የምንሸክፍበት መንገድ መሆኑን ነው፡፡

ቃለ መጠይቁ ለመምህራን የሚቀርብ ነው፡፡ በአንድ ቀን አምስቱም መምህራን ጋር ቆይታ ማድረጉ መሰላቸት እንዳይፈጥር በሁለት ቀናት ወይም ከዚያ በላይ በሚወስድ ጊዜ ይደረጋል፡፡ ያለው (1998) ሦስት የቃለ መጠይቅ አይነቶች አሉ፡፡ እነሱም፡- ውስን ቃለመጠይቅ (structure interview)፣ ከፊል ነጻ ቃለ መጠይቅ (semi structure interview) እና ነጻ ቃለ መጠይቅ (unstructure interview) እንዳሉ ይገልፃሉ፡፡ ጥናቱም ነፃ ቃለ መጠይቅ ዓይነትን በመጠቀም የሚፈለገውን መረጃ ሰብስቧል፡፡ ይህ የሆነውም መረጃ ሰጪዎች በነፃነት መግለፅ ያለባቸውን ሁሉ በነፃነት እንዲናገሩ ስለሚያስችል ነው፡፡

### 3.3 የመረጃ አተናተን (Methods of Data analysis)

በመረጃ መሰብሰቢያነት ያገለገሉት ምንጮችን መሰረት በማድረግ ሁሉንም መረጃዎች በተገቢ መንገድ በመተንተን ማቅረብ ተችሏል፡፡ በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በሰነድ ፍተሻ የተገኙት መረጃዎች በገለጻ ስልት የተተነተኑ ሲሆን በጽሁፍ መጠይቅ የተገኙት መረጃዎች ደግሞ ስርዓታዊ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው ቁጥር ነክ ትንተና ስልት የቀረበ ነው፡፡ በመሆኑም ጥናቱ የገለፃ ስልት እና ቁጥር ጠቃሽ በሆነ መንገድ ተተንትኗል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃ ትንተና

በመጀመሪያው ምዕራፍ የጥናቱ ዓላማ ክፍል እንደተገለፀው በተማሪዎች የአማርኛ ትምህርት የማንበብና የመፃፍ ክሂሎች ላይ የመምህራንን ቃላዊና ጽሁፋዊ ምጋቤምላሽ አቀራረብ መተንተን ነው፡፡ ይህንን ዓላማ ለማሳካትም በመረጃ መሰብሰቢያነት ምልከታ፣ ሰነድ ፍተሻ፣ ቃለ መጠይቅ እና የጽሁፍ መጠይቅ ያገለገሉ ሲሆን የተሰበሰቡት መረጃዎች አንድ በአንድ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

## 4.1 ሰነዶችን በመፈተሽ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

በምዕራፍ ሶስት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ አቅርቦት ክፍል የሰነድ ፍተሻ በማድረግ ለዚህ ጥናት የሚጠቅም መረጃ እንደሚሰበሰብ መግለፅ ተችሏል፡፡ ስለሆነም ባልተንዛዛ መልኩ የተማሪዎችን ደብተር ማየት ተችሏል፡፡ በተጨማሪ የሙከራና አጋማሽ ፈተናዎችን፣ የተናጠልና የቡድን ስራዎችን ለማየት ቢቻልም እንኳን በጽሁፍ የቀረበ ምጋቤምላሽ መስጠት እንዳልተቻለ ማየት ተችሏል፡፡ በመሆኑም ጥናቱ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን ሲፈትኑና የቡድን ስራ ሲሰጡ ፈተናዎች ላይም ሆነ የቡድን ስራዎች ላይ የጽሁፍ ምጋቤምላሽ መስጠት እንደሚቻል ጥናቱ ያሳያል፡፡ ከተነገረ ይልቅ የታየ ነገር የበለጠ ተቀባይነት ስላለው አንዳንድ ተማሪዎች ፈተናዎች ላይና የቡድን ስራዎች ላይ ጽሁፋዊ ምጋቤምላሽ እንደሚሰጣቸው ቢገልፁም በተደረገው የሰነዶች አሰሳ ምንም ዓይነት ምጋቤምላሽ የተሰጠበት መረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡

እንዲሁም የመርጃ መሳሪያማዕከሎችንበማየት ተዘጋጅተው የተቀመጡ መርጃ መሳሪያዎች መኖር አለመኖራቸውን ጭምር መፈተሽ ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ ማዕከሉ ላይ ለዚህ ጥናት የሚጠቅም ነገር መመልከት አልተቻለም፡፡

መጨረሻ ላይ በቀረበው የአባሪ ክፍል መመልከት እንደሚቻለው ከተማሪዎች ደብተር ላይ በየጊዜው የተፃፉ ዓረፍተነገሮችና አንቀፆች ላይ ምጋቤምላሾች ተሰብስበዋል፡፡ ለማስረጃ እንዲሆን አስፈላጊ የሆኑትን መውሰድ ተችሏል፡፡ እነዚህም የስርዓተነጥብ አጠቃቀም ችግሮች፣ መደበኛ ቃላትን አለመጠቀም፣ ሆህያትን በትክክል አለመፃፍ፣ ህዳግና የአንቀፅ ቅርፅ አጠቃቀም ችግር፣ ከሃሳብ መውጣት (ማፈንገጥ)፣ ርዕስን የሚመለከቱ ጉዳዮች፣ የሃሳብ አደረጃጀት፣ የሃሳብ መግተልተል፣ የአጨራረስ ችግሮች፣ ትኩረት አለመስጠትና ሌሎችንም በፍተሻ ሂደቱ ላይ ማግኘት የተቻሉ ነጥቦች ናቸው፡፡ በመሆኑም የተማሪዎች ደብተር ላይ በየጊዜው እንደነዚህ

አይነት ምጋቤምላሾች መሰጠታቸው ተማሪዎች የተሰጧቸውን አስተያየቶች ደጋግመው በማየት የተሻለ ጽሁፍ ለመጻፍ የሚጠቅም መሆኑን ማሳየት ተችሏል፡፡
ይህ የሚያሳየውም ስርዓተ ነጥቦችን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው፣ ለተግባቦት የሚያመቹ ቃላትን ለመጠቀም የሚያስችል ምጋቤምላሽ መስጠታቸው ለተግባቦት ሂደቱ አስፈላጊ መሆኑን እንዲማሩ ያደርጋል፡፡ ሃሳባቸው ድሪቶ የበላበት እንዳይሆን አደረጃጀቱን የተበቀ ፅሁፍ እንዲፅፉ የሚያስችል ስለሆነ ተገኒነት ያለው ምጋቤምላሽ እንደተሰጣቸው የሚያመላክት መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ የተማሪዎች ደብተር፣ ፈተናዎች፣ የተናጠልና የቡድን ስራዎች እና የክፍል ውስጥ ተግባራት ላይ ምጋቤምላሽ መስጠት እንደሚቻል ጥናቱ ይጠቁማል፡፡ በመሆኑም መምህራን ተማሪዎቻቸውን ከፈተኑ በኋላ በሚያርሙበት ወቅት ጊዜ እየሰጡ በማረም ፈተናዎች ላይ ምጋቤምላሾችን ማስቀመጥ፣ የግልና የቡድን ስራዎች ላይም የምጋቤምላሽ ተግባሩ መቀጠል እንዳለበት ጥናቱ ይመክራል፡፡

## 4.2 ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

**ሰንጠረዥ 1:- የማንበብ ክሂል ትምህርትን አቀራረብ በተመለከተ**

| ተ/ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | በጥቂቱ እስማማለሁ | አልስማማም | ድምር |
| | | በመቶኛ | በመቶኛ | በመቶኛ | በመቶኛ | በመቶኛ |
| 1 | መምህራችሁ የምንባቡን ርዕስ ሰሌዳ ላይ ከጻፉ በኋላ አንብበው ያስነብቧችኋል፡፡ | 63.63 | 29.09 | 7.27 | - | 100 |
| 2 | በንባብ ጊዜ ቃላትን፣ ሐረጋትንና ዓረፍተ ነገሮችን አስተካክሉ ሲሏችሁ ወዲያውኑ ሳትረሱት ደግማችሁ በማለት ታስተካክላላችሁ፡፡ | 72.72 | 3.63 | 18.18 | 5.45 | 100 |
| 3 | በንባብ ወቅት የሚያጋጥሟችሁን መደናቀፎች (አዳዲስ ቃላት ፍች፣ የሀሳብ ግልጽነት፣ የቃላት መጥበቅ መላላት፣ አገባብን አለመረዳት ወዘተ) መምህራችሁ እንዲያስወግዱላችሁ ትጠይቃላችሁ፡፡ | 18.18 | 18.18 | 36.36 | 27.27 | 100 |

ከላይ የቀረበው ሰንጠረዥ 3 ከማንበብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ አንፃር የቀረቡ ጥያቄዎችን የሚያሳይ ነው፡፡ የጥያቄዎች ምላሽ በቁጥር ተቆጥረው በመቶኛ ተሰልተው ቀርበዋል፡፡ መጠይቁ

ለ70 ተማሪዎች የቀረበ ሲሆን 55 በሚገባ ሞልተው የመለሱ ሆነዋል፡፡ የተማሪዎችን መልስ አሰጣጥ በተመለከተ በጣም እስማማለሁ፣ እስማማለሁ፣ በጥቂቱ እስማማለሁ እና አልስማማም በማለት መልስ ተሰጥቷል፡፡ በዚህ መነሻነት ሁሉም ጥያቄዎች ተተንትነዋል፡፡

ጥያቄ ቁጥር 1 መመልከት እንደሚቻለው በጣም እስማማለሁ 63.63 ከመቶ የሚሆነውን ይዘዋል፡፡ እስማማለሁ በሚል የመለሱ 29.09 ከመቶ የሚሆነውን ሲይዙ በጥቂቱ እስማማለሁ በሚል የመለሱ ደግሞ 7.27 ከመቶ የሚሆነውን መያዝ ችለዋል፡፡ አልስማማም የሚል መልስ የመለሱ ተማሪዎች የሉም፡፡ ይህ የሚያሳየውም መምህራቸው የምንባቡን ርዕስ ሰሌዳ ላይ ከጻፉ በኋላ መጀመሪያ አንብበው በማሳየት ተራ በተራ እንዲያነቡ የሚያደርጓቸው መሆኑን ነው፡፡

ጥያቄ ቁጥር 2 ላይ መመልከት እደሚቻለው በንባብ ጊዜ ቃላትን፣ ሐረጋትንና ዓረፍተነገሮችን አስተካክሉ ስትባሉ ወዲያውኑ ሳይረሳ ታስተካክላላችሁ ወይ? ተብለው ለተጠየቁት በጣም እስማማለሁ የሚል መልስ የሰጡት 72.72 ከመቶ የሚሆኑት ናቸው፡፡ እስማማለሁ በሚል የመለሱት 3.63 ከመቶ ይይዛሉ፡፡ በጥቂቱ የተስማሙ ተማሪዎች 18.18 ከመቶ ናቸው፤ አልስማማም በሚል ምላሽ የሰጡት 5.45 ከመቶ ሆነዋል፡፡ መረጃው እንደሚያሳየው ብዙውን ቁጥር የሚያካልሉት ተማሪዎች እንዲያስተካክሉ የሚጠየቁትን በስዓቱ የሚያስተካክሉ መሆኑን ነው፡፡ ወደ 5.45 ከመቶ የሚሆኑት ግን ማስተካከያቸውን እንደማይወስዱ ያሳየ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስተዚህም የተደረገላቸውን ማስተካከያ መውሰድና አለመውሰዳቸው በመምህራን መረጋገኝ ያለበት መሆኑን ጥናቱ አመላካች ነው፡፡

ጥያቄ ቁጥር 3 ን ሰንጠረዡ ላይ መመልከት እንደሚቻለው በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ እያንዳንዳቸው 18.18 ከመቶ የሚሆነውን የያዙ ሲሆን በጥቂቱ እስማማለሁ 36.36 በመቶ የሚሆነውን ይዟል፡፡ 27.27 ከመቶ የሚሆነውን የያዘው ደግሞ አልስማማም የሚለው መሆኑን የተሰበሰበው መረጃ ያሳያል፡፡ ይህም የሚያሳየው ተማሪዎች በንባብ ወቅት የሚያጋጥሟቸው መደናቀፎች (የቃላት መጥበቅና መላላት፣ ዓውድ (አገባብ)፣ ልዩ ልዩ ፍችዎች) መምህራቸው እንዲቀርፉላቸው የሚጠይቁት 18.18 ከመቶ የሚሆኑት ናቸው፡፡ 27.27 ከመቶ የሚሆኑት ግን የማይጠይቁ መሆናቸውን ከመረጃው መመልከት ተችሏል፡፡ ይህ ዓይነት ሁኔታ የሚፈጠረውም በርካታ ለመጠየቅ መፍራት ወይም አለመድፈር፣ ትኩረት ማነስ፣ ለመግለፅ ወይም ጥያቄን ለማቅረብ መቸገርና ራስን የማዘጋጀት ጉድለት (አለማጥናት) የሚሉና ሌሎችንም የግል ምክንያቶች መሰረቱ ስለሚያደርግ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን

የተማሪዎቻቸውን ነፃነት አለመንፈግ፣ እንዲጠይቁና ራሳቸውን እንዲገልፁ በማድረግ ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡

ቀጥሎ የቀረበው የማንበብ ክሂል ትምህርትን አቀራረብ በተመለከተ ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ ከላይኛው የቀጠለ ስለሆነ ቁጥር አልተሰጠውም፡፡ የትንተና አቀራረቡ ውስብስብነት እንዳይታይበት ከፋፍሎ ማቅረብ ተመራጭ ሆኗል፡፡

| ተ/ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | በጥቂቱ እስማማለሁ | አልስማማም | ድምር |
| | | በመቶኛ | በመቶኛ | በመቶኛ | በመቶኛ | በመቶኛ |
| 4 | መምህራችሁ ተራ በተራ ካስነበቧችሁ በኋላ ሰሌዳ ላይ የሚፅፉላችሁን አንዳንድ ማስተካከያዎች (የድምፅ ሁኔታ፣ ተደጋጋሚ ስህተት የታየባቸውን ቃላት በመጻፍ ወዘተ) ትይዟቸዋላችሁ፡፡ | 9.09 | 12.72 | 54.54 | 23.63 | 100 |
| 5 | ደጋግማችሁ እንድታነቡ ካደረጓችሁ በኋላ በምንባቡ ዙሪያ ሃሳብና ምክሮችን ሲሰጧችሁ የንባብ ልምዳችሁን ለማሻሻል ይጠቅማችኋል፡፡ | 18.18 | 47.27 | 12.72 | 21.81 | 100 |
| 6 | የምንባቦችን ፍሬ ሃሳብ እንድትገልፁ እና እንደገና ደብተራችሁ ላይ እንድታሰፍሩት በማዘዝ የጻፋችሁት ላይ ሃሳብ ይሰጡበታል፡፡ | 49.09 | 10.9 | 3.63 | 36.36 | 100 |

ጥያቄ ቁጥር 4 ላይ መመልከት እንደሚቻለው በጣም እስማማለሁ በሚል የመለሱት 9.09 ከመቶ፣ እስማማለሁ 23.63 ከመቶ፣ በጥቂቱ እስማማለሁ 54.54 ከመቶ እና አልስማማም 23.63 ከመቶ ናቸው፡፡ በመረጃው መሰረትም ንባቡ ከተጠናቀቀ በኋላ ሰሌዳ ላይ የሚጽፉላቸውን ምጋቤምላሾች በማስታወሻ ደብተራቸው ከሚይዟቸው ይልቅ ተከታትለው ምጋቤምላሾችን የማይዙ ተማሪዎች ቁጥር ከፍ ያለ ሆኖ ታይቷል፡፡ የሚሰጣቸውን ምጋቤምላሽ እየተከታተሉ መያዝ የሚጠቅመው አይረሴነትን ለመቅረፍ በመሆኑ ተማሪዎች አያያዝ ላይ ችግር የታየባቸው ስለሆነ ለወደፊቱ ክትትል የሚያስፈልጋቸው መሆኑን መረጃው አሳይቷል፡፡

ጥያቄ ቁጥር 5 ላይ ማስተዋል እንደሚቻለው በተደጋጋሚ የሚቀርብላቸውን ምንባብ እንዲያነቡ ከተደረገ በኋላ በምንባቡ ሃሳብ ዙሪያ ገንቢ ሃሳቦችና ምክሮችመሰጠታቸው ጠቀሜታ አላቸው የሚል እምነት ያላቸው በድምሩ 78.17 ከመቶ የሚሆኑት ሲሆኑ አልስማማም በማለት የመለሱት 22.81 ከመቶ የሚሆኑት ናቸው፡፡ ይህ መረጃ የሚያሳየው ደግሞ ከግማሽ በላይ የሆነውን ቁጥር የሚሸፍኑት የሚሰጣቸውን ምክሮችና ሃሳቦች በትክክል የሚረዱት መሆናቸውን ነው፡፡ ከዚህ በተቃራኒ 22.81 ከመቶ የሚሆኑት በምንባብ ትምህርታቸው ዙሪያ የሚቀርቡላቸውን ሃሳቦች የማይቀበሉ ወይም ጠቀሜታውን ያላወቁት ተማሪዎች እንዳሉ መረዳት ተችሏል፡፡ ስለዚህም በምንባቦች ዙሪያ የሚለገሱት ሃሳቦች የሚኖራቸውን ጠቀሜታ ማሳወቅ ቀዳሚነት እንዳለው ጥናቱ ጠቋሚ ነው፡፡

ጥያቄ ቁጥር 6 ን ሰንጠረዡ ላይ መመልት እንደሚቻለው በጣም እስማማለሁ 49.09 ከመቶ፣ 10.9 ከመቶ እስማማለሁ፣ 3.63 ከመቶ በጥቂቱ እስማማለሁ እና 36.36 ከመቶ ደግሞ አልስማማም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከመረጃው መገንዘብ የሚቻለውም ከመቶ ግማሽ አካባቢ የሚሆኑት የምባቡን ፍሬ ሀሳብ በአግባቡ የሚገልፁ፣ ማስታወሻ ደብተራቸው ላይ ፅፌው የሚያሳዩ እና ከመምህራቸው ምጋቤምላሽ የሚወስዱ መሆናቸውን ነው፡፡ ከዚህ በተቃራኒ በሆነ እይታ ደግሞ 36.36 ከመቶ የሚሆኑት የሚያነቡትን ምንባብ ፍሬ ሃሳብ በቃላቸው መግለፅ የሚቸገሩ፣ ፍርሃት የሚያረብባቸው፣ በደብተራቸውም ፍሬ ሃሳቡን ጨምቀው በመፃፍ ከመምህራቸው ምጋቤምላሽ የማይቀበሉ መሆናቸውን ነው፡፡ ይህን መነሻ በማድረግም ጥናቱ መምህራን ሁሉንም ተማሪዎች ማወቅና ክፍተታቸውን መረዳት አስፈላጊ እንደሆነ ነው፡፡

ቀጥሎ የቀረበው የማንበብ ክሂል ትምህርትን አቀራረብ በተመለከተ ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ ከላይኛው የቀጠለ ስለሆነ ቁጥር አልተሰጠውም፡፡ ትንተናው ውስብስብነት እንዳይታይበት ሊከፋፈል ተችሏል፡፡

| ተ/ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | |
| --- | --- | --- | --- | --- | --- | --- |
| | | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | በጥቂቱ እስማማለሁ | አልስማማም | ድምር |
| | | በመቶኛ | በመቶኛ | በመቶኛ | በመቶኛ | በመቶኛ |
| 7 | በንባብ ወቅት መምህራችሁ የንባብ ጎደሏችሁን ያሳያሉ፡፡ | 12.72 | 12.72 | 21.81 | 52.72 | 100 |
| 8 | መምህራችሁ ካስነበቧችሁ በኋላ ማንኛውንም ማስተካከያ አይተው ዝም አይሉኝም፡፡ | 29.09 | 20 | 30.09 | 20 | 100 |
| 9 | ስታነቡ ቆምታ የሚያስፈልግበት ቦታ ላይ እረፍት በመውሰድ እንድታነቡ ያግዟችኋል፡፡ | 36.36 | 36.36 | 14.54 | 12.72 | 100 |

ጥያቄ ቁጥር 7 ላይ በንባብ ወቅት መምህራቸው የንባብ ጎደሏቸውን እንደሚያሳዩና እንደሚመለከቱ ተጠይቀው ነበር፡፡ ለዚህም በጣም እስማማለሁና እስማማለሁ 25.44 ከመቶ የሚሆኑት ናቸው፡፡ 21.81 ከመቶ የሚሆኑት ደግሞ በጥቂቱ እስማለሁ  በማለት የመለሱ ሲሆን 52.72 ከመቶ ያልተስማሙ ናቸው፡፡ ከዚህ መረጃ መረዳት የሚቻለውም ተማሪዎች በንባብ ጊዜ የሚታዩባቸውን የፊደላት መሸራረፍ፣ የድምፅ መቆራረጥ፣ በተለየ ዓውድ ማንበብ፣ ፊደል መቁጠር እና የመሳሰሉት ጉዳዮች ትኩረት መስጠት ያለባቸው ቢሆንም ተማሪዎች ተራ በተራ  በሚያነቡበት ጊዜ የሁሉንም ጉድለት (ክፍተት) እንደማያሳዩ ነው፡፡ ነገር ግን የሁሉንም ተማሪዎች ጉድለት በአጭር ጊዜ ማሳየት ከበድ ያለ ተግባር ቢሆንም ጎልተው የሚታዩ የጋራ ችግሮችን እየተከታተሉ ማሳየት አስፈላጊ መሆኑን ጥናቱ አመላክቷል፡፡

ጥያቄ ቁጥር 8 ን ከሰንጠረዡ ውስጥ ማየት እንደሚቻለው በጣም እስማማለሁ 29.09 ከመቶ፣ እስማማለሁ 20 ከመቶ፣ በጥቂቱ እማማለሁ 30.09 ከመቶ እና አልስማማም 20 ከመቶ ነው፡፡ ከተገኘው መረጃ መረዳት የሚቻለው 81 ከመቶ የሚሆኑት በከፊልም ይሁን ሙሉ በሙሉ መምህራቸው ምንባብ ካስነበቧቸው በኋላ ማስተካከያ እንደሚሰጧቸው የገለፁ ናቸው፡፡ 20 ከመቶ የሚሆኑት ግን አልተስማሙም፡፡ የሚያሳየውም በንቃት ከመከታተል ጉድለት፣ አዘውትረው ክፍል ውስጥ ካለመገኘት፣ ጥቅሙን ካለመረዳት እና ፅኑ ፍላጎት ካለመኖር ሊከሰት የሚችል በመሆኑ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ምጋቤምላሽ በሚሰጡበት ወቅት ክፍል ውስጥ የተገኘውንና ያልተገኘውን፣ የሚከታተላቸውንና የማይከታተላቸውን መፈተሽ ይኖርባቸዋል የሚል ድምዳሜ ወስዷል፡፡

ጥያቄ ቁጥር 9 ላይ መመልከት እንደሚቻለው በጣም እስማማለሁና እስማማለሁ 72.72 ከመቶ፣ በጥቂቱ የተስማሙ 14.54 ከመቶ እና አንስማማም በማለት የመለሱ 12.72 ከመቶ ናቸው፡፡ የተገኘው መረጃ የሚያሳየው አብላጫው የንባብ ቆምታ (የአፍታ ጊዜ) የሚያስፈልግበት ቦታ ላይ እረፍት እያደረጉ እንዲያነቡ መምህራቸው የሚያግዟቸው መሆኑን ነው፡፡ 12.72 ከመቶ የሚሆኑት ደግሞ የቆምታ ጊዜ እንዲወስዱ በመምህራቸው ድጋፍ እንደሚደረግላቸው የገለፁ ናቸው፡፡ ስራው ድካምና መሰላቸት ሊኖረው ስለሚችል ሁሉንም ተማሪዎች እንዴት ማንበብ እንዳለባው ማሳየት፣ ማንበብ አለማንበባቸውን ማረጋገጥ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፡፡ ጥናቱ የሚጠቁመው ግን እንዲህ ዓይነት ችግር ሲገጥም ስልትን መቀየር ወይም ተጨማሪ ዘዴ በመፍጠር ምጋቤምላሽ አይቀሬ መሆን ያለበት ነው፡፡ አንድም ተማሪ ሳይቀር በመከፋፈል አልያም ለምን ያህል ተማሪ እንደሚሰጡ በመለየት ምንባቡ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ እረፍት የሚወስዱባቸውን ቦታዎች ማሳየት ይገባል፡፡

በአጠቃላይ የማንበብ ክሂልን በተመለከተ ምጋቤምላሽ በሚቀርብበት ወቅት ጥቃቅንም ይሁን ጎልተው የሚታዩ ችግሮችን እየለዩ ለሁሉም ተማሪዎች ቃላዊ በሆነ መንገድ፣ ሰሌዳ ላይ እና ደብረታቸው ላይ እየፃፉ ምጋቤምላሽ መስጠት የንባብ እሎታቸውን ለማዳበር እንደሚጠቅም ያሳየ ነው፡፡

**ሰንጠረዥ 2፡- የመጻፍ ክሂል ትምህርትን አቀራረብ በተመለከተ**

| ተ/ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | በጥቂቱ እስማማለሁ | አልስማማም | ድምር |
| | | በመቶኛ | በመቶኛ | በመቶኛ | በመቶኛ | በመቶኛ |
| 1 | መምህራችሁ የቃላትና ተያያዥ ማስተካከያዎችን ይሰጧችኋል፡፡ | 72.72 | 18.18 | 9.09 | - | 100 |
| 2 | አንድ ርዕሰ ጉዳይ ሰጥተው ተደጋጋሚ እንድትጽፉ ያደርጋሉ፡፡ | 78.18 | 5.45 | 5.45 | 10.9 | 100 |
| 3 | መምህራችሁ በደብተራችሁ ላይ አንቀፆችን ያጽፏችኋል፡፡ | 52.72 | 36.36 | 3.63 | 7.27 | 100 |
| 4 | የፃፋችሁትን በማስነበብ ማስተካከያዎችን በቃልና በጽሁፍ ይሰጧችኋል፡፡ በማንበብና መፃፍ ክሂሎች ላይ ምጋቤምላሹ ዘወትራዊ ነው፡፡ | 20 | 34.54 | 27.27 | 18.18 | 100 |

ከላይ የቀረበው ሰንጠረዥ አራት ከመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ አንፃር ለተማሪዎች የቀረቡ ጥያቄዎችን የያዘ ነው፡፡ ሁሉም በአግባቡ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

ጥያቄ ቁጥር 1 ንበተመለከተ በጣም እስማማለሁ 72.72 ከመቶ የሚሆኑት ናቸው፡፡ ይህ ማለትም መጠይቁ ሞልተው ከተተነተኑ 55 ተማሪዎች 40 የሚሆኑት ማለት ነው፡፡ እስማማለሁ 18.18 ከመቶ፣ በጥቂቱ እስማማለሁ 9.09 ከመቶ ሲሆኑ አልስማማም የሚል ምላሽ የመለሱ ተጠኝዎች የሉም፡፡ መረጃው የሚያመለክተውም የቃላትና ተያያዥ ማስተካከያዎችን መምህራቸው እንደሚሰጧቸው መረዳት ተችሏል፡፡ ምጋቤምላሾችን እንደሚሰጡ የተረጋገጠውም በቀረበላቸው ጥያቄ ያልተስማሙ ተጠኝዎች ባለመኖራቸው ነው፡፡ ጥያቄ ቁጥር 2 ላይ የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው በጣም የተስማሙ 78.18 ከመቶ፣ እስማማለሁ 5.45 ከመቶ፣ በጥቂቱ የተስማሙ 5.45 ከመቶ እና ያልተስማሙ 10.9 ከመቶ ናቸው፡፡ ይህም የሚያሳየው የመፃፍ ክሂል በተደጋጋሚ ልምምድን የሚጠይቅ በመሆኑ ደጋግሞ መፃፍን ይጠይቃል፡፡ በመሆኑም መምህራን ተማሪዎችን ክፍል ውስጥ እና ቤታቸው የሚለማመዱበትን መንገድ በማመቻቸት ፅፈውም እንዲመጡ በማድረግ ያለማምዷቸዋል፡፡ ከመረጃውም ደጋግመው እንደሚያፅፏቸው መረዳት ተችሏል፡፡ ነገር ግን መሰላቸትን እንዳያስከትል ወቅቱን የጠበቀና የተማሪዎች ፍላጎት ከግንዛቤ ያስገባ መሆን ይኖርበታል፡፡ የቀረበው ጥያቄ ላይ ካልተስማሙት መረዳት የሚቻለውም የመጻፍ ፍላጎትና የመጻፍ ብቃት የሌላቸው ተማሪዎች ሊኖሩ ስለሚችሉ መምህራን የተማሪዎቻቸውን የመጻፍ ችሎታ በሚገባ በመለየት ልዩ ክትትል የሚፈልጉ መኖራቸውን ነው፡፡

ጥያቄ ቁጥር 3 ን ሰንጠረዡ ላይ ማየት እንደሚቻለው በጣም እስማማለሁና እስማማለሁ 89.08 ከመቶ ሲሆኑ በጥቂቱ እስማማለሁ 3.63 ከመቶ እና አልስማማም 7.27 ከመቶ ናቸው፡፡ ይህ የሚያሳየውም መምህራቸው ማስታወሻ ደብተራቸው ላይ ለተደጋጋሚ ጊዜ ልምምድ ካስደረጉ በኋላ በዋናው ደብተራቸው አንቀፆችንና መሰል ፅሁፎችን እንዲፅፉ በማድረግ እንደሚያለማምዷቸው ነው፡፡ 7.27 ከመቶ የሚሆኑት ግን ልምምዱን በደብተራቸው እንደማይፅፉ መረዳት ተችሏል፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለውም የተማሪዎች ዝንባሌና ፍላጎት የተለያየ እንደመሆኑ ለልምምዱ ጊዜ ትኩረት ካለመስጠት ሊመጣ የሚችል ስለሚሆን መምህራን ሁሉም ተማሪዎች መሞከራቸውን እየተዘዋወሩ መመልከትና እያንዳንዳቸው ደብተር ላይ ምጋቤምላሾችን በሚፅፉበት ወቅት የፃፉላቸውንና ያፅፃፉላቸውን ተማሪዎች መለየት እንዳለባቸው የሚያሳይ ሆኗል፡፡

ጥያቄ ቁጥር 4 ን በተመለከተ በጣም እስማማለሁ 20 ከመቶ እስማማለሁ 34.54 ከመቶ፣ በጥቂቱ እስማማለሁ 27.27 ከመቶ እና አልስማማም 18.18 ከመቶ ናቸው። የተገኘው መረጃ የሚያመላክተው 54.54 ከመቶ የሚሆኑት መምህራን ተማሪዎች የፃፉትን ፅሁፍ እንዲያነቡ ካደረጉ በኂላ በቃልና በፅሁፉ ማስተካከያዎችን እንደሚጧቸው የተስማሙ ናቸው። የመፃፍ ክሂል ላይ ምጋቤምላሹ የማይቋረጥ መሆኑን ያሳዩ ናቸው። ይህ ጥናትም እንደዚህ ዓይነቱ ተግባር መቀጠል ያለበት መሆኑን ያመለክታል። 18.18 ከመቶ ከሚሆኑት ግን ምጋቤምላሹ ዘወትራዊ አለመሆኑን መረዳት ተችሏል። እነዚህም የመፃፍ ክሂል ትምህርት ሲቀርብ የጎደላቸውን ለመምህራቸው በማቅረብ አልያም ከመምህራን በኩል ለሁሉም ተማሪዎች የፅሁፍና የቃል ምጋቤምላሹ እየደረሰ መሆኑን ዘወትር ወይም ቀን በቀን እያረጋገጡ መስጠት ይገባል። ይህ ካልሆነ ምጋቤምላሹ ውጤታማ እንደማይሆን ጥናቱ ያሳያል።

የመጻፍ ክሂል ትምህርትን አቀራረብ በተመለከተ ከከሰንጠረዥ አራት  የቀጠለ በመሆኑ ራሱን የቻለ ቁጥር አልተሰጠውም። የትንተና አቀራረቡን አጭርና ግልፅ ለማድረግ በመከፋፈል ቀርቧል።

| ተ/ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | በጥቂቱ እስማማለሁ | አልስማማም | ድምር |
| | | በመቶኛ | በመቶኛ | በመቶኛ | በመቶኛ | በመቶኛ |
| 5 | መምህራችሁ የጋራ የሆኑትን ስህተቶች ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ያርማሉ? | 7.27 | 7.27 | 45.45 | 40 | 100 |
| 6 | የቃላት መረጣ፣ ስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም፣ ዓረፍተነገር አወቃቀር እና ለሌሎችም ትኩረት ሰጥጣችሁ እንድትፅፉ ይነግሯችኂል። | 58.18 | 18.18 | 10.9 | 12.72 | 100 |
| 7 | ስነ ልቦናዊና ማህበራዊ ይዘት ያላቸው ፅሁፎችን ያጽፏችኂል። | 14.54 | 5.45 | 30.9 | 49.09 | 100 |
| 8 | መምህራችሁ ፅሁፋችሁን ርስ በእርስ እንድትተያዩና እንድታቀርቡት ካደረጉ በኂላ ምጋቤምላሽ ይሰጧችኂል። | 30.9 | 36.36 | 16.36 | 16.36 | 100 |

ጥያቄ ቁጥር 5 ን በተመለከተ በጣም እስማማለሁ 7.27 ከመቶ፣ እስማማለሁ 7.27 ከመቶ፣ በጥቂቱ እስማማለሁ 45.45 ከመቶ እንዲሁም ያልተስማሙ 40 ከመቶ ናቸው። ይህም

የሚያሳየው ተማሪዎች የፃፏቸው ፅሁፎች ከታዩ በኂላ የጋራ የሚያደርጓቸውን ወይም ብዙሃኑ ማስተካከል የሚጠበቅበትን ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ምጋቤምላሽ መሰጠት እንዳለበት የሚያሳይ ነው፡፡ ምክንያቱም 40 ከመቶ የሚሆኑት ይህ ተግባር እንደማይከናወን መረጃ በመስጠታቸው ነው፡፡ጥናቱም በቃል ከተነገራቸው በኂላ ሰሌዳ ላይ በፅሁፍ ተፅፈው ቢቀርቡላቸው የተሻለ መሆኑን ያሳያል፡፡

ጥያቄ ቁጥር 6 የመፃፍ ልምምድ ሲደረግ መነሻ ሃሳብ መፈለግ፣ የቃላት መረጣ፣ ስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም፣ የአረፍተነገር አሰካክ (አወቃቀር) እና ሌሎችም ጉዳዮች ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም መምህራን እነዚህን ጉዳዮች መሰረት አድርገው መፃፍ እንዳለባቸው የሚያሳስቡ መሆኑን በጣም እስማማለሁ እና እስማማለሁ በድምሩ 76.36 ከመቶ የሚሆኑት መልስ የሰጡ ናቸው፡፡ በከፊል የተስማሙት 10.9 ከመቶ ሲሆኑ በጭራሽ ያልተስማሙት ደግሞ 12.72 ከመቶ ይሆናሉ፡፡ በተወሰነ መልኩ የተስማሙትና ምንም ያልተስማሙት ግን ችግራቸው እንዲቀረፍ መፃፍ ሲታሰብ መታሰብ ያለባቸው ነጥቦች የመጻፍ ትዕዛዙ ከመተላለፉ በፊት ሰሌዳ ላይ ተፅፈው ታሳቢ ማድረግ እንዲችሉ ቢደረግ ሁሉም ተማሪዎች እያሰቡ እንዲፅፉ ያደርጋል፡፡

ጥያቄ ቁጥር 7 በጣም እስማማለሁ 14.54%፣ እስማማለሁ 5.45%፣ በጥቂቱ እስማማለሁ 30.9% እና አልስማማም 49.09% ናቸው፡፡ ስሌቱ እንደሚያሳየው ተማሪዎች የሚፅፏቸው ፅሁፎች ስነልቦናዊና ማህበራዊ ይዘት ያላቸውን ፅሁፎች እንደሚያፅፏቸውና እንደማያፅፏቸው ለማወቅ የቀረበ ነው፡፡ በመሆኑም ያልተስማሙት ብዙውን ቁጥር የያዙ ሆነዋል፡፡ ለብዙ ጊዜ መፃፍ እንዲለማመዱ ይደረግና ያሰናዱት ፅሁፍ ግን ከየትኛው ይዘት እንደሚመደብ አለመገፁ (አለመነገሩ) ክፍተት ያመጣል፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት ተማሪዎች የሚፅፏቸው ፅሁፎች ሁሉ ማህበራዊ፣ ስነልቦናዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ በማለት መፈረጅ ይገባል፡፡ የትረካ ዓይነታቸውንም (ገላጭ፣ ስዕላዊ ወይም ምስላዊ፣ ተራኪ እና አመዛዛኝ) በማለት መመደብ የተፃፈው ፅሁፍ ምን ዓይነት ይዘት እንዳለውና ከየትኛው የድርሰት ዓይነት እንደሚመደብ ለማወቅ ይረዳል፡፡

ጥያቄ ቁጥር 8 ን ሰንጠረዡ ላይ መመልከት እንደሚቻለው በጣም እስማማለሁ 30.9 ከመቶ፣ እስማማለሁ 36.36 ከመቶ፣ በጥቂቱ እስማማለሁ 16.36 ከመቶ እና አልስማማም 16.36 ከመቶ ናቸው፡፡ ይህ ጥያቄ የጓደኛ (የብጤ) እርማትን የተመለከተ ነው፡፡ ሁልጊዜ ባይሆንም አልፎ አልፎ እርስ በርስ እንዲተራረሙ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ በመሆኑም 67.36 ከመቶ

የሚሆኑት ይህ ተግባር ክፍል ውስጥ እንደሚከናወን ነው፡፡ በጥቂቱ የተስማሙትና በጭራሽ ያልተስማሙት 32.72 ከመቶ የሚሆነውን ይዘዋል፡፡ ይህም የተማሪዎች አቀማመጥ ሁኔታና ስምምነታቸውን መፈተሽ እንደሚገባ ያሳያል፡፡ ምክንያቱም ዝቅተኛ ውጤት አስመዝጋቢ ተማሪዎች አንድ አካባቢ የሚቀመጡ ከሆነ እርስ በርስ ለመተራረም አስቸጋሪ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ስምሙ ካልሆኑም ተግባሩን ማስሄድ ከባድ ሊሆን ስለሚችል ተማሪዎችን ማንበብና አቀማመጣቸውን ቅድሚያ ማስተካከል ይገባል፡፡

በአጠቃላይ የመፃፍ ክሂል ትምህርት ሲቀርብ ክፍሉን ማመቻቸትና ዝግጁ ማድረግ፣ ህፀፆችን በቃል እና በፅሁፍ እየተከታተሉ መስጠት፣ የእርስ በርስ እርማትን ተግባራዊ ማድረግ እና ፅሁፎችን በይዘት መመደብ የትምህርቱ አቀራረብ የተሳካ እንዲሆን እንደሚያስችሉ ያየንበት ነው፡፡

**ሰንጠረዥ 3፡- የምጋቤምላሽ ዓይነቶች በተመለከተ**

| ተ/ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማለሁ | እስማ ማለሁ | በጥቂቱ እስማማለሁ | አልስማማም | ድምር |
| | | በመቶኛ | በመቶኛ | በመቶኛ | በመቶኛ | በመቶኛ |
| 1 | በትዕዛዝ መልኩ ምጋቤምላሽ ይሰጡኛል፡፡ | 18.18 | 25.45 | 30.9 | 25.45 | 100 |
| 2 | አጠናካሪ በሆነ መንገድ ምጋቤምላሽ ይሰጡኛል፡፡ | 27.27 | 16.3 | 41.81 | 14.54 | 100 |
| 3 | ግምገማ ወይም ትችት በሚመስል ሁኔታ ምጋቤምላሽ አሳይተውኝ ያውቃሉ፡፡ | 92.72 | 3.63 | 3.63 | - | 100 |
| 4 | የሚሰጠኝን አስተካካይ ምጋቤምላሽ ጊዜ ሳልወስድ አርማለሁ፡፡ | 56.36 | 21.81 | 10.9 | 10.9 | 100 |

ከምጋቤምላሽ ዓይነቶች አንፃር የቀረቡ ጥያቄዎች ተተንትነው የቀረቡበት ክፍል ነው፡፡ በዚህ መሰረት ጥያቄ ቁጥር 1 ን ከሰንጠረዥ አምስት መመልከት እንደሚቻለው በጣም እስማማለሁ 18.18 ከመቶ፣ እስማማለሁ 25.45 ከመቶ፣ በጥቂቱ እስማማለሁ 30.9 ከመቶ እና አልስማማም 25.45 ከመቶ ናቸው፡፡ ከዚህ መረጃ መረዳት የተቻለውም ትዕዛዝ እንደመሆኑ

መጠን እነዚህን ነገሮች አድርጉ እነዚህን ደግሞ አታድርጉ በማለት ትዕዛዙ ይቀርባል፡፡ የሚባሉትን በትክክል የሚያደርጉትም 43.63 ከመቶ ብቻ ናቸው፡፡ 25.45 ከመቶ የሚሆኑት ግን አልስማማም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በመሆኑም ትዕዛዛዊ ምጋቤምላሽ መቼ መስጠት እንዳለበት እሳቤ ውስጥ በማስገባት እንደሁኔታው በትዕዛዝ መልኩ ምጋቤምላሽ መስጠት እንዳለበት ጥናቱ አመላካች ነው፡፡

ተራ ቁጥር 2 ሰንጠረዥ አምስት ላይ የቀረበውን ስሌት ገለፃ መመልከት እንደሚቻለው በጣም እስማማለሁ 27.27 ከመቶ፣ እስማማለሁ 16.3 ከመቶ፣ በትቂቱ እስማማለሁ 41.81 ከመቶ እና አልስማማም 14.54 ከመቶ መሆኑ ተገልጿል፡፡ በዚህ መረጃ መሰረትም አልስማማም በማለት የመለሱት 14.54 ከመቶ ብቻ በመሆናቸው ተማሪዎች ፅሁፎችን ካሰናዱ በኋላ ጽሁፋቸውን ሊያጠናክሩ የሚችሉ ምጋቤምላሾች በትክክል እንደማይወስዱ ከመረጃው መገንዘብ ተችሏል፡፡ ፅሁፍ ሲዘጋጅ በባህሪው ድግግሞሽን የሚሻ በመሆኑና በሌሎች አካላትም መታየት የሚፈልግ ስለሆነ አጠናካሪ ምጋቤምላሾች ያስፈልጋሉ፡፡ ትልቁን ሚና የሚወስዱትም መምህራን ናቸው፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች የሚገኙበትን ደረጃ ለማወቅ ስለሚረዳቸው ጽሁፎችን በራሳቸው እንዲፅፉ ካደረጉ በኋላ ለሁሉም ተማሪዎች አጠናካሪ ምጋቤምላሾችን መስጠት ተገቢነት እንዳለው ይህ ጥናት ጠቁሟል፡፡

ጥያቄ ቁጥር 3 ን ሰንጠረዥ አምስት ላይ ማየት እንደሚቻለው 92.72 ከመቶ በጣም እስማማለሁ፣ 3.63 ከመቶ እስማማለሁ፣ 3.63 ከመቶ በጥቂቱ እስማማለሁ በማለት መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ መረዳት የተቻለው የግምገማ ምጋቤምላሽ ክፍል ውስጥ እንደሚሰጥ መግለፃቸውን ያሳያል፡፡ ምክንያቱም አልስማማም የሚል መልስ ከተጠኝዎች መካከል የሰጠ አይስተዋልም፡፡ የተፃፉትን ፅሁፎች መገምገም የሰራውን ስህተት ለመለየትና ወደፊት እንዳይደገም ስለሚያደርግ ነው፡፡ መምህራን ሁል ጊዜም በተገቢ መልኩ የተማሪዎቻቸውን ጽሁፎች መገምገምና ምጋቤምላሽ መስጠት አስፈላጊ ነሆኑን ጥናቱ ጠቁሟል፡፡

ጥያቄ ቁጥር 4 ን ሰንጠረዥ አምስት መጨረሻ ላይ መመልከት እንደሚቻለው በጣም እስማማለሁ 56.36 ከመቶ፣ እስማማለሁ 21.81 ከመቶ፣ በጥቂቱ እስማማለሁ 10.9 ከመቶ እና አልስማማም 10.9 ከመቶ መመለሳቸው ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ መረጃ መገንዘብ የሚቻለው 78.17 ከመቶ የሚሆኑት በቀረበላቸው ጥያቄ በትክክል የተስማሙ መሆናቸው ነው፡፡ ለመቶው 10.9% የሚሆኑት ደግሞ አንስማማም በማለት መልሰዋል፡፡ በመሆኑም የማስተካከያ ምጋቤምላሻቸውን እየተከታተሉ መውሰድ ያልቻሉት መሆናቸውን መረዳት ይቻላል፡፡

ምክንያቱም ከላይ የቀረቡት መውሰዳቸውን ከገለፁ እነዚህ አለመውሰዳቸውን ገላጭ በመሆኑ ነው፡፡ ከዚህ በመነሳትም ጥናቱ በፅሁፎቻቸው ላይ የሚሰጧቸውን የማስተካከያ ምጋቤምላሾች መውሰድ እንዳለባቸው ይጠቁማል፡፡ ይህን ለማድረግም መምህሩ የራሳቸውን መንገድ (ስልት) በመጠቀም ምጋቤምላሹን መውሰድ አለመውሰዳቸውን ማረጋገጥ እንዳለባቸው አመላክቷል፡፡

በአጠቃላይ መምህራን የእያንዳንዱን ምጋቤምላሽ ዓይነቶች ጠቀሜታ እሳቤ ውስጥ በማስገባት አገልግሎት ላይ መዋል እንዳለባቸው በማሰብ እንዳስፈላጊነታቸው እየቀያየሩ እና አንዱን ከሌላው እያጣመሩ መገልገል ያለባቸው መሆኑን ጥናቱ ያስገነዝባል፡፡

**ሰንጠረዥ 4፡- የምጋቤምላሽ መስጫ መንገዶችን በተመለከተ**

| ተ/ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | በጥቂቱ እስማማለሁ | አልስማ ማም | ድምር |
| | | በመቶኛ | በመቶኛ | በመቶኛ | በመቶኛ | በመቶኛ |
| 1 | መምህራችሁ አንዳንድ ጊዜ በቪዲዮ ወይም ምስል ምጋቤምላሽ ይሰጣሉ፡፡ | 9.09 | 5.45 | 20 | 65.45 | 100 |
| 2 | መምህራችሁ በቃል ብቻ ምጋቤምላሽ የሚሰጡበት ጊዜ አለ፡፡ | 72.72 | 9.09 | 9.09 | 9.09 | 100 |
| 3 | ቃላዊ እና ፅሁፋዊ ምጋቤምላሾችን በአንድ ጊዜ የሚጠቀሙበት ጊዜ አለ፡፡ | 67.27 | 10.9 | 18.18 | 3.63 | 100 |

በምዕራፍ ሁለት የተዛማጅ ፅሁፎች ክለሳ የምጋቤምላሽ መስጫ መንገዶች ቃላዊ፣ ጽሁፋዊ፣ ይዘታዊ፣ ቅርጻዊ፣ አዎንታዊ እና አሉታዊ ምጋቤምላሽ መሆናቸው ተብራርቶ ቀርቧል፡፡ ከእነዚህ አንፃር የተጠቁ ጥያቄዎች ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

ሰንጠረዥ ስድስት ጥያቄ ቁጥር 1 ን በተመለከተ እንደሚያሳየው በጣም እስማማለሁ 9.09 ከመቶ፣ እስማማለሁ 5.45 ከመቶ፣ በጥቂቱ እስማማለሁ 29 ከመቶ እንዲሁም አልስማማም 65.45 ከመቶ መሆናቸው የተገለፀ ሲሆን ከመረጃው መገንዘብ እንደሚቻለው አልስማማም በማለት የመለሱት ሰፊውን ቁጥር ይዘዋል፡፡ በመሆኑም መምህራን ለዕይታ በሚያመች መልኩ የምስል ወይም የቪዲዮ የተደገፈ ምጋቤምላሽ በብዛት እንደማይሰጡ ነው፡፡ ነገር ግን ተማሪዎች በድምፅ፣ ምስልና ቪዲዮዎችን ድጋፍ በማድረግ ምጋቤምላሽ ቢሰጥ የበለጠ የሚሰጠው ምጋቤምላሽ የማይረሳ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

ጥያቄ ቁጥር 2 ን ሰንጠረዥ ስድስት ላይ ማስተዋል እንደሚቻለው መምህራን በቃል ብቻ ምጋቤምላሽ የሚሰጡበት ጊዜ መኖር አለመኖሩን ለቀረበላቸው ጥያቄ በጣም እስማማለሁ በሚል የመለሱ 72.72 ከመቶ፣ እስማማለሁ 9.09 ከመቶ፣ በጥቂቱ እስማማለሁ 9.09 ከመቶ እና በጭራሽ አልስማማም 9.09 ናቸው፡፡ በዚህ መረጃ መሰረት አንድን ዓይነት መንገድ በመከተል ምጋቤምላሽ መስጠት ውጤታማ ስለማያደርግ አንዳንድ ጊዜ በቃል፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ በቃልና ፅሁፍ አልፎ አልፎም በፅሁፍ ብቻ የሚሰጥበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ ለተጠየቁትም 72.72 ከመቶ የሚሆኑት በቃል ብቻ ምጋቤምላሽ እንደሚሰጣቸው ገልፀዋል፡፡ 9.09 ከመቶ የሚሆኑት ደግሞ አንስማማም በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ይህ የሚሆነው አንዳንድ ተማሪዎች መምህራን ክፍል ውስጥ የሚያደርጉትን ተግባር በትክክል የማያስተውሉ ሊኖሩ ስለሚችሉ በዚህ ምክንያት የመጣ ውጤት ሊሆን ይችላል፡፡ ዋናው ግን መምህራን ለተማሪዎቻቸው ቃላዊ በሆነ መንገድ ምጋቤምላሽ ሊሰጡ መሆናቸውን በማሳሰብ እንዲከታተሉ አንቅቶ መጀመር የተሻለ እንደሆነ ጥናቱ ይጠቁማል፡፡

ጥያቄ ቁጥር 3 ላይ የተጠየቀው ቃላዊና ጽሁፋዊ መንገድን በመከተል መምህራን ምጋቤምላሽ መስጠታቸውን ለማረጋገጥ የቀረበ ነው፡፡ በዚህ መሰረት በጣም እስማማለሁ 67.27 ከመቶ፣ እስማማለሁ 10.9 ከመቶ፣ በጥቂቱ እስማማለሁ 18.18 ከመቶ እንዲሁም አልስማማም 3.63 ከመቶ ናቸው፡፡ ከዚህ መረጃ በመነሳት ከምጋቤምላሽ መስጫ መንገዶች መካከል ሁለቱን በአንድ ላይ እያጣመሩ ምጋቤምላሽ መስጠት ይጠቀሳል፡፡ እያጣመሩ መጠቀም በቃል ገለፃ ግልፅ ያልሆነላቸው በጽሁፍ፣ በጽሁፍ ያልተገለጠላቸው ደግሞ በቃልግልፅ ሊሆንላቸው ስለሚችል 78.17 ከመቶ የሚሆኑት መምራቸው እያጣመሩ መጠቀማቸውን የገለፁ ሲሆን 3.63 ከመቶ የሚሆኑት አንስማማም በማለት መልሰዋል፡፡ ከመረጃው መገንዘብ እንደሚቻለው መምህራን አስፈላጊ በሆነበት ስዓት ብቻ ሁለቱን መንገዶች አጣምረው እንደሚጠቀሙ ነው፡፡ ጥናቱም በማንኛውም ዘወትራዊ ተግባር እና አስፈላጊ በሚሆንበት ወቅት የቃልና ጽሁፍ ምጋቤምላሾችን በማቅረብ ለተማሪዎች የመጻፍ ክሂል እድገት በመሆኑ ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት መሆኑን አመልካች ነው፡፡

በአጠቃላይ በቃል፣ በጽሁፍ እና በቃልና በጽሁፍ ከሦስቱ በአንዱ መንገድ ምጋቤምላሽ መስጠት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ሰንጠረዡ እንደሚያስመለክተው በተሻለ መልኩ እየተሰራበት ያለው በቃል ብቻ ምጋቤምላሽ የመስጠቱ ሂደት ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ በቃልና በጽሁፍ ምጋቤምላሽ እንደሚሰጥ ሰንጠረዡ ያስመለክታል፡፡ ሦስቱንም መንገድ እየቀያየርን መጠቀም ፍሬያማ ለመሆን እንደሚያስችል ይህ ጥናት ይጠቁማል፡፡

**ሰንጠረዥ 5፦ ምጋቤምላሽ ሊሰጡ የሚችሉ አካላትን በተመለከተ**

| ተ/ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | በጥቂቱ እስማማለሁ | አልስማማም | ድምር |
| | | በመቶኛ | በመቶኛ | በመቶኛ | በመቶኛ | በመቶኛ |
| 1 | መምህራችሁ ከተነበበ በኋላ የራስን ስህተት ፈልጎ ማውጣት እንደሚቻል አሳይተው ያውቃሉ፡፡ | 21.81 | 25.45 | 34.54 | 18.18 | 100 |
| 2 | መምህራችሁ እርስ በርስ በመተያየት ስህተቶችን እንድታርሙ ያደርጋሉ፡፡ | 43.63 | 9.09 | 12.72 | 34.54 | 100 |
| 3 | መምህራችሁ ራሳቸው ምጋቤምላሾችን እንዳስፈላጊነቱ ይሰጣሉ፡፡ | 27.27 | 45.45 | 16.36 | 10.9 | 100 |

በምዕራፍ ሁለት የተዛማጅ ፅሁፎች ክለሳ ስርምጋቤምላሽ ሊሰጡ የሚችሉ አካላት በግልፅ ተብራርተው ቀርበዋል፡፡ በመሆኑም ከላይ በቀረበው የሰንጠረዥ ‘ሠ’ስር ሦስት መሰረታዊ ጥያቄዎች ተጠይቀው የተገኘው መረጃ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

ጥያቄ ቁጥር 1 ን ሰንጠረዥ ሰባት መጀመሪያ ላይ ይገኛል፡፡ መምህራችሁ ምንባቡ ከተነበበ በኋላ የራስን ስህተት ፈልጎ ማውጣት እንደሚቻል አሳይተው ማወቅና አለማወቃቸውን የሚያጠይቅ ነው፡፡ በመሆኑም በጣም እስማማለሁ 21.81 ከመቶ፣ እስማማለሁ 25.45 ከመቶ፣ በጥቂቱ እስማማለሁ 34.54 ከመቶ እና አልስማማም 18.18 ከመቶ ናቸው፡፡ በዚህ መሰረት መረጃው እንደሚያስገነዝበው ተማሪዎች በአቅማቸው ልክ ፅሁፎችን እንዲጽፉ ከተደረገ በኋላ የፃፉትን ደጋግመው በማስነበብ የራሳቸውን ስህተት በራሳቸው ፈልገው እንዲያወጡ በማድረግ ምጋቤምላሽ መስጠት ይቻላል፡፡ በዚህ መሰረት በቁጥር ትቂት የማይባሉ ተግባሩ ክፍል ውስጥ እንደሚከናወን የገለፁ ሲሆን 18.18 ከመቶ የሚሆኑት የራስን ስህተት በራስ ፈልጎ ለማስተካከል ከመምህራቸው ትዕዛዝ የሚጠብቁ ይኖራሉ፡፡ ለዚህም ሊሆን ይችላል አንስማማም በማለት የመለሱት፡፡ በመሆኑም የእነዚህን ተማሪዎች ግልፅ ምክንያት ማወቅ ባይቻልም የራስን ስህተት በመፈለግ እንደሚያቀርቡ ከገለፁት ተማሪዎች ጋር ሲነፃፀሩ የመጻፍ ብቃታቸው

ዝቅተኛ ሊሆን እንደሚችል መረዳት ይቻላል። የራስን ፅሁፍ ደጋግሞ ማየትና በራስ ማስተካከል እንደሚገባ ጥናቱ ይጠቁማል።

ጥያቄ ቁጥር 2 ን በተመረከተ የተገኘው የሰንጠረዥ ሰባት መረጃ እንደሚያሳየው በጣም እስማማለሁ 43.63 ከመቶ፣ እስማማለሁ 9.09 ከመቶ፣ በጥቂቱ እስማማለሁ 12.72 ከመቶ እና 34.54 ከመቶ ነው። ከአቻ ጓደኛ ጋር ወይም እርስ በርስ ምጋቤምላሽ መውሰድ እንደሚቻል የሚያሳይ ሲሆን መምህራን ለተማሪዎቻቸው ማድረጋቸውን አረጋጋጭ በመሆኑ በጣም እስማማለሁና እስማማለሁ በሚል የመለሱ በድምሩ ከግማሽ ፐርሰንት በላይ መሆናቸውን ሰንጠረዡ ያሳያል። ይህም መምህሩ ምንም ድጋፍ ለተማሪዎች ሳያደርጉላቸው ከጓደኞቻቸው ጋር ደጋግመው እያነበቡ እርስ በርስ እንዲተራረሙ እድል ሰጪ ነው። አልስማማም በማለት የመለሱት 34.54 ከመቶ ሲሆኑ ለእነዚህ ተማሪዎች የብጤ ምጋቤምላሽን ምንነትና ጠቀሜታ በተመለከተ ልዩ ግንዛቤ እንዳለበት ጥናቱ ጠቋሚ ነው።

ስለጥያቄ ቁጥር 3 ሰንጠረዡ ላይ እንደቀረበው መረጃ በጣም እስማማለሁ 27.27 ከመቶ፣ እስማማለሁ 45.45 ከመቶ፣ በጥቂቱ እስማማለሁ 16.36 ከመቶ እና አልስማማም 10.9 ከመቶ ነው። ከመረጃው መገንዘብ የሚቻለው ብዙውን ጊዜ መምህራን ብቻ ምጋቤምላሽ እንደሚሰጡ ያሳየ ነው። ምክንያቱም አልስማማም በማለት የመለሱት 10.9 ከመቶ የሚሆኑት ብቻ ናቸው። በብዛት ግን በሚጽፏቸው ጽሁፎች ላይ መምህራን ምጋቤምላሽ እንደሚሰጡ አስገንዛቢ ሆነዋል። ጥናቱ አንስማማም በማለት ለመለሱት መምህራን ምጋቤምላሽ ከመስጠታቸው በፊት ዝግጁ መሆናቸውን መፈተሽ መቻልና በሚሰጡበት ጊዜ ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ ምጋቤምላሹ ለሁሉም ተማሪዎች ተደራሽ እንደሚሆን ይጠቁማል።

በአጠቃላይ ሦስት አካላት ምጋቤምላሽ ሊሰጡ ይችላሉ። ራሱ ጽሁፉን ያዘጋጀው አካል፣ እርስ በርስ እና የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ሲሆኑ ከሦስቱ የበለጠ ጎልቶ የታየው ምጋቤምላሽ ከመምህራቸው ሲወስዱ ነው፤ ነገር ግን የእርስ በርስ እና የራስን ስህተት መፈለግ በመቻል ምጋቤምላሽ መውሰድ እንደሚቻል በመጠቆም የግል (ብጤ)፣ እርስ በርስ (ከጓደኛ ጋር) እና መምህራን ምጋቤምላሽ ማቅረብ ስለሚችሉ እንደክፍሉ ሁኔታ እየቀያየሩ መጠቀም እንደሚቻልና መሰላቸትን ቀራፊ መሆኑን ይህ ጥናት አስገንዛቢ ነው።

## 4.3 ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

የማንበብ ክሂልን በሚያስተምሩበት ወቅት ተማሪዎች ለሚፈጽሟቸው ስህተቶች በምን መልኩ ቃላዊ ምጋቤምላሾችን እንደሚሰጡ ለተጠየቁት መምህራን የሰጡት ምላሽ የተተነተነበት ክፍል ነው፡፡

መምህርት 1፡- "ቃላትን እያነበቡ በማሳየት፣ ደግመው እንዲሉት በማድረግ፣ የተገደፉትን ሌሎች እየተከታተሉ እንዲፅፉ በማድረግና የሰሩት ግድፈት ምንያህል እንደሆኑ በመጠቆም፣ ለአዳዲስ ቃላት ፍቺ በመጠቆም፣ የምዘና እና መፅሃፉ ላይም ሆነ ያዘጋጀኋቸውን የመልመጃ ጥያቄዎች በማሰራት ስለቀረበው ትምህርት አጠቃላይ የቃል ምጋቤምላሽ እሰጣለሁ" የሚል ምላሽ ተሰጥቷል፡፡

መምህር 2፡- "ከሚመልሱት መልስ በመነሳት ማስተካከል፣ የተሳሳቱበትን ቦታ በማሳየት፣ ደጋግመን በማስነበብ፣ የቃላትን አገባብ እየደጋገሙ እንዲረዱት በማድረግ እና አነባበቡን በማሳየት ምጋቤምላሽ እሰጣቸዋለሁ" በማለት ገልፀዋል፡፡

መምህር 3፡- "መጀመሪያ ተራ ቁጥር በመስጠት ማስነበብ፣ በንባብ ወቅት ስህተት የሚሰሩበትን ቦታ መከታተል፣ አንዳንድ ጊዜ እያስቆምሁ ሌላ ጊዜ ደግሞ አጠቃላይ የሰሯቸውን ስህተቶች ጠቅለል አድርጌ በመናገር ምጋቤምላሽ እሰጣለሁ" በሚል ተናግረዋል፡፡

መምህርት 4፡- "ምንባቡን በተመለከተ በንግግር ወይም በቃል ምጋቤምላሽ እሰጣለሁ፡፡ ያየሁባቸውን የንባብ ወቅት ስህተቶች አርማለሁ" ብለዋል፡፡

መምህር 5፡- "ከመካከላቸው የተሻለ አንባቢ አንብቦ እንዲያሳቸው አደርግና መካከለኛ ከዚያም ዝቅተኛ አንባቢዎችን በማድረግ እንደየአቅማቸው ካስነበብሁ በኋላ እንዴት ማንበብ እንዳለባቸው አንብቤ በማሳየት አጠቃላይ የቃል ምጋቤምላሾችን እሰጣለሁ" በማለት ገልፀዋል፡፡

ከመምህራን አባባል የምንረዳው የማንበብ ክሂልን ሲያስተምሩ የቃል ምጋቤምላሾችን ከቃላት ንበትና አገባብ አኳያ አጣጥመው እንዲያነቡ በማድረግ፣ አንብበው በማሳየት ምጋቤምላሽ እንደሚሰጡ ወይም ተማሪዎች ውስጥ የተሻለ አንባቢ በመምረጥና በማስነበብ ስህተት ሲነበብ እንዳይኖር ጥረት እንደሚደረግ ያሳየ ነው፡፡ በአጠቃላይ የንባብ ተግባሩ ከመጠናቀቁ በፊትና እንዳለቀ ቃላዊ በሆነ መልኩ ምጋቤምላሽ እንደሚሰጡ ነው፡፡

ንባብካስነበቡ በኋላ የፅሁፍ ምጋቤምላሽ መስጠት አለመስጠታቸውን ለተጠየቁት መምራን የሰጡት ምላሽ ቀርቧል፡፡

መምህርት 1፡- አዎ! "ምንባቡን ካስነበብሁ በኂላ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን በማሰራትና ምንባቡን የተመለከቱ የክፍል ስራዎችን በመስጠት እንዲሰሩ ካደረግሁ በኂላ ጥቁር ሰሌዳ ላይ ምጋቤላሾችን እፅፍላቸዋለሁ፤ በዚያ መልኩ እርማት ይወስዳሉ" በማለት ገልፀዋል፡፡

መምህር 2፡- "ምንባብ አስነብቤ በፅሁፍ ምጋቤምላሽ አልሰጥም፣ ምክንቱም የማንበብ ክሂልን ሳስተምር የቃል ስራዎች ላይ ነው ትኩረት የማደርግ" ብለዋል፡፡

መምህር 3፡- "ሲያነቡ የሳቷቸው አዳዲስ ቃላት ከሆኑ ፅፌ ደግመው እንዲሉት በማድረግ የምጠቀምበትም፣ የምልፅፍበትም ጊዜ አለ" ብለዋል፡፡

መምህርት 4፡- "የሰሯቸውን ስህተቶች ራሳቸው እንዲፅፉ አደርጋለሁ እንጂ እኔ አልፅፍም፤ ምክንያቱም በራሳቸው ጥረት ማድረግን እንዲለምዱ ነው የማግዛቸው፡፡ ይህንን ካደረግሁ በኂላም ቢሆን ተጨማሪ ነገሮችን በቃል ነው ልነግራቸው የምችለው" በማለት ተናግረዋል፡፡

መምህር 5፡- "በሚያነቡበት ጊዜ እያስቆምሁ ችግራቸውን እያስተካከልሁ ስለምሄድ ስህቶቻቸውን በፅሁፍ ማሳየት ጊዜ ወሳጅ ሲሆን ይችላል" በማለት መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

በአጠቃላይ መምህራን ከሰጡት ምላሽ መውሰድ የተቻለው የማንበብ ክሂል ትምህርት ሲቀርብ ለተማሪዎች መድረስ የሚኖርባቸው ምጋቤምላሾች በቃልም ሆነ በፅሁፍ እንደሚያቀርቡ ነው፡፡ ከመምህራን ሃሳቦች መመልከት እንደሚቻለውም በምንበብ ክሂል ጊዜ የጽሁፍ ምጋቤምላሽ አያስፈልግም ያሉ ተስተውለዋል፡፡ ጥናቱ የክሂል ትምህርቱ ሲቀርብ ተማሪዎች የሚታዩባቸው ስህተቶች ከቃል ባለፈ ደብተራቸው ወይም ሰሌዳ ላይ እየተፃፉ ቢቀርቡላቸው የተሻለ መሆኑን ያሳያል፡፡

በምዕራፍ ሁለት የተዛማጅ ድርሳናት ክለሳ ክፍል እንደቀረቡት ምጋቤምላሽ ሲሰጡ የትኛውን ምጋቤምላሽ ዓይነት (ገምጋሚ፣ ትዕዛዛዊ፣ አጠናካሪና አስተካካይ) እንደሚጠቀሙ፣ ተመራጭ የሆነበትን መንገድና የምጋቤምላሽ ዓይነቶችን በመቀያየር መጠቀም አለመጠቀማቸውን እንዲገልፁ ለተጠየቋቸው ያቀረቡት መልስ ተተንትኗል፡፡

መምህርት 1፡- "የምጋቤምላሽ ዓይነቶችን እንደአስፈላጊነታቸው እጠቀማለሁ፡፡ የሚነገራቸውን የማያስተካክሉ ተማሪዎች ሲገጥሙኝ ትዕዛዛዊ በሆነ መንገድ እንዲያስተካክሉ እማደርግበትም ጊዜ አለ፣ አልያ ግን ሁሉንም እየቀያየርሁ እጠቀማለሁ" በማለት ገልፀዋል፡፡

መምህር 2፡- "አብዛኛውን ጊዜ የምጠቀማቸው አጠናካሪና አስተካካይ ምጋቤምላሾችን ነው፤ ምክንያቱም የተስተካከለ ንባብ እንዲያደርጉና የፃፉትን እንደገና አስተካክለው እንዲፅፉ የሚያግዙ መሆናቸውን ስለማምን ተመራጭ ናቸው" በማለት ገልፀዋል፡፡

መምህር 3፡- “ሁሉም ዓይነቶች ያስፈልጋሉ፣ የትኛው ነው ተመራጭከተባለ ግን ከትውልዱ የትምህርት ፍላጎትና አቀባበል አንፃር ትዕዛዛዊ ምጋቤምላሽን ተመራጭ አደርገዋለሁ፡፡ ማዘዝ እወዳለሁ፤ ሲያዟቸውና ሲቆጧቸው የበለጠ ተነሳስተው ምጋቤምላሳቸውን ይቀበላሉ” በማለት ገልፀውታል፡፡

መምህርት 4፡- “ብዙውን ጊዜ አስተካካይ ምጋቤምላሽን ተመራጭ በማድረግ እጠቀመዋለሁ” ብለዋል፡፡

መምህር 5፡- “መሰላቸት እንዳይታይባቸው ሁሉንም ለመጠቀም እሞክራለሁ፤ ለአስተካካይ ምጋቤምላሽ ግን ትኩረት እሰጣለሁ” በማለት መልሰዋል፡፡

በአጠቃላይ የመምህራን ምላሽ እንደሚያሳየው ሁሉንም የምጋቤምላሽ ዓይነቶች ተጠቅሞ ምጋቤምላሽ እንደሚሰጡ የገለፁ፣ ለአስተካካይና አጠናካሪ ምጋቤምላሽ ዓይነቶች ትኩረት የሚሰጡ፣ አስተካካይ ምጋቤምላሽን ብቻ የሚጠቀሙ እና ትዕዛዛዊ ምጋቤምላሽን ብቻ በመጠቀም ምጋቤምላሽ የሚሰጡ መኖራቸውን መመልከት ተችሏል፡፡ በመሆኑም እየቀያየሩ እንዳስፈላጊነታቸው መጠቀማቸው መቀጠል የሚኖርበት ቢሆንም ጥቅም ላይ የሚውለው የምጋቤምላሽ ዓይነት ለተማሪዎች የሚኖረውን ምቹነት ማሰብና ሁሉንም አንድ ላይ በመጠቀም ምጋቤምላሽ ዓይነት አገልግሎት ላይ ለማዋል ሲባል የጊዜውን ሁኔታና መሰላቸት እንዳይፈጥር በትኩረት ማሰብ እንደሚገባ ጥናቱ ይጠቁማል፡፡

የመፃፍ ክሂል ላይ ምጋቤምላሽ ሲሰጡ ትኩረት የሚያደርጓቸውን ነጥቦች እንዲገልፁ ለተጠየቁት ያቀረቡትን ምጋቤምላሽ በሚከተለው መልኩ መተንተን ተችሏል፡፡

መምህርት 1፡- “አንቀፅ ሳጽፉቸው የአንቀፅ ቅርፅ መጠበቃቸውን፣ ዓረፍተነገር ስርዓቱን፣ ስርዓተ ነጥብና አጨራረሱ ላይ በይበልጥ ጥንቃቄ ማድረጋቸውን ካየሁ በኋላ ምጋቤምላሽ እሰጣለሁ” ብለዋል፡፡

መምህር 2፡- “አንቀፅ ከሆነ ነጠላ መልዕክት መያዙን፣ የራሳቸውን ሃሳብ ለመግለፅ መሞከራቸውን፣ ስርዓተ ነጥብ አጠቃቀማቸውን፣ ከርዕስ አለመውጣታቸውን እና የመሳሰሉት ላይ ትኩረት አድርጌ ምጋቤምላሽ እሰጣለሁ” በማለት ገልፀዋል፡፡

መምህር 3፡- “መስመር መጠበቃቸውን፣ መስፈርት ተሰጧቸው ከሆነም መጠበቃቸውን፣ ስርዓተ ነጥብ፣ ቃላት አጠቃቀም እና የጽሁፉን አጀማመርና አጨራረሱ ምን እንደሚመስል ትኩረት በማድረግ ምጋቤምላሽ እሰጣለሁ” ብለዋል፡፡

መምህርት 4፡- “የጻፍትን ነገር ተገቢነት፣ ቅርጽ፣ የይዘት አቀራረብ የመሳሰሉት ላይ ተነስቸ ለፅሁፋቸው ምጋቤምላሽ ለመስጠት እሞክራለሁ” ብለዋል፡፡

መምህር 5፡- “የጻፉት ጽሁፍ አስተማሪ መሆን አለመሆኑን፣ የአፃፃፍ ስልቱን፣ ቅርፁን፣ ስርዓተ ነጥብ፣ ምጥን ያለ (ያልተንዛዛ) መሆኑን እና አወቃቀሩ ላይ ትኩረት አድርጌ ምጋቤምላሽ አቀርባለሁ” በሚል መግለፅ ችለዋል፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ከመምህራን ምላሽ ማስተዋል የተቻለው የመፃፍ ክሂልን አስተምረው በሚያለማምዱበት ወቅት መምህራን ምጋቤምላሽ ሲሰጡ ከበርካታ ነጥቦች አንፃር ምጋቤምላሽ እንደሚሰጡ መገንዘብ ተችሏል፡፡ ይህ መሆኑም ተማሪዎች ለሚጽፏቸው ጽሁፎች በቂ ምጋቤምላሽ እንደሚያገኙ አመላካች መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡ ይህ ጥናት የሚመርጡትን ርዕስ ተገቢነት፣ ሀሳብ አጀማመርና ፍሰት፣ ሂደት መጠበቁን፣ አጨራረሱን በቅደም ተከተል ከታየላቸው በኂላ የቃላት አጠቃቀማቸው፣ የስርዓተ ነጥብ፣ የጽሁፍ ተገቢነት፣ የይዘት ሁኔታው፣ ትኩረት ሰጥተው መፃፋቸውና ሌሎችም በቅደም ተከተል (ከአነሳስ እስከ ፍፃሜ) ያለውን ለእያንዳንዱ በጽሁፍ ምጋቤምላሽ መስጠትና እንደገና ለሁሉም ተማሪዎች ጠቅለል ያሉ ሀሳቦችን በማንሳት አጠንክረው ምጋቤምላሽ መስጠት የመጻፍ ችሎታቸው እንዲጎለብት የሚያደርግ በመሆኑ ትኩረት እንዲሰት የሚያሳይ ነው፡፡

መምህራን ጽሁፋዊ ምጋቤምላሽ መቼ እንደሚሰጡ ለተጠየቁት የሰጡትን መልስ ተንትኖ ማቅረብ ተችሏል፡፡

መምህርት 1፡- “የመጻፍ ክሂልን በማስተምርበትና በልምምድ ወቅት ምጋቤምላሽ እሰጣለሁ፡፡”

መምህር 2፡- “እንዲጽፉ የክፍል ወይም የቤት ስራ በምሰጣቸው ጊዜ የሰሩት ከታየ በኂላ ምጋቤምላሽ እሰጣለሁ” በሚል ገልፀዋል፡፡

መምህር 3፡- “ጽፈው ከጨረሱ በኂላ ፅሁፋቸውን በማየት ምጋቤምላሽ እሰጣለሁ” ብለዋል፡፡

መምህርት 4፡- “የጻፍትን አንድ በአንድ ካነበብሁት (ካየሁት) በኂላ ምጋቤምላሽ እሰጣለሁ” በማለት ገልፀዋል፡፡

መምህር 5፡- “የመጻፍን ክሂል ሳስተምር ወይም መጻፍን ሳለማምድ ምጋቤምላሽ እሰጣለሁ” በማለት መልሰዋል፡፡

ጠቅለል ባለ አገላለፅ መምህራን መቼ ምጋቤምላሽ እንደሚሰጡ ለተጠየቁት መፃፍን በሚያስተምሩበትና መጻፍን በሚያለማምዱበት ወቅት እንደሆነ ነው፡፡ በመሆኑም የመጻፍ ትምህረት ቀላል ባለመሆኑ፣ ትምህርቱ የሚሰጥበት ጊዜ ቢወሰንም ልምምዱ ግን በግልም ይሁን ከጓደኛ ጋር መቀጠል ያለበት ስለሆነ፣የመጻፍ ክሂልን ማስተማር ጥንቃቄንና ክትትልን፣ ደጋግሞ ማየትን ስለሚጠይቅ ከሌሎች ይዘቶች በተጓዳኝም ቢሆን ሰፋ ያለ ጊዜ እየተሰጠ የመጻፍ ልምምዱ እና ምጋቤምላሹ ሳይቋረጥ መቀጠል እንዳለበት ጥናቱ ይጠቁማል፡፡

መምህራን የማንበብና መጻፍ ክሂሎችን ሲያስተምሩ ሳይሰለቹ ለሁሉም ተማሪዎች ምጋቤምላሽ እንደሚሰጡና አድካሚነቱን እንዲገልፁ ለተጠየቁት ያቀረቡትን መልስ ተንትኖ ማቅረብ የተቻለበት ንዑስ ክፍል ቀርቧል፡፡

መምህርት 1፡- "ሰው ነኝ፤ መሰልቸት ይኖራል፤ ግን እስከምችል ድረስ ወይም አቅሜ እስከሚፈቅድ ምጋቤምላሽ እሰጣለሁ" ብለዋል፡፡

መምህር 2፡- "እንዳልሰለች ሆኘ ለክፍሉ እቀርባለሁ" ብለዋል፡፡

መምህር 3፡- "ስራ ሲበዛ የማይሰለችና የማይደክም የለም፤ ተቋቁሜ ምጋቤምላሽ ለመስጠት እሞክራለሁ" ብለዋል፡፡

መምህርት 4፡- "ተማሪዎች ካልደከሙ መሰልቸት የሚባል ታይቶብኝ አያውቅም" በሚል ጠንከር ያለ ምላሻቸውን ሰጥተዋል

መምህር 5፡- "ማንበብን ሳስተምርና ምጋቤምላሽ ስሰጥ አይደክመኝም የመጻፍ ክሂልን ሳለማምድ ግን ይደክመኛል፤ ቢሆንም ተማሪዎች ደግሞ እንዳይጎዱ ስለማስብ ለመቋቋም በመሞከር ምጋኔምላሹን እሰጣቸዋለሁ" ብለዋል፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ በተደጋጋሚ የገለፁት አድካሚና አሰልቺ መሆኑን ሲሆን እየተቋቀዋሙ ትምህርቱን በትክክል እንደሚያደርሱ ጠቁመዋል፡፡ ምንም ዓይነት መሰላቸትና ድካም የማይታቻቸው መሆኑን የገለፁም አሉ፡፡ ይህ ደግሞ የሚያሳየው የበለጠ ድካም እንደሚኖረው ቀድሞ በመገንዘብ በጥንካሬ አሸንፎ በመቅረብ የማንበብና መጻፍ ክሂሎችን እንደሚያስተምሩና ምጋቤምላሹን ሳይሰለቹ እንደሚሰጡ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት የሚያመለክተው የስራ ላይ ድካም ሊኖር እንደሚችል ማሰብ ሳይሆን ምንም ዓይነት የመድከም ስሜት ሳይኖር የማንበብና መፃፍ ክሂሎችን በብቃት በማስተማር አቀላጥፎ የማንበብ ችሎታን እና አቅማቸውን መጣኝ የሆኑ ፅሁፎችን መጻፍ እንዲችሉ ማድረግ ይገባል፡፡ ምክንያቱም የመምህራን ጥንካሬ ሊገለፅ የሚችለው በተማሪው ችሎታና ውጤት ልክ ስለሚሆን ድካምን ማሰብ በራሱ ውድቀት መሆኑን ጥናቱ ያሳያል፡፡

መምህራን በምጋቤምላሽ አሰጣጥ ወቅት ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ነገሮች እንዲገልፁ ለተጠየቁት የሰጡት ምጋቤምላሽ ተተንትኗል፡፡

መምህርት 1፡- "ተደጋጋሚ እንዲያነቡና እንዲፅፉ ሳደርግ መሰላቸት ይታይባቸዋል"የሚልሃሳብ ሰጥተዋል፡፡

መምህር 2፡- "ለሁሉም ተማሪዎች ምጋቤምላሽ ለመስጠት ስዓት ማነስ አንዱ ተፅዕኖ ነው"በሚል ሀሳባቸውን ገልፀዋል፡፡

መምህር 3፡- "የአንዳንድ ተማሪዎች ንቁ የሆነ የመማር ፍላጎት አለመኖር ትልቁ ችግር ነው"በሚል አቅርበውታል፡፡

መምህርት 4፡- "የስራ መብዛት (መደራረብ) የሚያመጣው ድካም ለእኔ ትልቅ ችግር ነው"በማለት ተናግረዋል፡፡

መምህር 5፡- "የተማዎች ፍላጎት ዝቅተኛ መሆን" የሚልሃሳብ አስቀምጠዋል፡፡"

ጠቅለል ባለ መልኩ መምህራን ምጋቤምላሽ በሚሰጡበት ወቅት ተፅዕኖ እንደሚያደርጉባቸው የስራ መደራረብ፣ የተማሪዎች ፍላጎት፣ የሰዓት ማነስ እና መሰላቸት የሚሉት በዋናነት ተጠቅሰዋል፡፡ በመሆኑም መምህራን በተደጋጋሚ እነዚህን ችግሮች የሚያስተውሉ ከሆነ መጀመሪያ ችግሮችን እንዲፈቱ ካላገረጉ የሚቀርበው ትምህርትና ምጋቤምላሽ ፍሬ እንደማይኖረው በመረዳት መፍትሔ መውሰድ እንደሚያስፈልጋቸው ያመለክታል፡፡ መፍትሔ ሊሆኗቸው የሚችሉትም በማነቃቃት (በአዝናኖት) መጀመር፣ ለተማሪዎች አዎንታዊ ንግግሮችን በመናገር፣ ለተማሪዎች እድሎችን በማመቻቸት ችሎታቸውን እንዲያሳዩ በማድረግ፣ የእረፍት ስዓታቸው ላይ የተመረጡ አዝናኝና አስተማሪ ምንባቦችን እና የሚፅፏቸውን አጫጭር ፅሁፎች እንዲያደርቡ በማድረግና በመሳሰሉት መንገዶች የቋንቋ ትምህርቱን በተለይም የማንበብና መፃፍ ክሂሎችን ወደዋቸው እንዲማሩ ማድረግ እንደሚቻል ጥናቱ ጠቋሚ ነው፡፡

ክለሳ ማድረግ ከምጋቤምላሽ አቀራረብ ጋር ግንኙነት መኖር አለመኖሩን ለተጠየቁት የሰጡትን ምጋቤምላሽ ተንትኖ ለማቅረብ የተቻለበት ክፍል ነው፡፡

መምህርት 1፡- "ክለሳ ማድረግ እና ምጋቤምላሽ መስጠት ለእኔ ልዩነት አላቸው፡፡ መከለስ ይዘቱን ነው፡፡ ምጋቤምላሽ ደግሞ እርማት መስጠት ነው፡፡ ምናልባት ግን የክለሳ ጥያቄዎችን ከሰሩ በኋላ ምጋቤምላሽ የምሰጥበት ጊዜ አለ" በማለት ገልፀዋል፡፡

መምህር 2፡- "ያገናኛቸዋል፤ ምክንያቱም ምጋቤምላሽ የማይሰጥበት ክፍል ስለማይኖር ነው፡፡ አሰጣጡ ሊለያይ ይችላል እንጂ" በማለት መግለፅ ችለዋል፡፡

መምህር 3፡- "በየምዕራፎች የሚገኙትን የክለሳ ጥያቄዎችን ተማሪዎች ከሰሩና መምህራን የሚያደርጉትን የይዘት ክለሳ በምዘና ስልት ተማሪዎችን ከለኩ በኋላ ማስተካከያዎችን ወይንም እርማቶችን ይሰጣሉ፤ በዚህ መልኩ ግንኙነት ይኖራዋል"በማለት ተናግረዋል፡፡

መምህርት 4፡- "ምጋቤምላሽ የክለሳው አካል በመሆኑ ትስስር ያላቸው ይመስለኛል" በሚል ገልፀውታል፡፡

መምህር 5፦ "በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ምጋቤምላሽ የማይሰጥበት ጉዳይ አይኖርም፡፡ ቋንቋ እርማትንና መስተካከልን ይፈልጋል፡፡ ይህ ደግሞ ነገሮችን እንድንከልስ ወይም ደጋግመን እንድናይ ያደርጋልና የጠበቀ ትስስር አላቸው" በማለት ተናግረዋል፡፡

ጠቅለል ባለ አገላለፅ መምህራን በክለሳ ወቅትም ምጋቤምላሽ ሊሰጥ እንደሚችል መግለፅ የቻሉበት ነው፡፡ ካቀረቧቸው ሃሳቦች የምንረዳው መምህራን ክለሳ ካደረጉ በኋላ ምዘና እንደሚኖር ነው፡፡ ከምዘናው በኋላም ምጋቤምላሽ አይቀሬ ይኖናል፡፡ የክለሳ ጥያቄዎችን እንዲሞክሩ ካደረጉ በኋላም ምጋቤምላሽ የማይቀር ነው፡፡ በመሆኑም ያላቸውን ትስስር መረዳት ተገቢ ነው፡፡ ምጋቤምላሽ በእያንዳንዱ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ይዘት ውስጥ ሰፊ ቦታ ያለው ነውና በእያንንዱ ይዘት ውስጥ ከተማሪዎች ተግባር በኋላ ምጋቤምላሽ መኖሩን ጥናቱ ይጠቁማል፡፡

# ምዕራፍ አምስት
# ማጠቃለያና አስተያየት

## 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በምስራቅ ጉራጌ ዞን ኬላ ወረዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን ትኩረት በማድረግ በተማሪዎች የአማርኛ ትምህርት የማንበብና የመጻፍ ክሂሎች ላይ የመምህራንን ቃላዊና ጽሁፋዊ ምጋቤምላሽ አቀራረብ መተንተን ሲሆን በወረዳው የሚገኙ አጠቃላይ ሁለተኛ ትምህርት ቤቶች ሁለት ብቻ በመሆናቸው በጠቅላይ ንሞና ተወስደዋል፡፡ ተማሪዎች ደግሞ እጣ ናሙና መመረጣቸው ተገልጿል፡፡ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የጽሁፍ መጠይቅ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ሰነድ ፍተሻ እና የክፍል ውስጥ ምልከታ ናቸው፡፡ ስለሆነም ጥናቱ ቅኝታዊ ሂደትን የተከተለ በመሆኑ የመረጃ መሰብሰቢያዎችን በብዛትና እየደጋገመ መጠቀሙ አላማውን ያሳካ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ በዚህ መልኩ መረጃዎች በሚገባ ተሰብስበውና ለትንተና በሚያመች መልኩ ተደራጅተው ቀርበዋል፡፡

በመሆኑም የጥናቱ ግኝት ከመቅረቡ በፊት Hedge (1988) እና Raimes (1983) እንደመምህራን ስህተቶችን በማመልከት የሚጠቀሙባቸው የምጋቤምላሽ ዘዴዎች የተለያዩ ናቸው፡፡ ምልክቶችን በመጠቀም ስህተቶችን ማመልከት በሚለው የጽሁፍ ወይም የድርሰት ምጋቤምላሽ ዘዴ መምህራን ሲጠቀሙ ተማሪዎቻቸው ለሁሉም ምልክቶች እንግዳ እንዳልሆኑና ሲያጋጥሟቸው አገልግሎት እንዳላቸው በቅድሚያ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ ይጠበቅባቸዋል ይላሉ፡፡

የጓደኛ እርማትን በተመለከተ ደግሞ Byren (1988) እና Edge (1990) የብጤ ምጋቤምላሽ ተማሪዎች ተራ በተራ በሚያነቡበት ወቅት ወይም በንባብ ጊዜ የሚያስተናግዱትን ስህተት በመልቀም የሚነጋገሩበት እናያዘጋጁትን ጽሁፍ (ያከናወኑትን ሙከራ) እርስ በርስ በመለዋወጥ አንዱ የሌላውን የሚያይበትና አስተያየት የሚሰጥበት ነው፡፡

Anker (2000) መምህራን ምጋቤምላሽ ዓይነቶችን በክፍል ውስጥ ሊጠቀሙ የሚችሉት አንዱን አይነት ለብቻው ወይም አንዱን ከአንዱ ጋር በማደበላለቅ ሲሆን እያንዳንዱ የምጋቤምላሽ አይነት የራሱ የሆነ አስተዋፅኦ ወይም ጠቀሜታ ስላለው መምህራኑ ይህን ተረድተው በአጠቃቀም ጊዜ አስፈላጊውን ትኩረትና ጥንቃቄ መስጠት ይገባቸዋል በማለት ገልፀዋል፡፡

ከላይ የቀረቡት የምሁራን ገለፃዎች ምልክቶችን በመጠቀምና ማስረጃዎችን በማቅረብ ከምጋቤምላሽ አሰጣጥ ትኩረቶች አንፃር መሆን የሚገባውን ያሳዩ ናቸው፡፡ የጓደኛ እርማትም

በንባብ ወቅት ስህተቶችን ለመልቀምና በጽሁፍ ጊዜ እርስ በርስ ሃሳቦችን በመለዋወጥ መተራረም እንደሚቻል ያመላከተ ነው፡፡ በተጨማሪም የምጋቤምላሽ ዓይነቶችን መምህራን በክፍል ውስጥ ምጋቤምላሽ ሲሰጡ መጠቀም እንዳለባቸው የሚያሳዩ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ የጥናቱ ውጤት ተጠቁሟል፡፡

በመሆኑም የጥናቱ ግኝት የቋንቋ መምህራን የማንበብና መጻፍ ክሂሎችን ሲያስተምሩ ሁሉንም የምጋቤምላሽ ዓይነቶች እየቀያየሩ ወይም አንዱን ከአንዱ ጋር እያጣመሩ በሚገባ መጠቀም አለመቻላቸውን፣ ብዙውን ጊዜ የግልና የብጤ (ጓደኛ) ምጋቤምላሾችን በመጠቀም ምጋቤምላሽ እንደማይሰጡ፣ በምጋቤምላሽ አሰጣጥ ወቅት ማስረጃዎችን እንጂ ደጋፊ ምልክቶችን እንደማይጠቀሙ፣ መምህራን ምጋቤምላሻቸውን የሚያቀርቡበት መንገድ አንዳንድ ጊዜ ተለምዷዊ የሚመስል ሁኔታን የታየበት መሆኑን፣ የመምህራን ምጋቤምላሽ አቀራረብ የተለያየ መሆኑን እና የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎች የአንብቦ መረዳትና የመፃፍ ክሂሎች ላይ ቃላዊና ጽሁፋዊ የምጋቤምላሽ መስጫ መንገዶችን ቶሎ ቶሎ እየቀያየሩ እንደማይጠቀሙ ወይም ቃላዊ መንገድን እንደሚያዘወትሩ ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

## 5.2 አስተያየት

ከጥናቱ ውጤቶች በመነሳት የግል አስተያየቶችን ማስቀመጥ የተቻለ ሲሆን የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ለአራቱም የምጋቤምላሽ ዓይነቶች ትኩረት ሰጥተው ለተማሪዎች የሚገባቸውን ምጋቤምላሽ እኩል ሊባል በሚችል ደረጃ ቢሰጡ፣ መምህራንለገምጋሚ ምጋቤምላሽ ዓይነት ትኩረት በመስጠት ክፍል ውስጥ ምጋቤምላሻቸውን ማቅረብ ቢችሉ፣ ምጋቤምላሽ በሚሰጡበት ወቅት የመሰላቸትና የድካም ስሜት በአንዳንድ መምህራን የተስተዋለ ስለሆነ በይበልጥ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን በሚያስተምሩበት ወቅት ድካማቸውን ሊያስወግድ የሚችሉ ዘዴዎችን ቢያመቻቹ፣ ተማሪዎች በሚጽፉበት ወቅት አጀማመራቸውን የመከታተል ልምድ ቢኖራቸው እና በጊዜ እጥረት ምክንያት ተማሪዎች ጽፈው እስኪጨርሱ ያለመጠበቅ ሁኔታ መመልከት ስለተቻለ የትምህርት ጊዜው ለትምህርቱ በቂ የሚሆንበትን መንገድ ታሳቢ ቢያደርጉ፣ ተማሪዎች የሚሰሯቸውን ስህተቶች ደጋግመው እንዲያዩ በማድረግ በግል ማስተካከያ እንዲወስዱ ቢደረግ፣ ካለንበት ዘመን አንፃር መምህራን በየጊዜው የትምህርት ደረጃቸውን ቢያሳድጉ ወይም እንዲያሳድጉ ቢደረግ፣ መምህራን የተማሪዎችን የማንበብና የመፃፍ ክሂሎች በተደጋጋሚ ወይም ሳይሰለቹ መፈተሽ ቢችሉ፣ የተናጠልና የቡድን ስራዎችን እንዲሁም ፈተናዎችን ሰጥተው በሚያርሙበት ወቅት የፅሁፍ ምጋቤምላሾችን መስጠት ቢችሉ፣ የማንበብና መጻፍ ክሂሎች ትምህርት አቀራረብ የተሳካ እንደሚሆን ይገልፃል፡፡

# ዋቢ መጻህፍት

ሰለሞን ሐለፎም:: (1994)። "ቋንቋን የማስተማሪያ ዘዴ"። አዲስ አበባ። የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ- ፅሁፍ ትምህርት ክፍል። ኮተቤ መም/ትም/ኮሌጅ:: (ያልታተመ)።

በድሉ ዋቅጅራ:: (1996)። በስነ-ጽሁፍ ቋንቋን ማስተማር። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት።

ተስፋዬ ሸዋዬ:: (1981)፡፡ "ስነ ልሳን እና ቋንቋን ማስተማር"፣ አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል (ያልታተመ)፡፡

አስካል ማናዬ:: (2001)። "ተማሪዎች በሚጽፏቸው ድርሰቶች መምህራን የሚሰጡት ምላሾች ድርሰት የመጻፍ ችልታን በማሻሻል ረገድ ያላቸው ተጽዕኖ"። አዱስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ MA ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሁፍ። (ያልታተመ)።

አበባየሁ ::(2011)። "በሰሜን ሸዋ ዞን ውስጥ በሚገኙ አራት ሁለተኛ ትምህርት ቤቶች የፅህፈት ክሂልን ለማለማመድ በሚቀርቡ የድርሰት መልመጃዎች ላይ በመምህራን የሚሰጡ ቃላዊና ፅሁፋዊ ግብረመልሶችን መተንተን"። አዲስ አበበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት። (ያልታተመ)።

እታለማሁ ታዬ:: (2006)። "የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተማሪዎች የፅሁፍ መለማመጃ ላይ የሚሰሰጡትን ፅሁፋዊ ምጋቤምላሽ መፈተሽ"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በተግባራዊ ሥነልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት። (ያልታተመ)።

እጅጋየሁ በቀለ:: (2011)። "በተማሪዎች ድርሰት ላይ የመምህራን ፅሁፋዊ ምጋቤምላሽ ያለው አስተዋፅኦ ትንተና በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት"። ጅማ ዩኒቨርሲቲ፣ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት። (ያልታተመ)።

በካሳዬ ሙሉ:: (2008)። "በተማሪዎች ድርሰት ላይ መምህራን የሚሰጡት ምጋቤምላሽ መለያየት ምክንያት"። ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት። (ያልታተመ)።

የሻረግ ጌታነህ:: (2010)። "ቅርፅ ተኮር፣ ይዘት ተኮርና ቅርፅና ይዘት ተኮር የፅሁፍ ምጋቤምላሽ የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ችሎታ የማሻሻል ሚና፣ በዘጠነኛ ክፍል ተተኳሪነት"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በተግባራዊ ስነልሳን የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ማስተማር ፍልስፍና ዶክትሬት ዬግሪ ማሟያ ጥናት። (ያልታተመ)።

ያለው እንዳወቀ:: (2006)። የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር። አዲስ አበባ፣ አልፋ አሳታሚ።

ደረጀ ገብሬ:: (2013)፡፡ መራሒ ንባብ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ አፍሪካ ማተሚያ፡፡

ግርማ ገብሬ:: (2008)፡፡ የአማርኛ ክሂሎችን ማስተማር፡፡ አዲስ አበባ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ደሳለኝ ኪሮስ፡፡ (1994)፡፡ ሰሚናርን ሜላን ቋንቋ ትግርኛ፡፡ አዲስ አባባ፣ እሌኒ ማተሚያ፡፡

ዳንኤል ተክሉ:: (1998)፡፡ ሜላ ኣመሃህራን ክእለታትን ቋንቋ፡፡ መቐለ፣ ሜጋ ሕትመት፡፡

Anker, W. (2000). Error and Corrective Feedback: Updated theory and Classroom Practice. Forum.

Anderson.P.B. and Faust.R.K.(1975) Error Expectation AGuid for Teacher of Basic Writing.NewYork Oxford University Press.

Atkins, J and et al. (1996).Skills Development Methodology II.Addis Ababa.Addis Ababa University Press.

Alderson, J. (2000). Assessing reading. Cambridge, UK: Cambridge University.

Arends, R.J. (1997).Classroom Instruction and Management. NewYork: Graw–Hill Companies Inc.

Angelo T.A. and Cross. P.K. (1993).Classroom Assessment technique.A handbook for College Teachers San Fracisco Bass Ltd.

Abadikhah, S. (2014). Comparison of the effects of peer-versus self-editing on Linguistic accuracy of Iranian EFL students. 3L: Language, Linguistics, Literature.

Beach, R. (1979). The effect of between-draft teacher evaluation versus student Self- evaluation on high school students' revising of rough drafts.Research in the Teaching of English.

Brown, (2000).Teaching by principles an interactive approach to Language pedagogy.Second edition.Longman. Sanfransisco, California.

Byrne .D.(1991) : Teaching Writing Skills . London Longman Group.

Byrne, D. (1988). Teaching English Writing. London: Longman.

Brookhart, S.M. (2008). How to Give Effective Feedback to Your Students.U.S.A.ASCD Publication.

Cohen.A.D.& Cavalcant .M.C. (1990) Feedback.One Ceompositins Teachers and Studnts verb alrports in B.kroll (Ed). Second language.Writing. CambridgeUniversity Press.

Coll .p .G .and chan .L .k. (1994).Teaching Principles and Practice. Australia: Mcpherson is Printing Group.

Daiker.D.J. (1989) Writing and Response.Theory.Practice and Research NJ Hampton.

Diab, N. (2010). Effects of peer-versus self-editing on students" revision of Language errors in revised drafts.System.

Dechant V.E and Smith, P.H. (1987), psychology in teaching reading. (2nd Ed). Englewood Cliffs, New Jersey: prentice hall, Inc

Ellis.R. (2008). A Typology of Written Corrective feedback types. ECT Journal.

Edge .J.(1990). Mistakes and Correction. London: Longman.

Edge, J. 1988.Mistakes and Corrections. London: Longman.

Ferris, D. (1995a). Student reactions to teaching responses in multiple drafts Composition Classroom. TESOL Quaternary.

Ferris, D. (1995b). Can advanced ESL students be taught to correct their most Serious and frequent errors? TESOL Journal.

Fathman, A. and Whalley, E. (1990). Teacher Response to Student Writing: Focus on Forum Versus Content. Oxford: Oxford University Press.

Grami.M. (2005). The Effect of Teachers' Written Feedback on ESL Students Perception AA study in A Jaudi ESL University .Level Context. ARECLS Journal.Grellet, F. 1981. Developing Reading Skills. London, penquine.

Gray, J. (2004). Doing research in the real world, sage publications, London: Thousands oaks; New Delhi.

Grellet, F. (1996).Developing Reading Skills: A practical guide to Reading Comprehension Exercises. Cambridge University Press.

Grellet, F. (1986).New Developments in teaching reading comprehension skills to Ef Learners. New York: Cambridge University Press, New York.

Gipps C, Callum, B.and Hergreaves, E. (2004). What Makes A Good Primary School Teacher: Expected Class Room Strategies? USA: Library Congress Cataloging In Publication Data.

Gipp, S, Callum, B.& Hargreaves, E. (2004). What makes A good Primary School teacher: Expected classroom strategies. USA Publication.

Glue, G.R. And Jacobson, B. (2001) Sinior of writing.California, My Field Publication Company.

Hyland F. and Hayland, K. (2006).Feedback on Second Language Students Writing.Language Teaching. Cambridge: Cambridge University Press.

Hedge, T. 1988. Writing. Hong Kong: Oxford University Press.

Heaton, J. (1988). The treatment of error in written work.Modern Language Journal.

J.Charles Anderson. (2000). Assessing Reading Cambridge. Cambridge University Press.

Keh, C. (1990).Feed Backin Writing Proses: A model and method for implementing.English Language Teaching Journal.

Kepner, C. (1991)."An Experiment in the Relationship of Types Written Feedback to the Development of Second Language Writing Skills".In Modern Language Journal.

Kroll,B(E.D).(1991). Second Language Writing. Cambridge. Cambridge University Press.

Kiroll B. 1990. Second Language Writing. Cambrige: Cambrige University Press.

Lalande.J (1982).Reducing Composition Errors: An Experiment. The modem Language journal.

Leki, L. (1986). Teaching Literature of the United States to Nonnative Speakers.English Teaching forum.

Lekii.(1990). Coaching from The Margin; Issues in Written response performance In B Kroll (Ed).second Language Writing; Research Insight for the 68 Classroom. Cambridge University Press.

Lucking, I. (2008). Understanding teacher'swritten feedback practices in Hong Kong secondary classrooms. Journal of Second Language Writing.

Madson.H. (1983) Techniques in testing.Hong k) Designing tasks for the ong:Oxford University Press.

Moxley.J. (1988).Responding to student writing Goals and Methods.

Mangelsdorf, K. (1992). Peer reviews in the ESL composition classroom: What Do the students think? ELT journal.

Min, H. (2005). Training students to become successful peer reviewers. System.

Moxley, J. 1989. Responding to Student Writing: Goals, Method and Alternatives.Freshman English News.

Nuttall.C.1982. Teaching Reading Skills in A Foreign Language. London: Heinemann. Publishers.

Olson, V. (1990). The revising processes of Sixth- grade writers with and without Peer feedback. Journal of Educational Research.

Pincas, A. (1992). Teacher English writing. London: Macmillan Publishers.

Parthasarathy, R. (2014). Peer feedback in the ESL writing Classroom. A Journal of Teaching English Language and Literature.

Paulus, T. (1999).The effect of peer and teacher feedback on student writing.Journal of Second Language Writing.

Raimes, A. (1983). Techniques in teaching writing.Oxford University Press.

Richards, J.C (1991). Second Language Teacher Education. Cambridge: CUP

Shih, M. 1986. Content-based Approaches to Teaching AcademicWriting. TESOL Quarterly,

Sanja Hadzic. (2016). Oral and written teacher feedback in an English as Foreign Language class Room. Linnaeus University, Swedo.

Taylor.B. (1981) Content and Written from Two Way Street TESOLQuarterly.

Timbur.John (1985).Collaborative Learning and Teaching Writing.In perspectives On Research and scholarship in composition.Moclell and Donovan (Eds.).The Modern Language Association of America.

Ur, P. (1996). A Course in Language Teaching Practice and Theory. Cambridge: Cambridge University Press.

Veliz.C.L (2013).Corrective Feedback in second language classrooms. Lit linguist:

Willams.E. 1984.Reading in the Language Class Room.

Xingadjin.(1984). Teaching of English.Prejb College, English.Revised.

Zamel, V. (1985).Responding to student Writer TESOL Quarterly.

Zamel, V. (1983). Responding to students’ writing.TESL quarterly.Boston University of Massachusetts.

# አባሪዎች

# አባሪ ሀ:- የተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረምረቃ መርሐግብር

ለምስራቅ ጉራጌ ዞን ኬላ ወረዳ ለኬላና ጎጊቲ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበ የጽሁፍ መጠይቅ ነው፡፡

የጽሁፍ መጠይቁን ለመሙላት የተሰጠው ጊዜ 27 ደቂቃ

**ውድ ተማሪዎች፡-** መጠይቁን ለመሙላትና ለግንዛቤ እንዲሆናችሁ Kepner (1991) ምጋቤምላሽ ማለት በማንኛውም የመማር ማስተማር ሂደት ትክክል ወይም ስህተት መሆንን የምናሳይበት መሳሪያ ነው፡፡ ምጋቤምላሽ የሚለው ቃል ግብረመልስ፣ አስተያየት፣ ማስተካከያና እርማት መስጠት ከሚሉት ቃላቶች ጋር ይመሳሰላል፡፡ እነዚህን ቃላቶች አንዱን በአንዱ በመተካት መጠቀም እንደሚቻል ይገልፃሉ፡፡ ነገር ግን ቃላቶቹን በተማሪዎች ፅሁፍ ላይ ስንጠቀም የተወሰነ ልዩነት ሊኖራቸው ስለሚችል ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ ያስረዳሉ፡፡ እንደ Timbur, John (1985) አገላለጽ ደግሞ ምጋቤምላሽ ተከታታይ የሆነ ክንውንን የሚነካ የተማሪዎችን ስሜት ወደ ተወሰኑ ጉዳዮች በመማረክ እነዚህኑ ጉዳዮች በተከታታይ ክንውን ውስጥ ለውጥ እንዲያካሂዱ የሚያደርግ የክንውን መረጃ (ዜና) ነው፡፡

ሀሳቦቹ እንደሚያስገነዝቡት ምጋቤምላሽ ማለት በንባብ ጊዜና በጽህፈት ልምምድ ጊዜ የተለያዩ ስህተቶች ይሰራሉ፡፡ ስህተቶችን የማረምና የማስተካከል ሂደትን የሚመለከት ጽንሰሃሳብ ነው፡፡

ይህ የፅሁፍ መጠይቅ በምስራቅ ጉራጌ ዞን ኬላ ወረዳ የኬላና የጎጊቲ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን ትኩረት በማድረግ በተማሪዎች የአማርኛ ትምህርት የማንበብና የመፃፍ ክሂሎች ላይ ብቻ የመምህራንን ቃላዊና ፅሁፋዊ ምጋቤምላሽ አቀራረብ መተንተን ዓላማው ያደረገ ጥናት ነው፡፡ ለዚህም መረጃዎችን ሁሉ ለማግኘት የእናንተ ድርሻ የጎላ ሆኖ

ተገኝቷል፡፡ መጠይቁን በትክክል በመሙላት የተለመደ ትብብራችሁን እንድታሳዩ ተጠይቃችኂል፡፡

መጠይቁ ውስጥ የተለያዩ ጥያቄዎች የቀረቡ ስለሆነ ሁሉንም በወጉ አንብባችሁ የምሰጠውን ምላሽ ይገልፅልኛል የምትሉትን ከአማራጮች አንዱን በመጠቀም ወይም በመምረጥ የኤክስ (x) ምልክት በማድረግ እንድትመልሱ ስትጠየቁ በአክብሮት ነው፡፡ ሰንጠረዡ ውስጥ የቀረቡላችሁ ምርጫዎች በጣም እስማማለሁ፣ እስማማለሁ፣ በጥቂቱ እስማማለሁ እና አልስማማም የሚሉ ውክልናዎችን የያዙ ናቸው፡፡ ለምታደርጉት ጉልህ ትብብር ልባዊ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

ማሳሰቢያዎች፡-

- መጠይቁ ላይ ማንነትን የሚገልፅ መረጃ አትሙሉ፡፡
- ሁሉንም ጥያቄዎች መሞከር ይኖርባችኂል፡፡
- መጠይቁን ለመሙላት ውይይት አስፈላጊ አይደለም፡፡
- በስዓቱ ሞልታችሁ መመለስ ይገባል፡፡

## በተማሪዎች ብቻ የሚሞላ የጽሑፍ መጠይቅ

| ሀ | ከማንበብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ አንፃር የቀረቡ ጥያቄዎች | አማራጮች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | በጥቂቱ እስማማለሁ | አልስማማም |
| 1 | መምህራችሁ የምንባቡ ርዕስ ሰሌዳ ላይ ከፃፉ በኋላ አንብበው ያስነብቧችኋል፡፡ | | | | |
| 2 | በንባብ ጊዜ ቃላትን፣ ሐረጋትንና ዓረፍተ ነገሮችን አስተካክሉ ሲሏችሁ ወዲያውኑ ሳትረሱት ደግማችሁ በማለት ታስተካክላላችሁ፡፡ | | | | |
| 3 | በንባብ ወቅት የሚያጋጥሟችሁን መደናቀፎች (አዳዲስ ቃላት ፍች፣የሀሳብ ግልጽነት፣ የቃላት መጥበቅ መላላት፣አገባብን አለመረጋት ወዘተ) መምህራችሁ እንዲያስወግዱላችሁ ትጠይቃላችሁ፡፡ | | | | |
| 4 | መምህራችሁ ተራ በተራ ካስነበቧችሁ በኋላ ሰሌዳ ላይ የሚፅፉላችሁን አንዳንድ ማስተካከያዎች (የድምፅ ሁኔታ፣ ተደጋጋሚ ስህተት የታየባቸውን ቃላት በመፃፍ ወዘተ) ትይዟቸዋላችሁ፡፡ | | | | |
| 5 | ደጋግማችሁ እንድታነቡ ካደረጓችሁ በኋላ በምንባቡ ዙሪያ ሃሳብና ምክሮችን ሲሰጧችሁ የንባብ ልምዳችሁን ለማሻሻል ይጠቅማችኋል፡፡ | | | | |
| 6 | የምንባቦችን ፍሬ ሃሳብ እንድትገልፁ እና እንደገና ደብተራችሁ ላይ እንድታሰፍሩት በማዘዝ የፃፋችሁት ላይ ሃሳብ ይሰጡበታል፡፡ | | | | |
| 7 | በንባብ ወቅት መምህራችሁ የንባብ ጎደሏችሁን ያሳያሉ፡፡ | | | | |
| 8 | መምህራችሁ ካስነበቧችሁ በኋላ ማንኛውንም ማስተካከያ አይተው ዝም አይሉኝም፡፡ | | | | |
| 9 | ስታነቡ ቆምታ የሚያስፈልግበት ቦታ ላይ እረፍት በመውሰድ እንድታነቡ ያግዟችኋል፡፡ | | | | |
| ለ | ከመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ አንፃር የቀረቡ ጥያቄዎች | | | | |
| 1 | መምህራችሁ የቃላትና ተያያዥ ማስተካከያዎችን ይሰጧችኋል፡፡ | | | | |
| 2 | አንድ ርዕሰ ጉዳይ ሰጥተው ተደጋጋሚ እንድትፅፉ ያደርጋሉ፡፡ | | | | |
| 3 | መምህራችሁ በደብተራችን ላይ አንቀፆችን ያፅፏችኋል፡፡ | | | | |
| 4 | የፃፋችሁትን በማስነበብ ማስተካከያዎችን በቃልና በፅሁፍ ይሰጧችኋል፡፡ በማንበብና መፃፍ ክሂሎች ላይ ምጋቤምላሹ ዘወትራዊ ነው፡፡ | | | | |
| 5 | መምህራችን የጋራ የሆኑትን ስህተቶች ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ያርማሉ፡፡ | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 6 | የቃላት መረጣ፣ ስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም፣ ዓረፍተነገር አወቃቀር እና ለሌሎችም ትኩረት ሰጥጣችሁ እንድትፅፉ ይነግሯችኂል፡፡ | | | | |
| 7 | ስነ ልቦናዊና ማህበራዊ ይዘት ያላቸው ፅሁፎችን ያጽፏችኂል፡፡ | | | | |
| 8 | መምህራችሁ ፅሁፋችሁን ርስ በእርስ እንድትተያዩና እንድታቀርቡት ካደረጉ በኂላ ምጋቤምላሽ ይሰጧችኂል፡፡ | | | | |
| ሐ | ከምጋቤምላሽ ዓይነቶች አንፃር የቀረቡ ጥያቄዎች | | | | |
| 1 | በትዕዛዝ መልኩ ምጋቤምላሽ ይሰጡኛል፡፡ | | | | |
| 2 | አጠናካሪ በሆነ መንገድ ምጋቤምላሽ ይሰጡኛል | | | | |
| 3 | ግምገማ ወይም ትችት በሚመስል ሁኔታ ምጋቤምላሽ ሰይተውኝ ያውቃሉ፡፡ | | | | |
| 4 | የሚሰጠኝን አስተካካይ ምጋቤምላሽ ጊዜ ሳልወስድ አርማለሁ | | | | |
| መ | ከምጋቤምላሽ መስጫ መንገዶች አንፃር የቀረቡ ጥያቄዎች | | | | |
| 1 | መምህራችሁ አንዳንዴ በቪዲዮ ወይም ምስል ምጋቤምላሽ ይሰጣሉ፡፡ | | | | |
| 2 | መምህራችሁ በቃል ብቻ ምጋቤምላሽ የሚሰጡበት ጊዜ አለ፡፡ | | | | |
| 3 | ቃላዊ እና ፅሁፋዊ ምጋቤምላሾችን በአንድ ጊዜ የሚጠቀሙበት ጊዜ አለ፡፡ | | | | |
| ሠ | ምጋቤምላሽ ሊሰጡ ከሚችሉ አካላት አኳያ የቀረቡ ጥያቄዎች | | | | |
| 1 | መምህራችሁ ከተነበበ በኂላ የራስን ስህተት ፈልጎ ማውጣት እንደሚቻል አሳይተው ያውቃሉ፡፡ | | | | |
| 2 | መምህራችሁ እርስ በርስ በመተያየት ስህተቶችን እንድታርሙ ያደርጋሉ፡፡ | | | | |
| 3 | መምህራችሁ ራሳቸው ምጋቤምላሾችን እንዳስፈላጊነቱ ይሰጣሉ፡፡ | | | | |

## ሀ. በተማሪዎች ብቻ የሚሞላ የጽሑፍ መጠይቅ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1 | መምህራችሁ የምንባቡ ርዕስ ሰሌዳ ላይ ከፃፉ በኋላ አንብበው ያስነብቧችኋል፡፡ | X | | | |
| 2 | አንብባችሁ ስትጨርሱ እነዚህን ሃሳቦች (ዓረፍተ ነገሮች) አስተካክሉ ሲሏችሁ ወዲያውኑ ሳይረሳችሁ ታስተካክላላችሁ፡፡ | | X | | |
| 3 | በንባብ ወቅት የሚገጥሟችሁን መደናቀፎች መምህራችሁ እንዲያስወግዱላችሁ ትጠይቃላችሁ፡፡ | X | | | |
| 4 | መምህራችሁ ተራ በተራ ካስነበቧችሁ በኋላ ሰሌዳ ላይ የሚፅፉላችሁን አንዳንድ ማስተካከያዎች ትይዟቸዋላችሁ፡፡ | X | | | |
| 5 | ደጋግማችሁ እንድታነቡ ካደረጓችሁ በኋላ በምንባቡ ዙሪያ ሃሳብና ምክሮችን ሲሰጧችሁ የንባብ ልምዳችሁን ለማሻሻል ይጠቅማል፡፡ | X | | | |
| 6 | የምንባቦችን ፍሬ ሃሳብ እንድትገልፁ እና እንደገና ደብተራችሁ ላይ እንድታሰፍሩት በማዘዝ የፃፋችሁት ላይ ሃሳብ ይሰጡበታል፡፡ | | | X | |
| 7 | በንባብ ወቅት መምህራችን የጎደለንን ያሳዩናል፡፡ | | | | X |
| 8 | መምህሬ ካስነበቡኝ በኋላ ማንኛውንም ማስተካከያ አይተው ዝም አይሉኝም፡፡ | | | X | |
| 9 | ተማሪዎች ስታነቡ ቆምታ የሚያስፈልግበት ቦታ ላይ እረፍት በመውሰድ እንድታነቡ ያግዟችኋል፡፡ | | | | X |
| 10 | መምህሬ እንዴት መፃፍ እንዳለብኝ ያስተምሩኛል፡፡ | | | | X |
| 11 | መምህሬ የቃላትና ተያያዥ ማስተካከያዎችን ይሰጡኛል፡፡ | | X | | |
| 12 | አንድ ርዕሰ ጉዳይ ሰጥተው ተደጋጋሚ እንድትፅፉ ያደርጋሉ፡፡ | | | | X |
| 13 | መምህራችሁ በደብተራችን ላይ አንቀፆችን ያፅፏችኋል፡፡ | X | | | |
| 14 | የፃፋችሁትን በማስነበብ ማስተካከያዎችን በቃልና በፅሁፍ ይሰጧችኋል፡፡ በማንበብና መፃፍ ክሂሎች ላይ ምጋቤምላሹ ዘወትራዊ ነው፡፡ | | | X | |
| 15 | መምህራችን የጋራ የሆኑትን ስህተቶች ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ያርማሉ፡፡ | X | | | |
| 16 | የቃላት መረጣ፣ ስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም፣ ዓረፍተነገር አወቃቀር እና ለሌሎችም ትኩረት ሰጥጣችሁ እንድትፅፉ ይነግሯችኋል፡፡ | | X | | |
| 17 | ስነ ልቦናዊና ማህበራዊ ይዘት ያላቸው ፅሁፎችን ያጽፏችኋል፡፡ | | X | | |
| 18 | መምህራችሁ ፅሁፋችሁን ርስ በእርስ እንድትተያዩና እንድታቀርቡት ካደረጉ በኋላ ምጋቤምላሽ ይሰጧችኋል፡፡ | X | | | |

# አባሪ ለ፡- ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቀረበ ቃለ መጠይቅ

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረምረቃ መርሐግብር

**ለምስራቅ ጉራጌ ዞን ኬላ ወረዳ ለኬላና ጎጊቲ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራን ብቻ የቀረበ ቃለ መጠይቅ ነው፡፡**

**ውድ መምህራን፡-** ለቃለ መጠይቁ ሙሉ ፈቃደኛ በመሆንዎ አመሰግናለሁ፡፡ ይህ ቃለ መጠይቅ መሰረታዊ ዓላማው  በተማሪዎች የአማርኛ ትምህርት የማንበብና የመፃፍ ክሂሎች ላይ የመምህራን ቃላዊና ፅሁፋዊ ምጋቤምላሽ አቀራረብ መተንተን ነው፡፡ በመሆኑም በዓላማው ዙሪያ የተያያዙ ጥያቄዎች የቀረቡ ስለሆነ ተገቢ መልሶቻቸውን እንዲሰጡ በአክብሮት ይጠየቃሉ፡፡

1. የማንበብ ክሂልን በምታስተምሩበት ወቅት ተማሪዎች ለሚፈፅሟቸው ስህተቶች በምን መልኩ ቃላዊ ምጋቤምላሾችን ትሰጣላችሁ?
2. ንባብ ካስነበባችኋቸው በኋላ በፅሁፍ ምጋቤምላሽ ትሰጧቸዋላችሁ?
3. ምጋቤምላሽ የምትሰጡት በየትኛው የምጋቤምላሽ ዓይነት ነው? ለምን ተመራጭ ሆነ?
4. የምጋቤምላሽ ዓይነቶችን በመቀያየርይጠቀማሉ ወይስ ሁል ጊዜ የሚጠቀሙት አንዱን ብቻ ነው?
5. የመፃፍ ክሂል ላይ ምጋቤምላሽ ስትሰጡ ትኩረት የምታደርጓቸው ምንድን ናቸው?
6. ፅሁፋዊ ምጋቤምላሽ የምትሰጡት መቼ ነው?
7. የማንበብና መፃፍ ክሂሎችን ስታስተምሩ ሳይሰለቹ ለሁሉም ተማሪዎች ምጋቤምላሽ ይሰጣሉ? ከአድካሚነቱ ጋር የተያያዘ ማብራሪያ ካለዎት ብትገልፁት?
8. በምጋቤምላሽ አሰጣጥ ወቅት ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ነገሮች ካሉ ብታጋሩኝ?
9. ክለሳ ማድረግ ከምጋቤምላሽ አቀራረብ ጋር ግንኙነት አለው ብለው ያስባሉ፡፡